ምዕራፍ 1

እስከ 20 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች (20 ክፍለ ጊዜ)

መግቢያ፡ በዚህ ምዕራፍ እስከ 20 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መቁጠር፣ ማንበብና መፃፍ፣ እንዲሁም ሙሉ ቁጥሮችን ከአቻ ምስሎች ጋር ማዛመድን ይማራሉ፡፡

የምዕራፉ ዓላማዎች፡ ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- በስብስብ ውስጥ የሚገኙ ምሥሎችን ይቆጥራሉ፡፡
- እስከ 20 ድረስ ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በቃል ይቆጥራሉ፡፡
- እስከ 20 ባሉ ቁጥሮችና መጠናቸው መካከል ያለውን ዝምድና ይረዳሉ፡፡
- የአባላትን ብዛት በቁጥር ይገልፃሉ፡፡

1.1 1 እስከ 5 ያሉ ቁጥሮችን መቁጠር (3 ክፍለ ጊዜ)

መግቢያ፡ በዚህ ንዑስ ርዕስ ተማሪዎች የተለያዩ ምስሎችን ብዛት እና ከ1 እስከ 5 ያሉ መቁጠሪያ ቁጥሮችን በቃል መቁጠርን ይማራሉ፡፡

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኃላ ተማሪዎች

- በስብስብ ውስጥ የሚገኙ ከ1- 5 ያሉ ቁሶችን ይቆጥራሉ፡፡
- ከ 1 እሰከ 5 ያሉ መቁጠሪያ ቁጥሮችን በስም ይጠራሉ፡፡

ዝርዝር ዓላማዎች፡ ከዚህ ንዑስ ርዕስ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- ከ 1 እስከ 5 ያሉ ቁጥሮችን በቃል ይቆጥራሉ፡፡

ለርዕሱ የሚያስፈልጉ ግብአቶች

- በአቅራቢያቸዉ የሚገኙ ማንኛዉንም ከ 5 ያልበለጡ ቁሳቁሶችን እንዲቆጥሩ ማድረግ፡፡ **ለምሳሌ፡-** ጫማቸዉን፣የጫማ ማሰሪያቸውን የመሣሰሉትን 1፤ 2 በማለት እንዲቆጥሩ ማድረግ፤
- ሦስት ጉልቻዎች የመሣሰሉትን 1፣ 2፣ 3 በማለት እንዲቆጥሩ ማድረግ፤

- ከምስሎች የላም ጡቶች የመሣሰሉትን 1፣ 2፣ 3፣ 4 በማለት እንዲቆጥሩ ማድረግ፤
- ከምስሎች የላም እግሮች የመሣሰሉትን 1፣ 2፣ 3፣ 4 በማለት እንዲቆጥሩ ማድረግ ፤
- የእጅ ጣታቸውን 1፣ 2፣ 3፣ 4፣ 5 በማለት እንዲቆጥሩ ማድረግ ፤

የማስተማሪያ ስልቶች

- ተማሪዎች በሚያዉቁት ዜማ ቁጥሮችን ማስቆጠር፡፡
- ተማሪዎች በአካባቢያቸዉ የሚገኙትን ቁሳቁሶች 1፤ 2፤ 3፣ 4፣ 5 እያሉ እንዲቆጥሩ ማድረግ፡፡
- ተማሪዎች የእጅ ጣቶቻቸዉን ተጠቅመዉ ቁጥርን እንዲለማመዱ ማድረግ፡፡

ማብራሪያ፡

የተግበር፡ 1 መልሶች

➢ በተማሪ በመማሪያ መፅሐፍ በተግባር 1 ላይ በሰንጠረዥ የሚታዩት ምስሎች የውሃ መጠጫ ኩባያ፣ ቀይ ሽንኩርት፣ዶሮ፣ ሣህን፣ ኳስና ሙዝ ናቸው፡፡ እነዚህ ምስሎች በቤታቸውና በአካባቢያቸው ይገኛሉ፡፡

የመልመጃ-1 መልሶች

አንድ ማንኪያ

አንድ ሙዝ

አንድ ዶሮ

አንድ ኳስ

አንድ ሣህን

አንድ አፕል

አንድ ቲማቲም

አንድ ቃሪያ

ቁጥር 1 ን ማንበብና መፃፍ

መምህር/ት! ተማሪዎች የመጀመሪያውን መቁጠሪያ ቁጥር አንድን ደጋግመው አንድ እያሉ በመጥራት እንዲያስታውሱ ያድርጉ፡፡

1 አንድ

1 1 1 1

እንደሚከተለው ያቀልማሉ

1 1 1 1

እንደሚከተለው በማያያዝ ያደምቃሉ

1	1	1	1

እንደሚከተለው ደጋግመው ይፅፋሉ

1	1 ___	1 ___	1 ___

ቁጥር 2 ን ማንበብና መፃፍ

2 ሁለት

ተማሪዎች ከዚህ በታች የሚታዩትን ምስሎች በስም በመለየት ብዛታቸውን ሁለት ሁለት በማለት ደጋግመው ይጠራሉ፡፡

		
2 የቡና ሲኒዎች	2 አናናሶች	2 ቡርቱኳኖች

እንደሚከተለው ሁለት ቁጥርን ያደምቃሉ

2	2	2	2

እንደሚከተለው ሁለት ቁጥርን ደጋግመው ይፅፋሉ

2	2	2	2

ቁጥር 3 ን ማንበብና መፃፍ

3 ሦስት

ከዚህ በታች የሚታዩት የተለያዩ ምሥሎች ብዛት ሁሉም ሦስት ሲሆን ተማሪዎች የምስሎቹን ብዛት ደጋግመው ይጠራሉ።

3 ቢራቢሮዎች	 3 ዣንጥላዎች	3 ኩባያዎች

እንደሚከተለው ሥስት ቁጥርን ያደምቃሉ

3 3 3 3 3

እንደሚከተለው ሦስት ቁጥርን ደጋግመው ይፅፋሉ

3 3 3 3 3

ቁጥር 4 ን ማንበብና መፃፍ

4 አራት

ተማሪዎች አራት ቁጥርን የበለጠ ለማስታወስ ይረዳቸው ዘንድ ቁጥሩን ደጋግመው ይጠራሉ።

4 4 4 4

የመልመጃ: 2 መልሶች

እንደሚከተለው በማያያዝ አራት ቁጥርን ያደምቃሉ

4	4	4	4	4

እንደሚከተለው በመደጋገም አራት ቁጥርን ይፅፋሉ

4	4	4	4	4

ቁጥር 5 ን ማንበብና መፃፍ

5 አምስት

ተማሪዎች የምስሎቹን ብዛት በመቁጠር ደጋግመው አምስትን ይጠራሉ፡፡



5 እንቁላሎች

5 ላባዎች

የመልመጃ: 3 መልሶች

እንደሚከተለው ነጠብጣቦቹን በማያያዝ አምስት ቁጥርን ያደምቃሉ፡፡

5	5	5	5	5

ተማሪዎች በመደጋገም አምስት ቁጥርን እንደሚከተለው ይፅፋሉ፡፡

5	5	5	5	5

በመቁጠር ብዛትን መግለፅ

ተማሪዎች የተለያዩ ምስሎችን ብዛት በመቁጠር ብዛትን መግለፅ ይችላሉ፡፡

ምሳሌ፡

ሦስት መኪኖች



አምስት አበባዎች

የመልመጃ፡ 4 **መልሶች**

በመልመጃው ላይ የተጠቀሱት የምስሎቹ ብዛት በምሳሌው መሰረት ይገልፃሉ፡፡ እነርሱም 5 እርሳሶች ፣ 1 የቡና ሲኒ ፣ 4 ዣንጥላዎች እና 5 ወፎች ናቸው፡፡

የመልመጃ፡ 5 **መልሶች**

ተማሪዎች በመቁጠር ከ 1 እስከ 5 ያሉ ቁጥሮችን እንዲያነቡ ማድረግ፡፡

	አንድ	1
	ሁለት	2
	ሶስት	3
	አራት	4
	አምስት	5

የመልመጃ፡ 6 መልሶች

ተማሪዎች የምሥሎቹን ብዛት በመቁጠር በምሳሌው መሰረት በቁጥር ይፅፋሉ፡፡



	2
	1
	4
	3

የመልመጃ፡ 7 መልሶች

1. **በተሰጠው ምሳሌ መሠረት ነጥቦችን በሳጥኑ ዉስጥ ያስቀምጣሉ፡፡**

ሀ)



ሐ)



ለ)

መ)





2. ተማሪዎች በሰንጠረዡ ውስጥ ያሉትን ምስሎች በመቁጠር 3 ን፣ 5 ን፣1 ን ና 2 ን ቆጥረው ያከባሉ፡፡
3. በምሳሌው መሰረት የጎደሉትን ቁጥሮች ያስቀምጣሉ፡፡

   ሀ) 2 ለ) 4 ሐ) 2 መ) 1 ሠ) 3 እና ረ) 4

4. ሀ) 4 ለ) 1 ሐ) 3 መ) 2 ሠ) 5

ምዘና፡

- መርጃ መሣሪያን ተጠቅመው ከ 1 እስከ 5 ቁጥር መቁጠር መቻላቸውን ማረጋገጥ
- አንድ በአንድ ቁጥር መቁጠር መቻላቸዉን ማርጋገጥ
- ከምስል ጋር በማቆራኘት ከ 1 ጀምሮ ቁጥር መጥራት እንዲችሉ ማድረግ

1.2 ከ 6 እስከ 9 ያሉ መቁጠሪያ ቁጥሮች (3 ክፍለጊዜ)

መግቢያ፡ በዚህ ንዑስ ርዕስ ተማሪዎች የተለያዩ ምስሎችን ብዛት በመቁጠር ከ 6 እስከ 9 ያሉ መቁጠሪያ ቁጥሮችን በቃል መቁጠርንና መፃፍ ይማራሉ፡፡

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- ከ 1 እስከ 9 ላሉ ቁጥሮች መጠናቸዉን በትክክል ይስቀምጣሉ፤
- ምስሎችን ከቁጥሮች ጋር ያዛምዳሉ፤
- ነጠብጣቦችና የመሣሰሉትን በመጠቀም የእቃዎችን ቁጥር እስከ 9 ይለያሉ፤
- ከዕቃዎች ስብስብ እያነሱ ከ 9 ወደ ታች ይቆጥራሉ፤

ዝርዝር ዓላማዎች፡ ከዚህ ንዑስ ርዕስ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- ከ 6 ወይም ከዚያ በላይ በመጀመር እስከ 9 ያሉ ቁጥሮችን ወይም ዕቃዎችን በቃል ይቆጥራሉ፡፡

- ከ 6 እስከ 9 ያሉ ቁጥሮችን በቃል ይቆጥራሉ።

ለርዕሱ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች

- የእጅ ጣቶቻቸዉን ማስቆጠር፤
- እስከ 9 ያሉ ቁጥሮችን በካርድ ማዘጋጀት፤
- እስከ 9 ያሉ ጠጠሮች፣ እንጨቶች የመሳሰሉትን መጠቀም።

የማስተማሪያ ስልቶች

- ተማሪዎች ከ 1-9 ያሉ መቁጠሪያ ቁጥሮችን የተለያየ የአካል እንቅስቃሴን በመጠቀም እንዲቆጥሩ ማድረግ። **ለምሳሌ፡-** አንድ ሲባል ዝቅ፤ሁለት ሲባል ቀና፤ሦስት ሲባል ዝቅ ወዘተ፤ ወይም በሙዚቃ መልክ በቃል እንዲቆጥሩ ማድረግ።
- ለተማሪዎች ሊቆጠሩ የሚችሉ ቁሳቁሶችን በመስጠት በጥንድ ወይም በሦስት አድርገዉ እንዲቆጥሩ ማድረግ።
- ተማሪዎች ቁጥርን በይበልጥ እንዲረዱ ዶሚኖ ወይም ቁጥሮችን የያዘ ካርድ በመጠቀም የተለያዩ ምሳሌዎች ማሰራት።

ማብራሪያ፡ ከዚህ በታች የተገለጹትን ተግባራት እና መልመጃዎችን በመጠቀም ከ6-9 ያሉ ቁጥሮችን ማስቆጠር።

የመልመጃ፡ 8 መልሶች

1) በእያንዳንዱ ሳጥን ዉስጥ ያሉት የምሥሎች ብዛት ስድስት ስድስት ነው።
2) በሳጥን ውስጥ የሚገኙ የምስሎቹ ብዛት


6
6



6

ቁጥር 6 ን ማንበብና መፃፍ

የተግባር-2 መልሶች



መምህር/ት! ተማሪዎች ስድስት ቁጥርን ደጋግመው እንዲጠሩ ያድርጓቸው፡፡

6 ስድስት

6	6	6	6

የመልመጃ: 9 መልሶች

ተማሪዎች እንደሚከተለው ነጠብጣቦቹን በማያያዝ ያደምቃሉ፡፡

6	6	6	6	6

ተማሪዎች እንደሚከተለው በመደጋገም ስድስት ቁጥርን እንዲፅፉ ማድረግ፡፡

6	6	6	6	6	6

እንደሚከተለው በተለያዩ ቀለማት ስድስት ቁጥርን እንዲቀቡ ማድረግ፡፡

6 6 6 6 6

ቁጥር 7 ን ማንበብና መፃፍ

7 ሰባት

የተግባር- 3 የምስሎቹ ብዛት 7 ነው።

በምስል ሲቀመጥ	በቁጥር ሲፃፍ	በፊደል ሲፃፍ
	7	ሰባት

የመልመጃ፡ 10 መልሶች

ተማሪዎች ነጠብጣቦቹን በማያያዝ ሰባት ቁጥርን እንደሚከተለው ያደምቃሉ።

7 7 7 7 7

ተማሪዎች በመደጋገም 7ን እንደሚከተለው ይፅፋሉ።

7	7	7	7	7	7

ቁጥር 8ን ማንበብና መፃፍ

8 ስምንት

የተግባር- 4 መልሶች

ሀ) ተማሪዎች ስምንት ቁጥርን ደጋግመው ቢያንስ አምስት ጊዜ እንዲጠሩ ማድረግ፡፡

ለ) የተሰጡትን ምስሎች ብዛታቸው ሰምንት ነው፡፡

		
8	8	8

የመልመጃ:11 መልሶች

ሀ) ተማሪዎች እንደሚከተለው ነጠብጣቦቹን በማያያዝ አድምቀው እንዲፅፉ ማድረግ፡፡

8	8	8	8	8

ለ) ስምንት ቁጥርን እንደሚከተለው ደጋግመው እንዲፅፉ ማድረግ፡፡

8	8	8	8	8	8

ሐ) እንደሚከተለው የተለያዩ ቀለማትን በመጠቀም ያደምቃሉ፡፡

8	8	8	8	8	8

መ) የምስሎቹ ብዛት 8 ነው፡፡ ስለዚህ የምስሎቹን ስም በመጥራት ቁጥሩን ደጋግሞ ማስጠራት፡፡

8	8	8

ቁጥር 9ን ማንበብና መፃፍ

ዘጠኝ

የተግባር- 5 መልሶች

ሀ)

በምስል ሲቀመጥ	በቁጥር ሲፃፍ	በፊደል ሲፃፍ
	9	ዘጠኝ

ለ) መምህር/ት! ተማሪዎች ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ዘጠኝን አምስት ጊዜ እንዲጠሩ ያድርጉ

9	9	9	9	9

ማስታወሻ: ተማሪዎች ብዛታቸው ዘጠኝ የሆኑ የተለያዩ ቁሶችን ደጋግመው እንዲቆጥሩ ማድረግ፡፡

የመልመጃ: 12 መልሶች

ሀ) ተማሪዎች እንደሚከተለው ነጠብጣቦችን በማያያዝ ያደምቃሉ፡፡

9	9	9	9	9	9

ለ) እንደሚከተለው በተለያዩ ቀለማት አድምቀው ይፅፋሉ፡፡

9	9	9	9	9	9

ሐ) የምስሎቹ ብዛት 9 ነው፡፡

	
9	9

ምዘና፡

- ተማሪዎች ቁጥሮችን ያለ ቅደም ተከተል ተመሳሳይ ሂደትን በመጠበቅ መቁጠራቸዉን መከታተል **ለምሳሌ፡**-2፤ 4፤ 6፤ 8…በማለት ይቆጥራሉ
- ተማሪዎች ቁጥሮችን፤ ምስሎችን ወይም ጣቶቻቸዉን ማዛመድ መቻላቸዉን በቃል ጥያቄ ማረጋገጥ

የመልመጃ፡ 13 መልሶች

1. ከ 1 እስከ 9 እንደሚከተለው ደጋግሞ ይፅፋሉ።

1	1	1	1	1	1	1
2	2	2	2	2	2	2
3	3	3	3	3	3	3
4	4	4	4	4	4	4
5	5	5	5	5	5	5
6	6	6	6	6	6	6
7	7	7	7	7	7	7
8	8	8	8	8	8	8
9	9	9	9	9	9	9

2. ተማሪዎች ከታች የተሰጡትን ከ 1 እስከ 9 ያሉ ቁጥሮች ከላይ ወደ ታች ደጋግመው አምስት ጊዜ ያነባሉ።

9	9	9	9	9
8	8	8	8	8
7	7	7	7	7
6	6	6	6	6
5	5	5	5	5
4	4	4	4	4

3	3	3	3	3
2	2	2	2	2
1	1	1		1

1.3 ዜሮ ቁጥር(2 ክፍለጊዜ)

መግቢያ፡ በዚህ ንዑስ ርዕስ ተማሪዎች የተለያዩ ስብስቦችን በማየት እና ከስብስቦቹ ባዶ የሆነውን ስብስብ በመለየት የዜሮ ቁጥር ፅንሰ ሀሳብ ይረዳሉ፡፡

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኃላ ተማሪዎች፡-

- ዜሮ ቁጥርን ፅንሰ ሀሳብ ይረዳሉ፡፡

ዝርዝር ዓላማዎች፡ ከዚህ ንዑስ ርዕስ ትምህርት በኂላ ተማሪዎች፡-

- ዜሮ ቁጥርን በቃል ይጠራሉ፡፡

መግቢያ፡ በዚህ ንዑስ ርዕስ ተማሪዎች የተለያዩ ስብስቦችን በማየት እና ከስብስቦቹ ባዶ የሆነውን ስብስብ በመለየት የዜሮ ቁጥር ፅንሰ ሀሳብ ይረዳሉ፡፡

ለርዕሱ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች

- ምንም ቁሳቁሶችን ያልያዘ ወይም ባዶ ስብስብን መጠቀም

የማስተማሪያ ስልቶች

- ሁለት ስብስቦችን በመዉሰድ በአንደኛዉ ስብስብ ዉስጥ 10 ነጠብጣቦችን ማስቀመጥና በሁለተኛዉ ስብስብ ዉስጥ ደግሞ ነጠብጣቦችን ባለማስቀመጥ የዜሮ ቁጥርን ፅንሰ ሀሳብ እንዲጨብጡ ማድረግ፡፡

የተግባር-6 መልሶች

እንቁላሎቹ ሙሉ በሙሉ ከተሰበሩ ምንም እንቁላሎቹ አይቀሩም፡፡

ማብራሪያ፡

የመጀመሪያው ምሥል

የሁለተኛው ምሥል

የሦስተኛው ምሥል

- በመጀመሪያው ምሥል ሁለት ወፎች በወፍ ጎጆ ላይ አርፈው ይታያሉ፡፡
- በሁለተኛው ምሥል ከሁለት ወፎች አንዱ ተነስቶ ሲሄዱ ይታያል፡፡
- በሦስተኛው ምሥል የቀረው ሁለተኛ ወፍ ተነስቶ ሲሄዱ ይታያል፡፡አሁን በጎጆ ውስጥ ምንም ወፍ የለም፡፡ ስለዚህ ምንም ወፍ የለም የሚለውን በቁጥር ስንገልፅ 0 እንላለን፡፡

ዜሮ ምንም አባል የሌለውን ስብስብ በመጠን ለመግለጽ የምንጠቀመው ቁጥር ነው፡፡ ስለዚህ ዜሮ ቁጥር ሲሆን ባዶ ወይንም ምንም የሚለውን መጠን ይገልፃል፡፡

ዜሮን በቁጥሮች ጨረር ላይም በሚከተለው ሁኔታ መግለጽ ይቻላል



የተግባር-3 መልስ

ምንም እንቁላሎች አይቀሩም፡፡

ቁጥር 0ን ማንበብና መፃፍ

ዜሮ

ሀ) ድምፃችሁን ከፍ አድርገው አምስት ጊዜ ዜሮ በማለት ይጠራሉ፡፡

0	0	0	0	0

ለ) ተማሪዎች ነጠብጣቦችን በማያያዝ ደጋግመው ይፅፋሉ፡፡

0	0	0	0	0

ሐ) በተለያዩ ቀለማት ክፍት ቦታውን ይሞላሉ፡፡

0	0	0	0	0

ምዘና

- የክፍል ሥራ በመስጠት ዜሮ ቁጥርን ደጋግመው መፃፋቸውን ማረጋገጥ
- ለዜሮ የለቸውን ግንዛቤ በመጠየቅ

የመልመጃ፡ 14 መልሶች

በቁጥር	በፍደል
0	ዜሮ
0	ዜሮ
0	ዜሮ
0	ዜሮ

1.4 እስከ 20 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መቁጠር(4 ክፍለ ጊዜ)

መግቢያ፡ ተማሪዎች እስከ አሁን ዜሮንና አስከ ዘጠኝ ያሉ መቁጠሪያ ቁጥሮችን ተምረዋል፡፡ በዚህ ንዑስ ርዕስ ደግሞ የተለያዩ ስብስቦችን በመጠቀም እስከ 20 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በቃል መጥራትን ይለማመዳሉ፡፡

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኃላ ተማሪዎች

- እቃዎችን ሁለት ሁለት እየጨመሩ እስከ 20 ይቆጥራሉ፡፡
- ከማንኛውም ከ 20 ከሚያንስ ቁጥር በመነሳት እስከ 20 ይቆጥራሉ፡፡
- 1 እስከ 20 ያሉ መቁጠሪያ ቁጥሮችን ያለ ቅደም ተከተል በተናጠል ይረዳሉ

ዝርዝር ዓላማዎች፡ ከዚህ ንዑስ ርዕስ ትምህርት በኂላ ተማሪዎች፡-

- እስከ 20 ያሉ ቁጥሮችን በቃል ይቆጥራሉ፡፡
- እስከ 20 ያሉ ቁጥሮችን በጥንድ ይቆጥራሉ፡፡

ለርዕሱ የሚያስፈልጉ ግብአቶች

- መቁጠሪያ ካርድ ማዘጋጀት፤
- ጠጠሮችን ማዘጋጀት፤
- የተለያዩ ቁሶችን የያዘ ስብስብ በማዘጋጀት ማስቆጠር፡፡

የማስተማሪያ ስልቶች

- ተማሪዎች ከተለያየ መነሻ በመነሳት እስከ 20 ድረስ ያሉ መቁጠሪያ ቁጥሮችን እንዲቆጥሩ ማድረግ፤
- ለተማሪዎች ሊቆጠሩ የሚችሉ ቁሳቁሶችን በመስጠት በጥንድ ወይም በሦስት ሆነው እንዲቆጥሩ ማድረግ፡፡

ማብራሪያ፡ ተማሪዎች ከዚህ በታች የተቀመጡትን ቁጥሮች ያጠናሉ፡፡ ተራ በተራም በመነሳት ለክፍል ጓደኞቻቸው ቁጥሮችን ያቆጥራሉ፡፡

	10 እና 0	አሥር	10
	10 እና 1	አሥራ አንድ	11
	10 እና 2	አሥራ ሁለት	12
	10 እና 3	አሥራ ሦስት	13
	10 እና 4	አሥራ አራት	14
	10 እና 5	አሥራ አምስት	15
	10 እና 6	አሥራ ስድስት	16
	10 እና 7	አሥራ ሰባት	17

			
	10 እና 8	አሥራ ስምንት	18
	10 እና 9	አሥራ ዘጠኝ	19
	10 እና 10	ሃያ	20

ምዘና

- ያለ ቅደም ተከተል ቁጥሮችን መለየታቸዉን በቃል ጥያቄ ማረጋገጥ፡፡
- እስከ 20 ያሉ ቁጥሮችን መለየት መቻላቸውን ለማረጋገጥ የተለያዩ ብዛት ያላቸውን ስዕሎች መስጠትና ብዛታቸውን መጠየቅ፡፡
- ከአንድ ቁጥር ወደ ሌላ ቁጥር እንዲቆጥሩ መጠየቅ
- ከምስል ጋር በማቆራኘት ከ 1 ጀምሮ ቁጥር መጥራት እንዲችሉ ማድረግ

የመልመጃ፡ 15 **መልሶች**

1) ሀ) የጎደሉት ሙሉ ቁጥሮች 11፣12 እና 14 ናቸው፡፡
   ለ) የጎደሉት ሙሉ ቁጥሮች 15፣14 እና 13 ናቸው፡፡
   ሐ) የጎደሉት ሙሉ ቁጥሮች 14፣15፣16 እና 17 ናቸው፡፡
   መ) የጎደሉት ሙሉ ቁጥሮች 12፣13፣14 እና 15 ናቸው፡፡

1.5 እስከ 20 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማንበብና መፃፍ (6 ክፍለ ጊዜ)

መግቢያ፡ ተማሪዎች እስከ አሁን ድረስ እስከ 20 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ከተለያየ መነሻ መቁጠር ተምረዋል፡፡ በዚህ ንዑስ ርዕስ ደግሞ እስከ 20 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማንበብና መፃፍ ይማራሉ፡፡

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- በአሃዝና በፊደል የተፃፉ እስከ 20 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ያነባሉ፤
- እስከ 20 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በፊደል ይፅፋሉ፤
- እስከ 20 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በአሃዝ ይፅፋሉ፡፡

ዝርዝር ዓላማዎች፡ ከዚህ ንዑስ ርዕስ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- እስከ 20 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ይቆጥራሉ፡፡
- እስከ 20 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ያነባሉ፡፡
- እስከ 20 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ይፅፋሉ፡፡

ለርዕሱ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች

- በካርቶን ላይ በአሃዝና በፊደል የተፃፉ እስከ 20 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን
- በካርቶኖች የተሰሩ እስከ 20 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች ቅርፆች

የማስተማሪያ ስልቶች

- ተማሪዎች እስከ 20 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች እንዲያስተውሉ በአካባቢያቸዉ የሚገኙትን ቁሳቁሶች 1፤2፤3 ወዘተ እያሉ እንዲቆጥሩ ማድረግ፡፡
- ለተማሪዎች የተለያዩ ተግባራትን በመስጠት ተማሪዎች እስከ 20 ድረስ ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማንበብና መፃፍ በደንብ እንዲረዱ ማድረግ፡፡
- 5 እና 10 አባላትን የያዙ መቁጠሪያ ካርድ ለተማሪዎች በመስጠት ከቁሶች ጋር እንዲያዛምዱ ማድረግ፡፡

ማብራሪያ፡ መምህር/ት! ተማሪዎች ከዚህ በታች የተሰጡ ቁጥሮችን ተራ በተራ እንዲቆጥሩ ያድርጓቸው፡፡

1	**አንድ**
2	**ሁለት**
3	**ሦስት**
4	**አራት**
5	**አምስት**
6	**ስድስት**

7	ሰባት
8	ስምንት
9	ዘጠኝ
10	አሥር
11	አሥራ አንድ
12	አሥራ ሁለት
13	አሥራ ሦስት
14	አሥራ አራት
15	አሥራ አምስት
16	አሥራ ስድስት
17	አሥራ ሰባት
18	አሥራ ስምንት
19	አሥራ ዘጠኝ
20	ሃያ

ምዘና፡

- እስከ 20 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማንበብ መቻላቸውን ለማረጋገጥ የተለያዩ ቁሶችን በመስጠት እንዲያነቡ ማድረግ፡፡
- እስከ 20 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መፃፍ መቻላቸውን ለማረጋገጥ አንድን ቁጥር ደጋግመው እንዲፅፉ ማድረግ፡፡

የመልመጃ፡ 16 መልሶች

1. **ቁጥሮቹን ደጋግሞ መፃፍ**

10	10	10	10	10	10	10	10	10	10	10
11	11	11	11	11	11	11	11	11	11	11
12	12	12	12	12	12	12	12	12	12	12
13	13	13	13	13	13	13	13	13	13	13
14	14	14	14	14	14	14	14	14	14	14
15	15	15	15	15	15	15	15	15	15	15
16	16	16	16	16	16	16	16	16	16	16
17	17	17	17	17	17	17	17	17	17	17
18	18	18	18	18	18	18	18	18	18	18
19	19	19	19	19	19	19	19	19	19	19
20	20	20	20	20	20	20	20	20	20	20

1.6 እስከ 20 ያሉ መቁጠርያ ቁጥሮችን ከአቻ ምስሎች ጋር ማዛመድ (2 ክፍለ ጊዜ)

መግቢያ፡ በዚህ ንዑስ ርዕስ ተማሪዎች እስከ 20 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በመለየት ከአቻ ምስሎች ጋር ያዛምዳሉ፡፡

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- ቁጥሮችን ከመጠን ገላጭ ስዕሎች ጋር በማዛመድ ይገልፃሉ፡፡
- ቁጥሮችን ከአባላት ጋር ያዛምዳሉ፡፡

የትምህርቱ ዓላማዎች፡ ከዚህ ንዑስ ርዕስ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- እስከ 20 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ከአቻ ምስሎች ጋር ያዛምዳሉ፡፡

ለርዕሱ የሚያስፈልጉ ግብአቶች

- በካርቶን የተፃፈ ቁጥሮች እና የተሳሉ ከቁጥሮች ጋር አቻ የሆኑ ምስሎች

የማስተማሪያ ስልቶች

- 5 እና 10 አባላትን የያዙ መቁጠሪያ ካርድ ለተማሪዎች በመስጠት ከቁሶች ጋር እንዲያዛምዱ ማድረግ፡፡

ማብራሪያ

ተማሪዎች ምሥሎቹ በመቁጠር ብዛታቸውን የ ሀ.14፣ለ.16 ሐ.18 እና መ.16 በማለት ይፅፋሉ፡፡





ምዘና፡

- ተማሪዎች ቁጥሮችን፤ ምስሎችን ወይም ጣታቸዉን ማዛመድ መቻላቸዉን በቃል ጥያቄ ማረጋገጥ
- እስከ 20 ያሉ ቁጥሮችን ከስዕሎች ስብስብ ማዛመድ መቻላቸውን ማረጋገጥ

የመልመጃ፡ 17 መልሶች

የምስሎቹ ብዛት በቁጥር ሲገለፅ፡፡

ሀ) = 2

ለ) = 12

ሐ) = 7

የማጠቃለያ መልመጃ መልሶች

1. ሀ) **አሥራ ስድስት** ለ) **አሥራ ዘጠኝ** ሐ) **አሥራ ሁለት** መ) **ሃያ** ሠ) **አሥራ አምስት**
2. ሀ) 7 ለ) 13 ሐ) 14 መ) 17 ሠ) 18 ረ) 20
3. በስተግራ የተቀመጡ ነጥብጣቦችን በመቁጠር በስተቀኝ ካለው ቁጥር ጋር ያዛምዳሉ፡፡
4. በባዶው ቦታ የሚገቡ ቁጥሮች

   ሀ) 4 እና 6 ለ) 7 ሐ) 5 እና 8 መ) 6 እና 7 ሠ) 3፤6 እና 7

5.

1	2	3	4	5	6	7	8	9	10
11	12	13	14	15	16	17	18	19	20

6.

20	19	18	17	16	15	14	13	12	11
10	9	8	7	6	5	4	3	2	1

ምዕራፍ-2

ቁጥሮችን ማወዳደርና ቅደም ተከተሎቻቸዉ (11 ክፍለ ጊዜ)

መግቢያ፡ ቀደም ባለው ምዕራፍ እስከ 20 ድረስ ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መቁጠር ማንበብ እና መፃፍ ተምረዋል፡፡ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ እስከ 20 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማወዳደር እና በቅደም ተከተል ማስቀመጥን ይማራሉ፡፡

የትምህርቱ ዓላማዎች፡ ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኃላ ተማሪዎች፡-

- የሁለት ቁጥሮችን መጠን ያነፃፅራሉ፡፡
- ቁጥሮችን በቅደም ተከተላቸዉ ያስቀምጣሉ፡፡

1.1 ሁለት ሙሉ ቁጥሮችን ማወዳደር (2 ክፍለ ጊዜ)

መግቢያ፡ በዚህ ትምህርት ክፍል ሁለት እስከ 20 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ያንሳል፣ ይበልጣል እንድሁም እኩል ይሆናል እያሉ ያወዳድራሉ፡፡ ቀዳማይ እና ተከታይ እያሉ በንጽጽር ይገልጻሉ፡፡

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኃላ ተማሪዎች፡-

- የሁለት ቡድኖች የእቃዎች ብዛትን ያነፃፅራሉ፡፡

ዝርዝር ዓላማዎች፡ ከዚህ ንዑስ ርዕስ ትምህርት በኂላ ተማሪዎች፡-

- እስከ 20 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ያወዳድራሉ፡፡

ለርዕሱ የሚያስፈልጉ ግብአቶች

- የቁጥር መስመር እና መቁጠሪያ ቁሳቁሶች።

የማስተማሪያ ስልት፡

- ዶሚኖ፤ ካርድ ወይም እስከ 20 ያሉ ቁጥሮችን የሚገልፅ ማንኛዉንም መርጃ መሣሪያ በመጠቀም ተማሪዎች ከትንሹ ቁጥር ወደ ትልቁ ቁጥር በቅደም ተከተል እንዲያስቀምጡ ማድረግ።
- የተለያዩ የእንጨት ዘንጎችና የተለያየ መጠን የተገለፀባቸዉ ወረቀቶችን ለተማሪዎች በመስጠት ተማሪዎች በመገጣጠም የቁጥር መስመር አንዲሰሩና ሀሳብን እነዲያዳብሩ ማድረግ።

የተግባር-1 መልስ በቀኝ በኩል ያለው የምስል ብዛት በግራ ካለው ምስል ብዛት ይበልጣል።

የመልመጃ፡ 1 መልሶች

የጎደሉት ቁሮች ከዚህ በታች ደመቅ ብለው የተፃፉት ናቸው።

ሀ)

1	**2**	3

መ)

3	**4**	5

ለ)

2	3	4

ሠ)

1	2	3

ሐ)

1	2	**3**	4

ረ)

2	3	**4**	5

ማብራሪያ

1. **ያንሳል**

አስተዉሉ፡- < የያንሳል ምልክት ነው።

ምሳሌ



1 ኳስ 1 < 3 3 ኳሶች

የመልመጃ፡ 2 መልሶች

በምሣሌው መሠረት የምስሎቹን ብዛት ያወዳድራሉ።

ሀ)  4 ኮኮቦች	5 ኮኮቦች
4 < 5	
 2 ዳክዬ	 3 ዳክዬ
2 < 3	

2. **ይበልጣል**

አስተዉሉ፡- > የይበልጣል ምልክት ነው፡፡

ምሳሌ		
	5 ኩባያ **5 > 2**	2 ኩባያ

የመልመጃ፡ 3 መልሶች

1. በምሣሌው መሠረት መልሶቻቸው እንደሚከተሉት ናቸው፡፡

ሀ) 	
2 > 1	

ለ) 	
$5 > 3$	

ሐ)	
$4 > 1$	

2. እኩል

አስተዉሉ፡- = የእኩል ይሆናል ምልክት ነው፡፡

ምሳሌ		
		
	2 ዶሮች 2 = 2	2 ዶሮች

የመልመጃ: 4 መልሶች

በምሣሌው መሠረት መልሶቻቸው እንደሚከተለው ነው፡፡

ሀ)	
3 እርሳሶች 3 = 3	3 እርሳሶች

ለ)	
4 የሜዳ አህዮች 4 = 4	4 የሜዳ አህዮች

የመልመጃ: 5 መልስ

በምሣሌው መሠረት መልሶቻቸው እንደሚከተለው ነው::

ምሳሌ		
	1 ____________ 3	1 < 3
	2 ____________ 1	2 > 1
	4 ____________ 5	4 < 5
	3 ____________ 3	3 = 3

ሀ)			
	3 > 2	3 < 5	3 < 4
	4 > 1	1 = 1	4 > 3

ለ)			
	5 = 5	5 > 2	1 < 5
	3 = 3	5 > 4	4 = 4

ምዘና: መምህሩ የራሱን ፈጠራ በመጠቀም ተማሪዎች ከ1-20 ያሉ ቁጥሮችን እንዲቆጥሩ መጠየቅ ተማሪዎች የእጅ ጣቶቻቸዉን በመጠቀም ለእያንዳንዱ ሆሄ ተመጣጣኝ ቁጥር እንዲገልፁ የቃል ጥያቄ መጠየቅ የመሳሰሉትን መጠቀም::

2.2 ቀዳማይና ተከታይ ቁጥሮች (2 ክፍለ ጊዜ)

መግቢያ: በዚህ ንዑስ ርዕስ ተማሪዎች የሦስት ቁጥሮችን ቅደም ተከተል ይለያሉ:

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት: ከዚህ ትምህርት በኃላ ተማሪዎች

- በውስጣቸው ባሉት የዕቃዎች ብዛት መሠረት ስብስቦችን ያነፃፅራሉ፤
- በቁጥር መስመር ከቁጥር በፊት፤ በኂላ እና በቁጥሮች መካከል ያሉ ቁጥሮችን ያመለክታሉ።

ዝርዝር ዓላማዎች፡ ከዚህ ንዑስ ርዕስ ትምህርት በኂላ ተማሪዎች

- ቀዳማይ ቁጥርን ይናገራሉ።
- ተከታይ ቁጥርን ይናገራሉ።

ለርዕሱ የሚያስፈልጉ ግብአቶች

- የቁጥር መሥመር ማዘጋጀት
- ሦስት ተከታታይ ቁጥሮችን የያዘ ካርድ ማዘጋጀት

የማስተማሪያ ስልቶች

- በቁጥር መሥመር ላይ ቁጥሮችን እንዲያነፃፅሩ ማድረግ።

ማብራሪያ፡

የተግባር- 2 መልሶች

መስተግራ በኩል ያለው ምስል ትንሽ ሲሆን በስተቀኝ ያለው ደግሞ ብዙ ነው።

ምሳሌ፡		
1ሙዝ	**2ሙዞች**	**3ሙዞች**

ስለዚህ $1 < 2$ ፣ $2 < 3$ ወይም $3 > 2$ ፣ $2 > 1$

በዘህ የተነሳ 1 የ 2 ቀዳማይ ነዉ። 3 ደግሞ የ 2 ተከታይ ነዉ።

የመልመጃ፡ 6 መልሶች

1. ሀ) የ 9 ቀዳማይ 8 ሲሆን ተከታይ 10 ነዉ፡፡

   ለ) የ 8 ቀዳማይ 7 ሲሆን ተከታይ 9 ነዉ፡፡

   ሐ) የ 3 ቀዳማይ 2 ሲሆን ተከታይ 4 ነዉ፡፡

   መ) የ 7 ቀዳማይ 6 ሲሆን ተከታይ 8 ነዉ፡፡

   ሠ) የ 5 ቀዳማይ 4 ሲሆን ተከታይ 6 ነዉ፡፡

2.3 እስከ 20 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችና ቅደም ተከተሎቻቸዉ (3 ክፍለ ጊዜ)

መግቢያ፡ በዚህ ንዑስ ርዕስ ተማሪዎች እስከ 20 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን የቁጥር መሥመርን በመጠቀም በቅደም ተከተል ያስቀምጣሉ፡፡

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- በቁጥር መስመር ቁጥሮችን በቅደም ተከተላቸዉ መሰረት ያስቀምጣሉ፡፡

ዝርዝር ዓላማዎች፡ ከዚህ ንዑስ ርዕስ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- እስከ 20 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በቅደም ተከተላቸዉ መሠረት በቁጥር መሥመር ላይ ያስቀምጣሉ፡፡

ለርዕሱ የሚያስፈልጉ ግብአቶች

- እስከ 20 ያሉ ቁጥሮችን እና ተዛማጅ ምስሎችን የያዙ ካርቶኖች ማዘጋጀት፡፡
- እስከ 20 ያሉ ቁጥሮችን የያዘ የተለያዩ ወረቀቶችን በማዘጋጀት በቅደም ተከተሎቻቸዉ በቁጥር መሥመር ላይ እንዲያስቀምጡ ማድረግ፡፡

የማስተማሪያ ስልቶች

- የእንጨት ዘንግና የተለያዩ ቁጥሮችን የያዘ ወረቀት በማዘጋጀት ተማሪዎች በመገጣጠም በቅደም ተከተል እንዲያስቀምጡ ማድረግ፡፡

- ተማሪዎች በቁጥር መስመር ላይ ቁጥሮችን እንዲያነፃፅሩ ማድረግ።

ማብራሪያ፡

አስተውሉ፡ እስከ 10 ያሉ መቁጠሪያ ቁጥሮች ቅደም ተከተል ከትንሹ ወደ ትልቁ እንደሚከተለው ይሆናል።

1፣ 2፣ 3፣ 4፣ 5፣ 6፣ 7፣ 8፣ 9፣ 10

የመልመጃ፡ 7 መልሶች

1) በባዶ ቦታው የሚገቡ መልስቹ እንደሚከተሉት ናቸው።

ሀ. 7 እና 10

ሐ. 3፣ 5፣ 7፣ እና 8

መ. 4፣ 6 እና 8

ሠ. 4፣ 5፣ 6 እና 7

ረ. 8፣ 7፣ 5 እና 3

2) መልስቹ እንደሚከተሉት ናቸው።

$6 < 8$	$7 < 9$
$6 < 9$	$7 < 8$
$6 < 7$	$7 > 6$
$6 = 6$	$7 = 7$
	$7 > 5$

አስተውሉ፡ ከ 11 – 20 ያሉ የሙሉ መቁጠሪያ ቁጥሮች ቅደም ተከተል ከትንሽ ወደ ትልቅ እንደምከተለው ይሆናል።

11፣ 12፣ 13፣ 14፣ 15፣ 16፣ 17፣ 18፣ 19፣ 20

2.4 ቁጥሮችን በ 10 መመደብ (2 ክፍለ ጊዜ)

መግቢያ፡ በዚህ ንዑስ ርዕስ ተማሪዎች ከ 10 የሚበልጡ እስከ 20 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ወይም የዕቃዎችን ስብስብ በአሥር እና በባለ አንድ ሆሄ ቁጥር መልክ ያስቀምጣሉ፡፡

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኃላ ተማሪዎች፡-

- ሁለት በብዛት የተለያዩ አባላት ያሏቸዉን ስብስቦች በማዋሃድ አባላትን በ 10 ምድብ ያስቀምጣሉ

ዝርዝር ዓላማዎች፡ ከዚህ ንዑስ ርዕስ ትምህርት በኂላ ተማሪዎች፡-

- ቁጥሮችን በ 10 እና በባለ አንድ ሆሄ ቁጥር ያስቀምጣሉ፡፡

ለርዕሱ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች

- አሥር እና ከአሥር በላይ የሆኑ እስከ 20 ያሉ ጠጠሮች፣እንጨቶች፣ቆርኪዎች የመሳሰሉትን ማዘጋጀት፡፡

የማስተማሪያ ስልቶች

- አሥር እና ከአሥር በላይ የሆኑ እስከ 20 ያሉ ጠጠሮች፣ እንጨቶች፣ ቆርኪዎች የመሳሰሉትን በማዘጋጀት ተማሪዎችን 10 የመመደብ ፅንሰ ሀሳብን እንዲረዱ ማድረግ፡፡

ማብራሪያ፡ መምህር/ት ተማሪዎች የተለያዩ ቁሶችን በአሥር መአሥር አድርገው

እንዲቆጥሩና በ 10 የመመደብ ክህሎትን እንዲያዳብሩ ያድርጉ፡፡

የተግባር-3 መልስ በአንድ አሥሮችና በሰባት አንዶች፡፡

የመልመጃ፡ 8 መልሶች

ሀ) 20 = 2 አሥሮች እና 0 አንዶች አሉት፡፡

ለ) 17 = 1 አሥሮች እና 7 አንዶች አሉት፡፡

ሐ) 15 = 1 አሥሮች እና 5 አንዶች አሉት።

መ) 13 = 1 አሥሮች እና 3 አንዶች አሉት።

2.5 የቁጥር ቤት ዋጋ ሥርዓት (2 ክፍለ ጊዜ)

መግቢያ፡ በዚህ ምዕራፍ እስከ አሁን ድረስ የቁጥሮችን ማወዳደር፣ቅደም ተከተል ማስቀመጥ እና ቁጥሮችን በአሥር መመደብ አይተናል። በዚህ ንዑስ ርዕስ ደግሞ ተማሪዎች እስከ 20 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በአንድ ቤትና በአሥር ይመድባሉ።

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኃላ ተማሪዎች፡-

- ለባለ ሁለት ሆሄ ቁጥሮች የቁጥር ቤት ዋጋ ፅንሰ ሀሳብ ይረዳሉ፤
- በሙሉ ቁጥሮች ውስጥ ስንት አሥሮች እና ስንት አንዶች እንዳሉ ይናገራሉ።

ዝርዝር ዓላማዎች፡ ከዚህ ንዑስ ርዕስ ትምህርት በኂላ ተማሪዎች፡-

- ለባለ ሁለት ሆሄ ቁጥሮች የቁጥር ቤት ዋጋ ሥርዓትን ይረዳሉ።
- የቁጥሮችን መጠን በአንድ ቤት ይገልፃሉ።
- የቁጥሮችን መጠን በአሥር ቤት ይገልፃሉ።

ለርዕሱ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች

- አሥር እና ከዚያ በላይ አባላትን የያዘ ፍሬም በቆርኪ ማዘጋጀት።
- በክብሪት ቀፎ ዉስጥ አሥር እና ከዚያ በላይ የሆኑ የክብሪት እንጨት

የማስተማሪያ ስልቶች

ለባለ ሁለት ሆሄ ቁጥሮች የ 10 ቤት እና የ 1 ቤትን ዋጋ ለማስረዳት በክብሪት ቀፎ ዉስጥ ከ 10 እስከ 20 ያሉ የክብሪት እንጨት እንዲጨምሩ ማድረግ፤ የአንድ ቤት ዋጋ እና የአሥር ቤት ዋጋን ማስረዳት።

ማብራሪያ፡ ቀጥሎ ያሉትን ምስሎች ብዛት ቆጥረው እንዲናገሩ ያድርጓቸው።



10 + 5 = 15(1 አሥሮች እና 5 አንዶች)



15 + 5 = 20 (ሁለት አሥሮች እና ዜሮ አንድ)

አስተውሉ፡ ለምሳሌ አሥራ ስምንት አንድ አሥር እና ስምንት አንዶች እንደ ማለት ነው።

የሚከተሉትን አጥኑ።



10 + 0 = 10



10 + 1 = 11



10 + 2 = 12



10 + 3 = 13



10 + 4 = 14



20 + 0 = 20

የቡድን ሥራ 1 መልሶች

የተሰጠ ቁጥር	የአሥር ቤት ዋጋ	የአንድ ቤት ዋጋ
15	1	5
16	1	6
17	1	7
18	1	8
19	1	9
20	2	0

በሁለት አሃዞች የሚገለጹት ቁጥሮች ሁለት ቤት አላቸው፡፡ በስተቀኝ ያለው የአንድ ቤት ሲሆን በስተግራ ያለው የአሥር ቤት ነው፡፡

ምሳሌ:-

ሀ. 17

- 7 — የአንድ ቤት ዋጋ
- 1 — የአሥር ቤት ዋጋ

ለ. 20

- 0 — የአንድ ቤት ዋጋ
- 2 — የአሥር ቤት ዋጋ

አስተውሉ

ሀ. 17 = 10 + 7 =1 (አሥር) + 7 (አንዶች)

ለ. 20 = 20 + 0 =2 (አሥሮች) + 0 (አንድ)

ማለት ነው።

የመልመጃ: 9 መልስ

1. በምሳሌው መሠረት መልሶቹ እንደሚከተሉት ናቸው።

   12፡ 1 አሥር እና 2 አንዶች አሉት።

   ሀ) 18፡ 1 አሥር እና 8 አንዶች አሉት።

   ለ) 16፡ 1አሥር እና 6 አንዶች አሉት።

   ሐ) 11፡ 1 አሥር እና 1 አንዶች አሉት።

   መ) 19፡ 1 አሥር እና 9 አንዶች አሉት።

   ሰ) 15፡ 1 አሥር እና 5 አንዶች አሉት።

2. አሥራ አምስት ባለ አንድ ሳንቲም ዲናሮች ይሆናሉ።

የማጠቃለያ መልመጃ

1. ሀ)

0	1	2	3	4	5	6	7	8	9
10	11	12	13	14	15	16	17	18	19

ለ)

8	10	12	14	16	18	20

2. ሀ) 2፣ 4፣ 6፣ 8፣ 10፣ 12፣ 14፣ 16::

ለ) 3፣ 6፣ 9፣ 12፣ 15 ፣ 18::

ሐ) 0፣5፣10፣15፣20።

3.

የተሰጠ ቁጥር	የአሥር ቤት ዋጋ	የአንድ ቤት ዋጋ
9	-	9
6	-	6
13	1	3
14	1	4
17	1	7
16	1	6

4.

ሀ	$8 < 9$	$16 < 19$
ለ	$12 = 12$	$18 > 10$
ሐ	$10 < 8$	$10 < 18$
መ	$8 < 10$	$15 = 15$
ሠ	$11 = 11$	$13 > 12$

5. ሀ) የ16 ቀዳሚይ 15 ተከታይ 17 ይሆናል።

ለ) የ 5 ቀዳሚይ 4 ተከታይ 6 ይሆናል።

ሐ) የ 10 ቀዳሚይ 9 ተከታይ 11 ይሆናል።

6. ሀ) 13 ለ) 4 ሐ) 8 መ) 16

7. ሀ) 1፣ 2 እና 3 ለ) 4፣ 5፣ 6፣ እና 7 ሐ) 11፣ 12፣ 13፣ እና 14

መ) 8፣ 9፣ 10፣ 11 እና 12

ምዕራፍ-3

ድምራቸው ከ 20 የማይበልጡ ሙሉ ቁጥሮችን መደመር (19 ክፍለ ጊዜ)

መግቢያ፡ ድምራቸው ከ20 የማይበልጡ ባለ አንድ ሆሄ ቁጥሮች ወይም እንድሁም ባለ አንድ ሆሄ እና ባለ ሁለት ሆሄ ቁጥሮችን በተለያዩ ዜዴዎች መደመር በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ይማራሉ፡፡

የትምህርቱ ዓላማዎች፡

- መደመር የሚመለከቱ ሐረጎችን ይረዳሉ፡፡
- ድምራቸዉ ከ20 የማይበልጡ ሁለት ቁጥሮችን በተለያዩ መንገዶች ይደምራሉ፡፡

3.1 የመደመር ዐረፍተ ነገሮች (3 ክፍለ ጊዜ)

መግቢያ፡ በዚህ ትምህርት ክፍል ተማሪዎች የመደመር ፅንስ ሀሳብ እና መደመር ምልክት እንዲረዱ እንዲሁም የመደመር ሂሳባዊ አረፍተ ነገር ለይተው እንዲያውቁ ይደረጋል፡፡

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኃላ ተማሪዎች

- ሁለት የተለያዩ ስብስቦችን በማቀላቀል የድብልቁን አባላት ብዛት በመቁጠር፤ ይገልፃሉ፡፡
- የ "+" እና የ "=" ምልክትን ትርጉም ይረዳሉ፡፡

ዝርዝር አላማዎች፤ ከዚህ ንዑስ ርዕስ ትምህርት በኂላ ተማሪዎች፡-

- የመደመር ፅንስ ሀሳብን ይረዳሉ፡፡
- የመደመር ምልክት ይረዳሉ፡፡
- የመደመር ሂሳባዊ አረፍተ ነገር ለይተው ያውቃሉ፡፡

ለርዕሱ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች

- የእጅ ጣቶች
- መቁጠሪያ ቁሳቁሶች (የክብሪት እንጨቶች፣ አባከስ፣ ዶሚኖ ...ወዘተ)

የማስተማሪያ ስልት

- የመደመር ፅንሰ ሀሳብን የያዙ ተረቶችን ወይም ጨዋታዎችን ለተማሪዎች መግለፅ። **ለምሳሌ፡-** እኔ አንድ ብርቱካን ነበረኝ እህቴ ሁለት ብረቱካኖችን ሰጠችኝ በጠቅላላዉ ስንተ ብርቱካኖች ይኖሩኛል?
- የተለያየ መርጃ መሣሪያ በመጠቀም የመደመር ፅንሰ ሀሳብን ለተማሪዎች ማቅረብ። ተማሪዎች የራሳቸዉን የመደመር መንገድ ተጠቅመዉ ማለትም የእጅ ጣት በመቁጠር ፤ በአፍ ተራ በተራ በመቁጠር ወዘተ ተጠቅመዉ ምላሽ እንዲሰጡ ማድረግ።

ማብራሪያ

የተግባር-1 መልሶች

ሀ)

5

ለ)

3

ሐ)

7

መ)

5

የተግባር-2 መልሶች

4	**እና 2**	**6**

		
1	1	ይሆናል 2

		
3 ቃሪያዎች	እና 4 ቃሪያዎች	ይሆናል 7 ቃሪያዎች

ባለ አንድ ሆሄ ቁጥር ከባለ አንድ ሆሄ ቁጥር እንድሁም ባለ አንድ ሆሄ ቁጥርን ከባለ ሁለት ሆሄ ቁጥር ስንደምር ቁጥሮችን እና የመደመር ምልክት በመጠቀም በመደመር አረፍተ ነገር መግለጽ ይቻላል፡፡

በምሣሌው መሠረት መልሶቹ እንደሚከተሉት ይሆናሉ፡፡

ለ) 5 እና 2 ሲደመሩ እኩል ይሆናል 7፡፡

ሐ) 5 እና 3 ሲደመሩ እኩል ይሆናል 8፡፡

መ) 6 እና 3 ሲደመሩ እኩል ይሆናል 9፡፡

አስተውሉ ሀ. + የመደመር ምልክት ነው፡፡
ለ. = የእኩል ይሆናል ምልክት ነው፡፡

እነዚህን ምልክቶች እንደሚከተለው ያነባሉ፡፡

ምሳሌ:- ሀ. 2 + 2 = 4...... ሁለት ሲደመር ሁለት እኩል ይሆናል አራት ፡፡
ለ. 4 + 1 = 5...... አራት ሲደመር አንድ እኩል ይሆናል አምስት፡፡
ሐ. 3 + 4 = 7...... ሶስት ሲደመር አራት እኩል ይሆናል ሰባት፡፡

የመልመጃ፡ 1 መልሶች

ሀ.



3 + 2 = 5

ለ.



4 + 3 = 7

ሐ.



3 + 5 = 8

ምዘና፡

- የክፍል ስራ፣ የቤት ስራ፣ የቡድን ስራ በመስጠት ወይም በቃል በመጠየቅ ድምርን መሰረት ያደረጉ ዐረፍተ ነገሮች ተማሪዎችን መጠየቅና ምላሻቸዉንም መገምገም፡፡ **ለምሳሌ፡-** ጠረጴዛ ላይ አንድ ብርቱካን ቢኖረኝና በእጄ ሁለት ብርቱካኖች ቢኖሩኝ አጠቃላይ ስንት ብረቱካኖች ይኖሩኛል?
- የመደመር ምልክትን ወይም ትርጉሙን መረዳታቸዉን ማረጋገጥ

3.2 **በመቁጠር መደመር** (2 ክፍለ ጊዜ)

መግቢያ፡ የዚህ ንዑስ ምዕራፍ ፅንሰ ሀሳብ ለማስቀመጥ ድምራቸው እስከ 20 የሆኑ ባለ አንድ ሆሄ ቁጥሮችን ወይም ባለ አንድ እና ባለ ሁለት ሆሄ ቁጥሮችን የቁጥር መሥመር በመጠቀም መደመር ይችላሉ፡፡

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- ሁለት የተለያዩ ስብስቦችን በማቀላቀል የድብልቁን አባላት በመቁጠር ይገልፃሉ፡፡

ዝርዝር ዓላማዎች፡ ከዚህ ንዑስ ርዕስ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- ድምራቸው ከሃያ የማይበልጡ ቁጥሮችን በመቁጠር ይደምራሉ፡፡

- ድምራቸው ከሃያ የማይበልጡ ቁጥሮችን በማቀላቀል ይደምራሉ፡፡

ለርዕሱ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች

- በአቅራቢያቸዉ የሚገኙ ቁሳቁሶችን (የክብሪት እንጨት፣ አባክስ፣ ዶሚኖ ...ወዘተ)
- የተለያ ብዛት ያላቸው አባላትን የያዙ ስብስቦች

ማስተማሪያ ስልት

- በአቅራቢያቸዉ የሚገኙ ቁሳቁሶችን በመጠቀም ሁለት የተለያ ብዛት ያላቸው አባላትን የያዙ ስብስቦችን ለተማሪዎች ማቅረብ፡፡ ተማሪዎችም በመቀላቀል የስብስቡን አባላት ብዛት በቁጥር ይገልፃሉ፤
- ተማሪዎች ከ 1 እስከ 20 ያሉ ቁጥሮችን በቅደም ተከተል እንዲቆጥሩ ማድረግ፡፡ ሁለት ፤ ሦስት ወይም አምስት እየዘለሉ እንዲቆጥሩ ማድረግ፤
- ተማሪዎች እየዘለሉ መቁጠርን እንዲለማመዱ በተለያዩ ምሳሌዎች ደጋግሞ ማሰራት፤ መነሻቸዉ ከአንድ ውጪ የሆኑ ምሳሌዎችን መጠቀም፤
- ለመቁጠሪያ የሚረዱ ቁሳቁሶችን መጠቀም፡፡

ሁለት የተለያዩ ቁጥሮችን መደመር በሁለት ቦታ ተቆጥረው የተቀመጡትን ነገሮች አንድ ላይ በመቀላቀል እንደ መቁጠር ነው፡፡

የተግባር፡ 2 መልሶች

ሀ) በምሳሌ መሰረት መልሶቹ እንደሚከተሉት ናቸው፡፡

ሀ)



4 + 3 = 7

ለ)



5 + 3 = 8

ሐ)



6 + 2 = 8

የመልመጃ፡ 2 መልሶች

1) ሀ) ሦስቱ ዶሮዎች በየቀኑ አንድ አንድ እንቁላል ሲጥሉ አጠቃላይ 3 እንቁላሎች

ያገኛል፡፡

ለ) በጠቅላላዉ አየለች የተገዛላትን የደብተር ብዛት ለማወቅ እንደምራለን

$3 + 4 + 2 = 9$ ደብተሮች ተገዝቶላታል፡፡

2) ሀ) 5 ለ) 9 ሐ) 8 መ) 9 ሠ) 9 ረ) 9 ሰ) 9 ሸ)9

ምዘና፡

- የክፍል ስራ፣ የቤት ስራ፣ የቡድን ስራ በመስጠት ወይም በቃል በመጠየቅ
- ተማሪዎች በራሳቸዉ መንገድ ቁጥርን ለመደመር የተረዱበት ስልት ካለ መጠየቅና ምላሻቸዉንም መገምገም **ምሳሌ፡-** $5 + 1 = 6$፣ $7 + 2 = 9$

1. ጥያቄዉን እንዴት ተረዳችሁት? 2. እንዴት እንደተረዳችሁት ልትነግሩኝ ትችላላችሁ?

3.3 በቁጥር መስመር መደመር (2 ክፍለ ጊዜ)

መግቢያ፡ በዚህ ትህምርት ክፍል ተማሪዎች በቁጥር መስመር ቁጥሮችን በመደመር ያመለክታሉ፡፡ እንድሁም የቁጥር መስመር በመጠቀም ሁለት፣ ሦስት፣ የመሳሰሉትን እየዘለሉ ይደምራሉ ወይም ይቆጥራሉ፡፡

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኃላ ተማሪዎች

- ሁለት ባለ አንድ ሆሄ ቁጥሮችን ይደምራሉ፡፡

ዝርዝር አላማዎች፡ ከዚህ ንዑስ ርዕስ ትምህርት በኂላ ተማሪዎች፡-

- ሁለት ባለ አንድ ሆሄ ቁጥሮችን የቁጥር መስመር በመጠቀም ይደምራሉ፡፡

ለርዕሱ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች

- የቁጥር መስመር

ማስተማሪያ ስልት፡

- በቁጥር መስመር ድምራቸዉ ከ 10 ያነሱ ምሳሌዎችን በመጠቀም ድምርን ማሳየት፡፡
- በቁጥር መስመር ድምራቸዉ ከ 20 ያነሱ ባለ አንድ ሆሄ ቁጥሮችን የቁጥር መስመር በመጠቀም መደመር፡፡

ምሳሌ፡- 1) $5 + 4 =$ ____

በቁጥር መሥመር ላይ 5 እና 4 ን ይደምራሉ፡፡

መጀመሪያ በቁጥር መሥመር ላይ 5 ን አሳዩ፡፡ ቀጥሎ 4 ምድብ ወደ ቀኝ ሂዱ፡፡ የደረሳችሁበት ቁጥር መልስ ይሆናል፡፡



ስለዚህ $5 + 4 = 9$ ይሆናል፡፡

የመልመጃ፡ 3 መልሶች

1) በምሳሌው መሠረት መልሶቹ እንደሚከተሉት ናቸው፡፡

ሀ.



1 + 5 = 6

ለ.



2 + 8 = 10

ሐ.



1 + 4 = 5

መ.



2 + 6 = 8

2) በምሳሌው መሠረት መልሶቹ እንደሚከተሉት ናቸው፡፡

ሀ. $2 + 6 = 8$ **ለ.** $5 + 4 = 9$ **ሐ.** $1 + 8 = 9$ **መ.** $3 + 1$ **ሠ.** $12 + 5 = 17$

ምዘና፡ የክፍል ስራ፣ የቤት ስራየቡድን ስራ በመስጠት ወይም በቃል በመጠየቅ በቁጥር መስመር ላይ በትክክል መደመራቸውን ማረጋገጥ፡፡

3.4 አንድን ቁጥር በሁለት ቁጥሮች ድምር መፃፍ (3 ክፍለ ጊዜ)

መግቢያ፡ በዚህ ትምህርት ክፍል ተማሪዎች የተሰጣቸውን ቁጥር በሁለት ቁጥሮች ድምር

መግለፅ ይማራሉ፡፡

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኃላ ተማሪዎች፡-

- እስከ 20 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በሁለት ሙሉ ቁጥሮች ድምር ይገልፃሉ፡፡

ዝርዝር አላማዎች፡ ከዚህ ንዑስ ርዕስ ትምህርት በኂላ ተማሪዎች፡-

- የተሰጣቸውን ቁጥር በሁለት ቁጥሮች ድምር ይገልፃሉ፡፡
- የአንድ ቁጥር ድምርን በስዕላዊ መግለጫ ያሳያሉ፡፡

ለርዕሱ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች

- የተለያዩ ቁጥሮችን በሁለት የተለያ ቦታ መመደብ

ማስተማሪያ ስልት

ተማሪዎች አምስትን የሚገልፅ ሁለት የመደመር ዐረፍተ ነገር ሦስትን ተጠቅመዉ እንዲፅፉ ማድረግ፤ ለምሳሌ፡ 5 = 3 + 2 ወይም 5 = 2 + 3 ተመሳሳይ ምሳሌ በመጠቀም ደጋግሞ ማሠራት፡፡ አንድን ሙሉ ቁጥር የሁለት ሙሉ ቁጥሮች ድምር አድርጎ መግለጽ ይቻላል፡፡

የተግባር፡ 1 መልሶች

በምሳሌ መሠረት መልሶቹ እንደሚከተሉት ደምቀው የተፃፉት ናቸው፡፡

ሀ)



ለ)



ሐ)



ምዘና፡ የክፍል ስራ፣ የቤት ስራ፣ የቡድን ስራ በመስጠት ወይም በቃል በመጠየቅ የሆነ ቁጥርን በሁለት ቁጥሮች ድምር እንዲገልፁ መጠየቅ፡፡

3.5 ተመሳሳይ ቁጥሮችን መደመር (2 ክፍለ ጊዜ)

መግቢያ፡ በዚህ ትህምርት ክፍል ተማሪዎች ሁለት ተመሳሳይ ቁጥሮችን መደመር ይማራሉ፡፡

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኃላ ተማሪዎች

- ሁለት ተመሳሳይ ባለ አንድ ሆሄ ቁጥሮችን ይደምራሉ፡፡

ዝርዝር አላማዎች፡ ከዚህ ንዑስ ርዕስ ትምህርት በኂላ ተማሪዎች

- ሁለት ባለ አንድ ሆሄ ተመሳሳይ ቁጥሮችን ይደምራሉ፡
- ተመሳሳይ እና ለተመሳሳይ ቁጥሮች የቀረቡ ቁጥሮች መደመር ያውቃሉ፡፡

ለርዕሱ የሚያስፈልጉ ግብአቶች

የቁጥር ጨዋታ ማዘጋጀት(ቁጥር ያለባቸው የተለያዩ ካርዶች ማዘጋጀት)

ማስተማሪያ ስልት፡

- ተጨባጭ የሆኑ ቁሳቁሶችን ወይም ስዕላዊ መግለጫዎችን በመጠቀም ተማሪዎች የተመሳሳይ ቁጥር ድምር እንዲሠሩ ማድረግ፤ **ለምሳሌ፡-** $2 + 2$, $3 + 3$ …ወዘተ
- ለተመሳሳይ ቁጥር ድምር ቅርብ የሆኑ ምሳሌዎችን በመጠቀም ማስተማር፤

ለምሳሌ፡- $3 + 4$ ማለት $3 + 3 = 6$ ሲደመር 1፤ በዚህ የተነሳ $3 + 4 = 7$።

$4 + 5$ ማለት $4 + 4 = 8$ ሲደመር 1 ማለት ነዉ። በዚህ የተነሳ $4 + 5 = 9$።

ተመሳሳይ ቁጥሮችን መደመር ማለት በሁለት ቦታ በመጠን እኩል ተቆጥረው የተቀመጡትን ነገሮች አንድ ላይ በመቀላቀል እንደ መቁጠር ነው።

የመልመጃ፡ 4 መልሶች

1. ሀ) 8 ለ) 4 ሐ) 10
2. ሀ) 10 ለ) 12 ሐ) 8 መ) 4 ሠ) 2 ረ) 18

   ሰ) 6 ሸ) 16 ቀ) 10 በ) 0 ተ) 14 ቸ) 4

3) በምሳሌው መሠረት መልሶቹ እንደሚከተሉት ናቸው።

ሀ) 1 ለ) 7 ሐ) 5 መ) 9 ሠ) 3 ረ) 4

ሰ) 13 ሸ) 15 ቀ) 11 በ) 7 ተ) 15 ቸ) 13

ምዘና፡ የክፍል ስራ፣ የቤት ስራ፣ የቡድን ስራ በመስጠት ወይም በቃል በመጠየቅ ተመሳሳይ ቁጥሮችን መደመር መቻላቸውን ማረጋገጥ።

3.6 ሁለት ባለ አንድ ሆሄ ቁጥሮችን መደመር (3 ክፍለ ጊዜ)

መግቢያ፡ በዚህ ትህምርት ክፍል ተማሪዎች ሁለት ባለ አንድ ሆሄ ቁጥሮችን መደመር

ይማራሉ፡፡

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኃላ ተማሪዎች

- ሁለት ባለ አንድ ሆሄ ቁጥሮችን ይደምራሉ፡፡

ዝርዝር አላማዎች፡ ከዚህ ንዑስ ርዕስ ትምህርት በኂላ ተማሪዎች

- ሁለት ባለ አንድ ሆሄ ቁጥሮችን ይደምራሉ፡፡

ለርዕሱ የሚያስፈልጉ ግባቶች

- ከ 1 እስከ 9 ያሉ ቁጥሮችን በቁጥር መስመር ማዘጋጀት፡፡

ማስተማሪያ ስልት

- በቁጥር መስመር ድምራቸዉ ከ 10 ያነሱ ምሳሌዎችን በመጠቀም ድምርን ማሳየት፡፡
- ሁለት አስር አስር አባላትን የያዘ አባከስ በመጠቀም ባለ አንድ ሆሄ ከሌላ ባለ ሁለት ሆሄ ቁጥር ጋር በመደመር ማስተማር፡፡
- ወደ ጎን መደመር እና ቁልቁል መደመርን በተለያዩ ምሳሌዎች መግለፅ፡፡

የተግባር-1 መልስ

+	0	1	2	3	4	5	6	7	8	9
0	0	1	2	3	4	5	6	7	8	9
1	1	2	3	4	5	6	7	8	9	10
2	2	3	4	5	6	7	8	9	10	11
3	3	4	5	6	7	8	9	10	11	12
4	4	5	6	7	8	9	10	11	12	13
5	5	6	7	8	9	10	11	12	13	14
6	6	7	8	9	10	11	12	13	14	15
7	7	8	9	10	11	12	13	14	15	16
8	8	9	10	11	12	13	14	15	16	17
9	9	10	11	12	13	14	15	16	17	18

የመልመጃ፡ 5 መልሶች

1) ሀ) $5 + 5 = 10$ ለ) $6 + 6 = 12$ ሐ) $2 + 5 = 7$

መ) $4 + 8 = 12$ ሠ) $8 + 3 = 11$ ረ) $6 + 5 = 11$

2.

	+3
6	9
2	5
0	3
5	8
1	4
7	10
4	7
9	12
8	11

	+2
7	9
3	5
9	11
5	7
8	10
4	6
6	8
0	2
1	3

ማስታወሻ፡ ዜሮን በአንድ ሙሉ ቁጥር ላይ ብንደምር ውጤቱ እራሱ ሙሉ ቁጥሩ ነው፡፡

ምሳሌ፡

$4 + 0 = 4$ $0 + 1 = 1$ $7 + 0 = 7$

የመልመጃ፡ 6 መልሶች

1) ባዶ ቦታውን ይሞላሉ

ሀ) $3 + 0 = 3$ መ) $8 + 0 = 8$ ሰ) $4 + 0 = 4$

ለ) $5 + 0 = 5$ ሠ) $7 + 0 = 7$ ሸ) $0 + 0 = 0$

ሐ) $6 + 0 = 6$ ረ) $1 + 0 = 1$ ቀ) $0 + 9 = 9$

ምዘና

- የክፍል ስራ፣የቤት ስራ፣የቡድን ስራ በመስጠት ወይም በቃል በመጠየቅ
- ሁለት ባለ አንድ ሆሄ ቁጥሮችን መደመር መቻላቸውን ማረጋገጥ፡፡

3.7 ባለ አንድ ሆሄ ቁጥሮችን ከባለ ሁለት ሆሄ ቁጥሮች ጋር መደመር (4 ክፍለ ጊዜ)

መግቢያ፡ በዚህ ትህምርት ክፍል ተማሪዎች ባለ አንድ ሆሄ ቁጥሮችን ባለ ሁለት ሆሄ ቁጥሮች ላይ መደመርን ይማራሉ፡፡

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኃላ ተማሪዎች

- ባለ አንድ ሆሄ ቀጥርን ባለ ሁለት ሆሄ ቁጥር ላይ ይደምራሉ፡፡

ዝርዝር አላማዎች፡ ከዚህ ንዑስ ርዕስ ትምህርት በኂላ ተማሪዎች፡-

- ባለ አንድ ሆሄ ቁጥርን ከባለ ሁለት ሆሄ ቁጥር ጋር በመተንተን ይደምራሉ፡፡
- ቁልቁል ይደምራሉ፡፡

ለርዕሱ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች

- ከ 0 እስከ 20 ያሉ ቁጥሮችን ማዘጋጀት፡፡

ማስተማሪያ ስልት

- ተማሪዎች የመደመርን ፅንስ ሀሳብ በጥልቀት እንዲረዱ በአይነት እና በይዘታቸው የተለያዩ ምሳሌዎችችን በመጠቀም ማስረዳት፤ **ምሳሌ**፡ ለሚከተለው ጥያቄ የባዶ ሳጥኑን ዋጋ ፈልግ

  ሀ) $13 + 4 = ___$

  ለ) $14 + ___ = 17$

  ሐ) $__ + __ = 19$

- ሁለት አስር አስር አባላትን የያዘ አባከስ በመጠቀም ባለ አንድ ሆሄ ከሌላ ባለ ሁለት ሆሄ ቁጥር ጋር በመደመር ማስተማር፡፡
- ወደ ጎን መደመር እና ቁልቁል መደመርን በተለያዩ ምሳሌዎች መግለፅ፡፡

ምሳሌ፡

1. $\mathbf{15 + 4 = 10 + 5 + 4}$ 3) $\mathbf{16 + 2 = 10 + 6 + 2}$

$= 10 + 9 = 19$ $= 10 + 8 = 18$

2. $14 + 3 = 10 + 4 + 3$

$= 10 + 7 = 17$

የመልመጃ፡ 7 መልሶች

1. ሀ) $14 + 4 = 18$ ለ) $18 + 1 = 19$ ሐ) $12 + 7 = 19$ መ) $11 + 5 = 16$

   ሠ) $13 + 7 = 20$ ረ) $14 + 5 = 19$ ሰ) $12 + 6 = 18$ ሸ) $15 + 4 = 19$

2. ሀ) አጠቃላይ በቅርጫት ውስጥ $10 + 5 = 15$ አሻንጉሊቶች አሉ።

   ለ) $12 + 6 = 18$ በጎች አሉ።

ማስታዎሻ፡ ሁለት የተለያዩ ቁጥሮችን መደመር በሁለት ቦታ ተቆጥረው የተቀመጡትን ነገሮች አንድ ላይ በመቀላቀል እንደመቁጠር ነው።

የሚከተሉትን ምሳሌዎች አጥኑ።

ሀ.



10 + 2 = 12

የመልመጃ፡ 8 መልሶች

ሀ.



12	+ 3	= 15
ለ.		
16	+ 4	= 20

1. በምሳሌው መሠረት መልሶቹ እንደሚከተሉት ናቸው፡፡

8 + 1 = 9	5 + 13 = 18
13 + 3 = 16	16 + 3 = 19
13 + 4 = 17	14 + 6 = 20

2.

3 + 6 = 9	18 = 5 + 13
4 + 6 = 10	3 + 12 = 15
10 + 6 = 16	14 + 5 = 19
17 + 0 = 17	1 + 19 = 20

የማጠቃለያ መልመጃ

1.

$0+0=0$	$0+0+0=0$
$2+3=5$	$2+2+2=6$
$4+5=9$	$3+4+1=8$
$1+8=9$	$1+6+2=9$
$2+6=8$	$4+3+2=9$
$5+2=7$	$5+2+1=8$
$6+3=9$	$3+2+3=8$
$4+0=4$	$5+3+0=8$

2.

8	6	9	10	9	13

3. ሀ. 14 ለ. 8 ሐ. 9 መ. 3 ሠ. 9 ረ. 16

4. 2 በሬዎች + 5 በሬዎች = 7 በሬዎች

ምዕራፍ-4

እስከ 20 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መቀነስ (20 ክፍለ ጊዜ)

የትምህርቱ ዓላማዎች

- በመደመርና በመቀነስ መካከል ያለዉን ዝምድና ያውቃሉ፡፡
- ከ20 የሚያንሱ ቁጥሮችን ያለብድር ይቀናንሳሉ፡፡

መግቢያ፡ እስከ 20 ካሉ መሉ ቁጥሮች ባለ አንድ ሆሄ ቁጥርን ከሚበልጠው ባለ አንድ ሆሄ ቁጥር እንድሁም ባለ አንድ ሆሄ ቁጥርን ከባለ ሁለት ሆሄ ቁጥር መቀነስ ይቻላል፡፡ በዚህ ምዕራፍ እነዝህን የተለያዩ ዜዴዎች ይማራሉ፡፡

4.1 ከ 20 ጀምሮ ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ከ ላይ ወደ ታች መቁጠር (2 ክፍለ ጊዜ)

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኃላ ተማሪዎች

- ከላይ ወደ ታች በሁለት ሁለት እና በሦስት በሶስት ይቆጥራሉ::

ዝርዝር ዓላማዎች፡ ከዚህ ንዑስ ርዕስ ትምህርት በኂላ ተማሪዎች፡-

- ከ 20 ጀምሮ ቁጥሮችን ከላይ ወደ ታች ይቆጥራሉ፡፡
- ከ20 ወደ ታች በሁለትና በሦስት ይቆጥራሉ፡፡
- ከተለያየ መነሻ ከላይ ወደ ታች ይቆጥራሉ፡፡

መግቢያ፡ በዚህ ትምህርት ክፍል ተማሪዎች ቁጥሮችን ከላይ ወደ ታች ከ20 መነሻ በሁለት፣በሦስት እና በአምስት መቁጠርን ይማራሉ ፡፡

ለርዕሱ የሚያስፈልጉ ግብዐቶች

- የቁጥር መስመር
- መቁጠሪያ ቁሳቁሶች (የክብሪት እንጨት ፣ አባከስ ፣ ዶሚኖ ...ወዘተ)

ማስተማሪያ ስልት

- ከከፍተኛ ቁጥር ወደታች በመቁጠር ከመቀነስ ፅንሰ ሀሳብ ጋር ተያያዥ መሆኑን ለተማሪዎች በምሳሌ መግለፅ፡፡ **ምሳሌ፡-** ወደታች በ2 ልዩነት መቁጠር ማለት ከላይኛዉ ሁለት መቀነስ ማለት ነዉ፡፡ 20, 18, 16, 14, 12, 10, 8, 6, 4, 2

ማብራሪያ

ሙሉ ቁጥሮችን ከታች ወደ ላይ ማለትም ከትንሹ ሙሉ ቁጥር ወደ ትልቁ ሙሉ ቁጥር መቁጠር እንደሚቻለው ሁሉ ከላይ ወደ ታች ማለትም ከታወቀ መነሻ ትልቅ ሙሉ ቁጥር ወደ ትንሹ ሙሉ ቁጥር በመቁጠር ይማራሉ፡፡

ተማሪዎች ከታች ወደ ላይ ሲቆጥሩ የአንድ ሙሉ ተከታይ ሙሉ ቁጥሩ ቀዳማይ ሙሉ ቁጥሩን በሁለት እንደሚበልጥ መገንዘብ አለባቸው፡፡

1	2	3	4	5	6	7	8	9	10	11	12	13	14	15	16	17	18	19	20
አስከ 20 ድረስ ያሉ ሙሉ ቁጥሮች ከታች ወደ ላይ ሲቀመጡ																			

ተማሪዎች ከላይ ወደ ታች ሲቆጥሩ የአንድ ሙሉ ተከታይ ሙሉ ቁጥር ከቀዳማይ ሙሉ ቁጥሩን በሁለት እንደሚያንስ መገንዘብ አለባቸው፡፡

20	19	18	17	16	15	14	13	12	11	10	9	8	7	6	5	4	3	2	1
አስከ 20 ድረስ ያሉ ሙሉ ቁጥሮች ከላይ ወደ ታች ሲቀመጥ																			

ምዘና፡ የክፍል ስራ ፣የቤት ስራ፣የቡድን ስራ በመስጠት ወይም በቃል በመጠየቅ ተማሪዎች ቁጥሮችን ከላይ ወደ ታች በትክክል መቁጠር መቻላቸውን ማረጋገጥ፡፡

የመልመጃ 1 መልስ

ሀ)

12	10	8	6	4	2

ለ)

16	14	12	10	8	6

4.2 መቀነስ (3 ክፍለ ጊዜ)

መግቢያ፡ በዚህ ትምህርት ክፍል ተማሪዎች የመቀነስ ፅንስ ሀሳብ እና የመቀነስ ምልክት እንዲረዱ እንዲሁም የመቀነስ ሂሳባዊ አረፍተ ነገር ለይተው እንዲያውቁ ይማራሉ፡፡

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኃላ ተማሪዎች፡-

- የመቀነስ ምልክትን ለይተዉ ያዉቃሉ፡፡

ዝርዝር ዓላማዎች፡ ከዚህ ንዑስ ርዕስ ትምህርት በኂላ ተማሪዎች፡-

- መቀነስን መግለፅ ይችላሉ፡፡
- የመቀነስ ምልክትን ይለያሉ፡፡
- የመቀነስ የሂሳብ አረፍተ ነገር ለይተው ያውቃሉ፡፡

ለርእሱ የሚያስፈልጉ ግብዐቶች

- ቁጥር ያለባቸው የተለያዩ ካርዶች ማዘጋጀት
- የመቁጠሪያ ቁሳቁሶች (የክብሪት እንጨት፣ አባከስ፣ ዶሚኖ ወዘተ)

ማስተማሪያ ስልት

- ለተማሪዎች ከመቀነስ ጋር ተያያዥነት ያሏቸዉን ተረቶችን ወይም ጨዋታዎችን መንገር፤ **ለምሳሌ፡-** ሰላም ሰባት ኳሶች ነበሯት የተወሰኑ ኳሶች በጨዋታ ብዛት እና በብልሽት ጠፍተዉ አሁን በእጇ አራት ኳሶች ቀሩ፡፡ ከሰላም የጠፉት ኳሶች ስንት ናቸዉ?

ማስታወሻ፡ "–" የመቀነስ ምልክት ነው፡፡

" = " የእኩል ይሆናል ምልክት ነው፡፡

ከላይ ያየናቸውን ምሥሎች ሁኔታ እንደሚከተለው መግለጽ ይቻላል፡፡

- $3-2=1$……….ከ 3 ላይ 2 ሲቀነስ 1 ይቀራል፡፡
- $5-2=3$……….ከ 5 ላይ 2 ሲቀነስ 3 ይቀራል፡፡

የመልመጃ፡ 2 መልስ

የሚከተሉትን የቃላት ፕሮብሌሞች ስሩ፡፡

1) 3 — 1 = 2 ብርቱካኖች ይቀሩታል፡፡

2) $2 - 1 = 1$ አንድ ጠርሙስ ይቀራል፡፡

ምዘና

- ተማሪዎች በራሳቸዉ መንገድ ቁጥርን ለመቀነስ የተረዱበት ስልት ካለ መጠየቅና ምላሻቸዉንም መገምገም፡፡

ምሳሌ፡- 1) ጥያቄዉን እንዴት ተረዳችሁት?

2) እንዴት እንደተረዳችሁት ልትነግሩኝ ትችላላችሁ? የመሳሰሉ ጥያቆዎችን መጠቀም፡፡

4.3 ሙሉ ቁጥሮችን በማቀናነስ መፃፍ (2 ክፍለ ጊዜ)

መግቢያ፡ በዚህ ትምህርት ክፍል ተማሪዎች እስከ 20 ሉ ሙሉ ቁጥሮችን በማቀናነስ ይፅፋሉ፡፡

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኃላ ተማሪዎች፡-

- የመቀነስ ምልክትን ለይተዉ ያዉቃሉ፡፡

ዝርዝር ዓላማዎች፡ ከዚህ ንዑስ ርዕስ ትምህርት በኂላ ተማሪዎች

- እስከ 20 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ይቀንሳሉ፡፡
- ሁለት ባለ አንድ ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን በመቀነስ ዐረፍተ ነገር ይፅፋሉ፡፡

ለርእሱ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች

- የቁጥር መስመር
- መቁጠሪያ ቁሳቁሶች (የክብሪት እንጨት፣ አባከስ፣ ዶሚኖ ...ወዘተ)

ማስተማሪያ ስልት

- ለመቁጠሪያ የሚረዱ ቁሳቁሶችን መጠቀም

ማብራሪያ

ከዚህ ቀጥሎ የተሰጠውን ምሳሌ በማጥናት መልመጃዎችን ይሰራሉ፡፡

ምሳሌ፡- $20 - 18 = 2$፣ $18 - 16 = 2$፣ $16 - 14 = 2$

በዚህ የተነሳ ከላይ የተገለፁት ሁለት ሙሉ ቁጥሮች በመቀናነሳቸው የመጣ ውጤት ነው፡፡

የመልመጃ 3 መልስ

ሀ.



ሐ.



ምዘና

- የክፍል ስራ፣ የቤት ስራ፣ የቡድን ስራ በመስጠት ወይም በቃል በመጠየቅ ተማሪዎች ቁጥሮችን በማቀናነስ መፃፋቸውን ማረጋገጥ።

4.4 ሁለት ባለ አንድ ሆሄ ቁጥሮችን መቀነስ (3 ክፍለ ጊዜ)

መግቢያ፡ በዚህ ትምህርት ክፍል ተማሪዎች ባለ አንድ ሆሄ ሙሉ ቁጥርን ከሚበልጠው ወይም እኩል ከሆነው ባለ አንድ ሆሄ ሙሉ ቁጥር በተለያየ ዘዴ መቀነስ ይማራሉ ።

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- ከትልቁ ከባለ አንድ ሆሄ ቁጥር ትንሹን ባለ አንድ ሆሄ ቁጥር ይቀንሳሉ።

ዝርዝር ዓላማዎች፡ ከዚህ ንዑስ ርዕስ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- ሁለት ባለ አንድ ሆሄ ቁጥሮችን በመቁጠር ይቀንሳሉ።
- ሁለት ባለ አንድ ሆሄ ቁጥሮችን በቁጥር መሥመር ይቀንሳሉ።

ለርእሱ የሚያስፈልጉ ግብዐቶች

- የቁጥር መስመር
- መቁጠሪያ ቁሳቁሶች (የክብሪት እንጨት፣ አባከስ፣ ዶሚኖ ...ወዘተ)

ማስተማሪያ ስልት

- የቁጥር መስመር በመጠቀም ባለ አንድ ሆሄ ቁጥር የመቀነስ ስልትን ለተማሪዎች መግለፅ፡፡

4.4.1 በመቁጠር መቀነስ

ተማሪዎች በመቁጠር ሲቀንሱ ከአንድ ስብስብ ውስጥ ተቀናሹን በማስቀረት ወይም በማስወገድ የተቀረውን የስብስብ አባል በመቁጠር መልሱን ያስቀምጣሉ፡፡

መልመጃ፡ 4 መልሶች

1. እንደሚከተለው በመቁጠር ይቀንሳሉ

ሀ) 

7 – 6 = 1

ለ) 

4 – 2 = 2

ሐ) 

6 – 1 = 5

መ) 

9 – 5 = 4

2. መልሶቹ እንደሚከተሉት ይሆናሉ፡፡

6 − 5 = 1	9 − 5 = 4
6 − 6 = 0	8 − 3 = 5
7 − 2 = 5	9 − 9 = 0

3. መልሶቹ እንደሚከተሉት ይሆናሉ፡፡

3 − 2 = 1	6 − 4 = 2	7 − 5 = 2	3 − 3 = 0	9 − 6 = 3	8 − 7 = 1
5 − 5 = 0	4 − 3 = 1	8 − 7 = 1	6 − 2 = 4	8 − 5 = 3	1 − 1 = 0

4.4.2 የቁጥር መስመር በመጠቀም መቀነስ

ባለ አንድ ሆሄ ቁጥርን ከሚበልጠው ባለ አንድ ሆሄ ቁጥር እንድሁም ባለ አንድ ሆሄን ከባለ ሁለት ሆሄ ቁጥር የቁጥር መስመር በመጠቀም ይቀንሳሉ፡፡

ምሳሌ፡ 1) 6 − 1 = ____

በቁጥር መሥመር ላይ ከ6 ላይ 1ን መቀነስ፡፡

መጀመሪያ በቁጥር መሥመር ላይ 6ን አሳይ/ዪ፡፡ ቀጥሎ 1 ምድብ ወደ ግራ ሂድ/ጂ፡፡ የደረስክበት/ሽበት ቁጥር ልዩነት ይሆናል፡፡



ስለዚህ 6 − 1 = 5 ይሆናል፡፡

የመልመጃ፡ 5 መልስ

ሀ) መልሶቹ እንደሚከተሉት ይሆናሉ፡፡

ሀ) 6 **ለ)** 1 **ለ)** 4 − 3 = 1 **ሐ)** 9 − 6 = 3 መ) 4

ምዘና

- የክፍል ስራ፣ የቤት ስራ፣ የቡድን ስራ በመስጠት ወይም በቃል በመጠየቅ ባለ ሁለት ሆሄ ቁጥሮችን መቀነስ መቻላቸውን ማረጋገጥ
- ሁለት ቁጥሮች ሲቀናነሱ ልዩነታቸዉ 20 ወይም ከ 20 በታች የሚሰጡ ቁጥሮች ተማሪዎችን መጠየቅ

4.5 ባለ ሁለት ሆሄ ቁጥሮችን መቀነስ (3 ክፍለ ጊዜ)

መግቢያ: በዚህ ትምህርት ክፍል ተማሪዎች ባለ ሁለት ሆሄ ቁጥሮችን ያለ አነኝታ መቀነስ ይማራሉ ፡፡

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት: ከዚህ ትምህርት በኂላ ተማሪዎች

- ከ20 የሚያንሱ ባለ ሁለት ሆሄ ቁጥሮችን ያለብድር ያቀናንሳሉ፡፡

ዝርዝር ዓላማዎች: ከዚህ ንዑስ ርዕስ ትምህርት በኂላ ተማሪዎች

- ባለ ሁለት ሆሄ ቁጥሮችን ይቀንሳሉ፡፡

ለርእሱ የሚያስፈልጉ ግብዐቶች

- የቁጥር መስመር
- መቁጠሪያ ቁሳቁሶች (የክብሪት እንጨት፣ አባከስ፣ ዶሚኖ ...ወዘተ)

ማስተማሪያ ስልት

- የቁጥር መስመር ላይ ቁጥሮችን በማቀናነስ እንዲፅፉ ማድረግ ፡፡
- ለመቁጠሪያ የሚረዱ ቁሳቁሶችን መጠቀም

ማብራሪያ

ባለ ሁለት ሆሄያት ቁጥሮችን በተለያዩ ዘዴዎች መቀነስ ይቻላል፡፡ ይህም ዋናውን ቁጥር በመነጣተል ይሆናል፡፡ መምህር/ት! በተማሪው መማሪያ መፅሃፍ ላይ በተቀመጠው ምሳሌ መሠረት ተማሪዎች እንዲሰሩ ያበረታቷቸው፡፡

የመልመጃ፡ 6 መልሶች

1. መልሶቹ እንደሚከተሉት ይሆናሉ፡፡

ሀ) 10 ለ) 19 ሐ) 5 መ) 6 ሠ) 6 ረ) 9 ሰ) 10 ሸ) 11

ምዘና

- የክፍል ስራ፣ የቤት ስራ፣ የቡድን ስራ በመስጠት ወይም በቃል በመጠየቅ ተማሪዎች ባለ ሁለት ሆሄ ቁጥሮችን እንደሚቀንሱ መመልከት፡፡

4.6 የመደመርና የመቀነስ ዝምድና (5 ክፍለ ጊዜ)

መግቢያ፡ በዚህ ትምህርት ክፍል ተማሪዎች በመደመርና በመቀነስ መካከል ያለውን ዝምድና ወይም መቀነስ ማለት የመደመር ተቃራኒ ስልት መሆኑን ይማራሉ ፡፡

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኃላ ተማሪዎች

- በመደመርና በመቀነስ መካከል ያለዉን ዝምድና ይረዳሉ

ዝርዝር ዓላማዎች፡ ከዚህ ንዑስ ርዕስ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- የመደመርና የመቀነስ ዝምድናን ይረዳሉ፡፡
- መቀነስ የመደመር ተቃራኒ ስልት መሆኑን ይለያሉ፡፡

ለርእሱ የሚያስፈልጉ ግብዐቶች

- Fact family (ሞዴል)
- መቁጠሪያ ቁሳቁሶች (ቆርኪ፣ የክብሪት እንጨት፣ አባከስ እና ዶሚኖ ...ወዘተ)

ማስተማሪያ ስልት

- Fact family በመጠቀም የመደመርና የመቀነስን ዝምድና ማሳየት፡፡

  ምሳሌ፡



3 + 4 = 7
4 + 3 = 7
7 - 3 = 4
7 - 4 = 3

- ለመቁጠሪያ የሚረዱ ቁሳቁሶችን መጠቀም

ማብራሪያ

የመደመርን ውጤት በመቀነስ ወይም የመቀነስን ውጤት በመደመር ማረጋገጥ ይችላሉ።

ምሳሌ፡ ሀ) $13 + 4 = 17$ ምክንያቱም $17 - 4 = 13$ ስለሆነ ነው።

ለ) $3 + 9 = 12$ ምክንያቱም $12 - 9 = 3$ ስለሆነ ነው።

ሐ) $12 - 10 = 2$ ምክንያቱም $2 + 10 = 12$ ስለሆነ ነው።

መ) $5+14 = 19$ ምክንያቱም $19 - 14 = 5$ ስለሆነ ነው።

ሠ) $13 - 3 = 10$ ምክንያቱም $10 + 3 = 13$ ስለሆነ ነው።

የመልመጃ 6 መልሶች

ሀ)



3	+	2	=	5
2	+	3	=	5
5	-	3	=	2
5	-	2	=	3

ሐ)



5	+	3	=	8
3	+	5	=	8
8	-	5	=	3
8	-	3	=	5

ለ)



5	+	1	=	6
1	+	5	=	6
6	-	5	=	1
6	-	1	=	5

መ)



4	+	3	=	7
3	+	4	=	7
7	-	4	=	3
7	-	3	=	4

ምዘና

- የክፍል ስራ፣ የቤት ስራ፣ የቡድን ስራ በመስጠት ወይም በቃል በመጠየቅ ተማሪዎችን ጥያቄ በመጠየቅ የመደመርና የመቀነስ ዝምድና እንዲያብራሩ ማድረግ ።

4.7 የቃላት ፕሮብሌሞች (2 ክፍለ ጊዜ)

መግቢያ፡ በዚህ ትምህርት ክፍል ተማሪዎች መቀነስንና መደመርን በመጠቀም የቃላት

ፕሮብሌሞችን ይሰራሉ፡፡

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኂላ ተማሪዎች

- መደመርንና መቀነስን ያካተቱ የቃላት ፕሮብሌሞችን ይሰራሉ፡፡

ዝርዝር ዓላማዎች፡ ከዚህ ንዑስ ርዕስ ትምህርት በኂላ ተማሪዎች

- የመደመር የቃላት ፕሮብሌሞችን ይሰራሉ፡፡
- የመቀነስ የቃላት ፕሮብሌሞችን ይሰራሉ፡፡
- የመደመር እና የመቀነስ የቃላት ፕሮብሌሞችን ይሰራሉ፡፡

ለርእሱ የሚያስፈልጉ ግብዐቶች

- የቃላት ፕሮብሌም ላይ የተጠቀሱ ነገሮችን ማዘጋጀት ወይም በስዕል መልክ ማቅረብ፡፡
- መቁጠሪያ ቁሳቁሶች (የክብሪት እንጨት፣ አባከስ፣ ዶሚኖ ...ወዘተ)

ማስተማሪያ ስልት

- የመደመርና የመቀነስ ፅንሰ ሀሳብን የያዙ የቃላት ፕሮብሌሞችን ማሰራት፡፡
- ለመቁጠሪያ የሚረዱ ቁሳቁሶችን መጠቀም፡፡

የቃላት ፕሮብሌሞች መልሶች

1) ባልዲ ውስጥ የተቀመጡት የአበባዎች ብዛት 7 ነው

2) ሦስቱም አንዳንድ እርሳስ ስለወሰዱ ቦርሳው ውስጥ ምንም እርሳስ አይኖርም፡፡

ስለዚህ $3 - 3 = 0$ ይሆናል

3) ከ15 በጎች ላይ 3 በጎች ሲቀነሱ 12 በጎች ይቀራሉ

$15 - 3 = 12$

4) አቶ አለማየው በኪሱ ውስጥ 11 ብር ይኖረዋል፡፡

$18 - 7 = 11$

5) በኪሱ ሊኖር የሚችለው የብር መጠን 14 ብር ነው

$20 - 6 = 14$

ምዘና

- የክፍል ስራ፣ የቤት ስራ፣ የቡድን ስራ በመስጠት ወይም በቃል በመጠየቅ ተማሪዎች የመቀነስ ፅንሰ ሀሳብን የያዙ የቃል ፕሮብሌሞችን መስራታቸውን መከታተል ።

የማጠቃለያ መልመጃ

1.

8	14	6	7	5	19
−2	−3	−2	−6	−4	−3
6	11	4	1	1	16

2. ሀ) 6 ለ) 4 ሐ) 10 መ) 14 ሠ) 8 ረ) 5

በቁጥር መስመር ላይ መልሶች 3፣ 6 እና 7 ናቸው።

3. ሀ) ሁለቱም እንቁላሎች ወድቀው ከተሰበሩ ሳህኑ ላይ ምንም እንቁላል አይቀርም ። 2 - 2 = 0

ምዕራፍ-5

እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች (25 ክፍለ ጊዜ)

መግቢያ፡ ባለፈው ምዕራፍ እስከ 20 ያሉትን ሙሉ ቁጥሮችን ተምረዋል፡፡ እነዚህም ቁጥሮች በቅደም ተከተል የሚከተሉት ናቸው፡፡

0	1	2	3	4	5	6	7	8	9	10
11	12	13	14	15	16	17	18	19		20

በዚህ ምዕራፍ እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ይማራሉ፡፡

የትምህርቱ ዓላማዎች

- በተለየ መንገድ ከ1 እስከ 100 ያሉ ቁጥሮችን ይቆጥራሉ፡፡
- የቁጥሮችን አንፃራዊ መጠንና ዋጋ ይረዳሉ፡፡

5.1 እስከ 100 ያሉ የአሥር ብዜቶች (4 ክፍለ ጊዜ)

መግቢያ፡- በዚህ ንዑስ ርዕስ ተማሪዎች እስከ 100 ድረስ ያሉትን የአሥር ብዜት ቁጥሮች የአባላትን ብዛት ቁጥረው በመመደብ ይማራሉ፡፡

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኃላ ተማሪዎች፡-

- የአስር ብዜት የሆኑ ቁጥሮችን ይጠራሉ፡፡

ዝርዝር ዓላማዎች፡ ከዚህ ንዑስ ርዕስ ትምህርት በኂላ ተማሪዎች፡-

- የአሥር ብዜቶችን ይቆጥራሉ፡፡
- የአሥር ብዜቶችን ያነባሉ፡፡
- የአሥር ብዜቶችን ይፅፋሉ፡፡

ለርዕሱ የሚያስፈልጉ ግባቶች

- የአሥር ብዜት ቻርት ማዘጋጀት
- በአሥር ምድብ የታሰሩ የክብሪት እንጨት

የማስተማሪያ ስልቶች

- ተማሪዎች እስከ 100 ድረስ ያሉ የ10 ብዜት ቁጥሮችን በቀላል እንዲቆጥሩ ማድረግ።
- የአስር ብዜቶችን የሚገልፁ የተለያዩ መግለጫዎችን በመጠቀም የአስር ብዜትን ፅንሰ ሀሳብ ለተማሪዎች መግለፅ።
- የ 100 መግለጫ ቻርት በመጠቀም ተማሪዎች የአስር ብዜት የሆኑ ቁጥሮችን እንዲለዩ እና እንዲረዱ ማስገንዘብ።

  ማብራሪያ

የሚከተሉትን የአሥር ምድብ ቁጥሮች ያጠናሉ

	10
	**10 + 10**
	**10 + 10 + 10**
	**10 + 10 + 10 + 10**
	**10 + 10 + 10 + 10 + 10**

	$10 + 10 + 10 + 10 + 10 + 10$

$10 = 10$	አሥር
$10 + 10 = 20$	ሃያ
$20 + 10 = 30$	ሰላሣ
$30 + 10 = 40$	አርባ
$40 + 10 = 50$	ሃምሣ
$50 + 10 = 60$	ስልሳ

የቡድን ሥራ መልሶች

1. በቡድን ሆነው ያነባሉ

10	20	30	40	50	60	70	80	90	100
አሥር	ሃያ	ሠላሳ	አርባ	ሃምሳ	ስልሳ	ሰባ	ሰማንያ	ዘጠና	መቶ

2. መልስቹ እንደሚከተሉት ናቸው።

10	10	10	10	10	10	10	10	10
20	20	20	20	20	20	20	20	20
30	30	30	30	30	30	30	30	30
40	40	40	40	40	40	40	40	40
50	50	50	50	50	50	50	50	50
60	60	60	60	60	60	60	60	60

70	70	70	70	70	70	70	70	70
80	80	80	80	80	80	80	80	80
90	90	90	90	90	90	90	90	90
100	100	100	100	100	100	100	100	100

አስተውሉ 10፣ 20፣ 30፣ 40፣ 50፣ 60፣ 70፣ 80፣ 90፣ 100
የአሥር ብዜቶች ናቸው።

የመልመጃ-1 መልሶች

1) በምሳሌው መሠረት መልሶቹ እንደሚከተሉት ናቸው።

1 አሥር = 10	6 አሥሮች = 60
2 አሥሮች = 20	7 አሥሮች = 70
3 አሥሮች = 30	8 አሥሮች = 80
4አሥሮች = 40	9 አሥሮች = 90
5 አሥሮች = 50	10 አሥሮች = 100

30 = 3 አሥሮች	90 = አሥሮች
70 = አሥሮች	100 = አሥሮች
40 = አሥሮች	80 = አሥሮች
60 = አሥሮች	50 = አሥሮች
10 = አሥሮች	20 = አሥሮች

2) በምሳሌው መሠረት መልሶቹ እንደሚከተሉት ናቸው።

2 + 3 = 5 ከሆነ 20+30=50
1 + 2 = 3 ከሆነ 10+20=30
3 + 3 = 6 ከሆነ 30+30=60
4 + 2 = 6 ከሆነ 40+20=60
5 + 4 = 9 ከሆነ 50+40=90
2 + 5 = 7 ከሆነ 20+50=70

3) በምሳሌው መሠረት መልሶቹ እንደሚከተሉት ናቸው።

4 − 3 = 1 ከሆነ 40-30=10
5 − 1 = 4 ከሆነ 50-10=40
3 − 2 = 1 ከሆነ 30-20=10
5 − 4 = 1 ከሆነ 50-40=10
7 − 5 = 1 ከሆነ 70-50=20
8 − 4 = 1 ከሆነ 80-40=40

5.2 እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መቁጠር (6 ክፍለ ጊዜ)

መግቢያ፡ በዚህ ንዑስ ርዕስ ተማሪዎች እስከ 100 ድረስ ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መለየትና በቃል መቁጠር ይማራሉ፡፡

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- ከ 20 እስከ 100 ያሉ መቁጠሪያ ቁጥሮችን በሆሄና በፊደል ያነባሉ ይፅፋሉ፡፡

ዝርዝር ዓላማዎች፡ ከዚህ ንዑስ ርዕስ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ይለያሉ፡፡
- እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ያነባሉ፡፡
- እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ይፅፋሉ፡፡

ለርዕሱ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች

- እስከ 100 ያሉ ቁጥሮችን የያዘ መግለጫ ቻርት ማዘጋጀት

የማስተማሪያ ስልቶች

- እስከ 100 ያሉ ቁጥሮችን የሚገልፅ ቻርት በመጠቀም ተማሪዎች ባለ አንድ ሆሄ እና ባለ ሁለት ሆሄ ቁጥሮችን እንዲቆጥሩ ማድረግ፡፡

ማብራሪያ

በቀደመው ርዕስ እስከ 100 ያሉትን የ10 ብዜቶችን አጥንተዋል፡፡ እነዚህም ቁጥሮች በቅደም ተከተል የሚከተሉት ናቸው፡፡

10 ፣ 20 ፣ 30 ፣ 40 ፣ 50 ፣ 60 ፣ 70 ፣ 80 ፣ 90 ፣ 100

አሁን ደግሞ ከ20 እስከ 100 ያሉትን የ10 ብዜት ያልሆኑትን ሙሉ ቁጥሮች ጨምራችሁ ትማራላችሁ፡፡

የተግባር-1

	2 አሥሮች እና 3 አንድ
	1 አሥር እና 1 አንድ

ምዘና

- አስከ 100 ያሉ ቁጥሮችን በሰንጠረዥ በማዘጋጀትና ተማሪዎች ተከታታይ ቁጥሮችን ከሰንጠረዡ በመመልከት በትክክል ማንበባቸዉን እና መፃፋቸዉን መገምገም

የመልመጃ-2 መልስ

1. በባዶ ቦታው የምስሎቹን ብዛት በምሳሌው መሠረት ቆጥረው ይሞላሉ፡፡

   በቀረበው ምሳሌ መሠረት

   ሀ) 4 አሥሮች እና 6 አንዶች **ለ) 4 አሥሮች እና 7 አንዶች**

2. አንብቡ

ሃያ አንድ	21	ሃያ ስድስት	26
ሃያ ሁለት	22	ሃያ ሰባት	27
ሃያ ሦስት	23	ሃያ ስምንት	28
ሃያ አራት	24	ሃያ ዘጠኝ	29
ሃያ አምስት	25	ሠላሳ	30
ሠላሳ አንድ	31	ሠላሳ ስድስት	36
ሠላሳ ሁለት	32	ሠላሳ ሰባት	37
ሠላሳ ሦስት	33	ሠላሳ ስምንት	38
ሠላሳ አራት	34	ሠላሳ ዘጠኝ	39
ሠላሳ አምስት	35	አርባ	40
አርባ አንድ	41	አርባ ሰባት	47
ሃምሳ ዘጠኝ	59	አርባ ሁለት	42
ስልሳ ስድስት	66	አርባ ዘጠኝ	49
ዘጠና ሁለት	92	ሃምሳ ሦስት	53
ዘጠና ስድስት	96	ሰማንያ አንድ	81
ስልሳ ሁለት	62	ሰባ አራት	74
ሰማንያ ዘጠኝ	89	ዘጠና ሰባት	97
ሃምሳ ሰባት	57	ሰባ አምስት	75

3. ከዚህ በታች ያሉትን ቁጥሮች በአሃዝ ይፅፋሉ።

   ሀ) ሰላሣ ሦስት= 33 ለ) ሰባ አንድ= 71 ሐ) ሃምሳ አንድ = 51

   መ) አርባ ስድስት= 46 ሠ) አስራ ሁለት= 12

4. በምሳሌው መሠረት ባዶ ቦታውን ሙሉ።

አሥራ ሁለት ⟶ 12 ሃያ ስድስት ⟶ 26	45 ⟶ አርባ አምስት 91 ⟶ ዘጠና አንድ
ሠላሳ አንድ ⟶ ____ አርባ ዘጠኝ ⟶ ____	41 ⟶ ______ 52 ⟶ ______
ስልሳ ሁለት ⟶ ____ ሰባ አራት ⟶ ____	94 ⟶ ______ 87 ⟶ ______
ሰማንያ አራት ⟶ ____ አርባ ሦስት ⟶ ____	93 ⟶ ______ 88 ⟶ ______
ዘጠና ሰባት ⟶ ____ ሃምሳ ሁለት ⟶ ____	26 ⟶ ______ 33 ⟶ ______
አርባ ዘጠኝ ⟶ ____ ሰላሳ ስድስት ⟶ ____	48 ⟶ ______ 56 ⟶ ______
ሰባ ሰባት ⟶ ____ ሃምሳ አምስት ⟶ ____	28 ⟶ ______ 97 ⟶ ______

5. ከዚህ በታች ያሉትን ቁጥሮች በፊደል ሲፃፉ

   ሀ) 37 = ሰላሣ ሰባት ለ) 69 = ስልሣ ዘጠኝ ሐ) 83 = ሰማኒያ ሦስት

   መ) 53 =ሃምሳ ሶስት ሠ) 73 = ሰባ ሶስት

5.3 እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች ቅደም ተከተል (7 ክፍለ ጊዜ)

መግቢያ:- በዚህ ንዑስ ርዕስ ተማሪዎች እስከ 100 ድረስ ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ቅደም ተከተላቸውን መለየትና በቁጥር መሥመር ማስቀመጥ ይማራሉ።

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት: ከዚህ ትምህርት በኃላ ተማሪዎች:-

- አስከ 100 ድረስ ያሉ ቁጥሮችን በቅደም ተከተሎቻቸዉ መሰረት ይደረድራሉ።

ዝርዝር ዓላማዎች: ከዚህ ንዑስ ርዕስ ትምህርት በኂላ ተማሪዎች:-

- እሰከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በቅደም ተከተል ይናገራሉ፡፡
- እሰከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በቅደም ተከተል ይፅፋሉ፡፡
- እሰከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በቅደም ተከተል በቁጥር መሥመር ያስቀምጣሉ፡፡

ለርዕሱ የሚያስፈልጉ ግባቶች

- እስከ 100 ያሉ ቁጥሮችን የያዘ መግለጫ ቻርት ማዘጋጀት
- የቁጥር መሥመር መጠቀም

የማስተማሪያ ስልቶች

- እስከ 100 ያሉ ቁጥሮችን የሚገልፅ ቻርት በመጠቀም ተማሪዎች ባለ አንድ ሆሄ እና ባለ ሁለት ሆሄ ቁጥሮችን እንዲቆጥሩ ማድረግ እና ቅድም ተከታላቸውን ለይተው በቁጥር መሥመር እንዲያስቀምጡ መምህሩ የራሱን ዘዴ ይጠቀማል፡፡

ማብራሪያ

ጥንድ ጥንድ በመሆን የሚከተሉትን ቁጥሮች ወደ ጎንና ቁልቁል እንዲያነቡ ማድረግ፡፡

1	2	3	4	5	6	7	8	9	10
11	12	13	14	15	16	17	18	19	20
21	22	23	24	25	26	27	28	29	30
31	32	33	34	35	36	37	38	39	40
41	42	43	44	45	46	47	48	49	50
51	52	53	54	55	56	57	58	59	60
61	62	63	64	65	66	67	68	69	70
71	72	73	74	75	76	77	78	79	80
81	82	83	84	85	86	87	88	89	90
91	92	93	94	95	96	97	98	99	100

የመልመጃ-3 መልስ

1) በምሳሌው መሠረት መልሶቹ እንደሚከተሉት ናቸው፡፡

ሀ) $5 > 2$ **ስለሆነም** $50 > 20$

$4 > 3$ **ስለሆነም** $40 > 30$

$7 > 1$ **ስለሆነም** $70 > 10$

$8 > 4$ **ስለሆነም** $80 > 40$

$9 > 5$ **ስለሆነም** $90 > 50$

ለ) $6 < 9$ ስለሆነም $61 < 91$

$3 < 6$ ስለሆነም $32 < 62$

$4 < 5$ ስለሆነም $43 < 53$

$7 < 8$ ስለሆነም $77 < 87$

$6 < 7$ ስለሆነም $63 < 73$

2) **ሀ**)

$\mathbf{5 < 6}$	$\mathbf{54 < 60}$
$\mathbf{3 < 7}$	$\mathbf{39 < 70}$
$\mathbf{4 < 5}$	$\mathbf{41 < 50}$
$\mathbf{6 > 2}$	$\mathbf{60 > 28}$
$\mathbf{7 > 5}$	$\mathbf{70 > 56}$
$\mathbf{8 > 4}$	$\mathbf{80 > 44}$

ለ.

$\mathbf{6 < 7}$	67<74
$\mathbf{4 < 5}$	43<51
$\mathbf{2 < 4}$	29<46
$\mathbf{5 > 1}$	50>19
$\mathbf{6 > 2}$	66>28
$\mathbf{4 > 3}$	44>_36
$\mathbf{7 < 9}$	74<92

3) ከትንሽ ቁጥር በመጀመር በቅደም ተከተል ቁጥሮችን መዘርዘር፡፡

ሀ. 18፣ 24፣ 36፣ 42 እና 57 **ለ**. 29፣ 42፣ 60፣ 64 እና 83

ሐ. 20፣ 22፣ 30፣ 60 እና 80

4) መልሶቹ እንደሚከተለው ደምቀው የተፃፉት ናቸው፡፡

ሀ. 2፣ 4 ፣6፣ **8** 10፣12፣ **14** ፣ **16** ፣ **18** ፣ 20፡፡

ለ. 10፣ 20፣ **30** ፣ **40** ፣ 50፣ **60** ፣ **70** ፣ **80** ፣ 90፣ **100**፡፡

ሐ. 20፣ 18፣ 16፣ **14** ፣ **12** ፣ **10** ፣ **8** ፣ **6** ፣ **4** ፣ 2፡፡

መ. 5፣ 10፣ 15፣ 20፣ **25** ፣ **30** ፣ **35** ፣ **40** ፣ 45፡፡

ሠ. 100፣ 90፣ 80፣ **70** ፣ **60** ፣ **50** ፣ **40** ፣ **30** ፣ **20** ፣ 10፡፡

5) መልሶቹ እንደሚከተሉት ደምቀው የተፃፉት ናቸው፡፡

ሀ.


ለ.

ሐ.

6) በተሰጡት ሁለት ሙሉ ቁጥሮች መካከል የሚገኙ ሙሉ ቁጥሮች

ሀ) 4፣ 5፣ 6፣ 7 እና 8

ለ) 31፣ 32፣ 33፣ 34፣ 35፣ 36፣ 37፣ 38 እና 39

ሐ) 16፣ 17፣ 18፣ 19፣ 20፣ 21፣ 22፣ 23 እና 24

መ) 85፣ 86፣ 87፣ 88 እና 89

7) ከትልቅ ወደ ትንሽ በቅደም ተከተል ሲፃፉ

12 19 26 31 57 73 85 ይሆናሉ

8)



5.4 እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች የቁጥር ቤት ዋጋ (8 ክፍለ ጊዜ)

መግቢያ፡- በዚህ ንዑስ ርዕስ ተማሪዎች እስከ 100 ላሉ ቁጥሮች በቁጥር ቤት ዋጋ ሥርዓት የአንድ ቤትና የአሥር ቤትን ለይቶ ማወቅ ይማራሉ፡፡

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኃላ ተማሪዎች

- የባለ ሁለት ሆሄ ቁጥርን የአንድና የአስር ቤት ዋጋ ይለያሉ

ዝርዝር ዓላማዎች፡ ከዚህ ንዑስ ርዕስ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- የአንድ ቤትን ይለያሉ፡፡
- የአሥር ቤትን ይለያሉ፡፡

ለርዕሱ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች

- የቁጥር ቤት ዋጋ ሥርዓት የያዘ ቻርት ማዘጋጀት፡፡

የማስተማሪያ ስልቶች

ለተማሪዎች የክብሪት ቀፎ በመስጠት በአስር አስር ምድብ እንዲቆጥሩ ማድረግ፡፡ በመጨረሻም ተማሪዎችን ስንት ባለ አስር ምድብ እና ስንት ባለ አንድ ምድብ እንዳለ በመጠየቅ ስለቁጥር ቤት ሥርዓት ማስተማር፡፡

ማብራሪያ፡ ቀደም ብለን እንዳየነው፤ ለምሳሌ 25 ማለት 20 + 5 ማለት ነው፡፡ ይህ ደግሞ ሁለት አስሮች እና 5 አንዶች ማለት ነው፡፡

ስለዚህ የ25 የአሥር ቤት ዋጋ 2 ስሆን የአንድ ቤት ዋጋው 5 ነው፡፡ በዚህ መሠረት የ25ን የቁጥር ቤት ዋጋ በሚከተለው መልክ መግለጽ ይቻላል፡፡

የሎቹንም ቁጥሮች የቤት ዋጋ በዚሁ ዓይነት መግለጽ ይቻላል፡፡

ምሳሌ

የተሰጠው ቁጥር	የአሥር ቤት ዋጋ	የአንድ ቤት ዋጋ
52	5	2
36	3	6

48	4	8

በዚህ ምሳሌ የተገለጹትን ቁጥሮች በሚከተለው ሁኔታ የዋጋ ቤታቸውን መግለጽ ይቻላል።

$52 = 50 + 2$ (5 አሥሮች እና 2 አንዶች)

$36 = 30 + 6$ (3 አሥሮች እና 6 አንዶች)

$48 = 40 + 8$ (4 አሥሮች እና 8 አንዶች)

የመልመጃ-4 መልሶች

1. በተሰጠው ምሳሌ መሠረት ባዶ ቦታው እንደሚከተለው ይሆናል

ሙሉ ቁጥር	የአሥር ቤት ዋጋ	የአንድ ቤት ዋጋ
18	1	8
24	2	4
80	8	0
31	3	1
46	4	6
85	8	5
93	9	3

2. አሥሮችንና እና አንዶችን ይገልፃሉ።

ሀ) 42 = 4 አሥሮች እና 2 አንዶች አሉት።

ለ) 36 = 3 አሥሮች እና 6 አንዶች አሉት።

ሐ) 67 = 6 አሥሮች እና 7 አንዶች አሉት።

መ) 85 = 8 አሥሮች እና 5 አንዶች አሉት።

ሠ) 78 = 7 አሥሮች እና 8 አንዶች አሉት።

3. ቀጥሎ ያሉትን ቁጥሮች በአሃዝ ፃፏቸው፡፡

ሀ) 59　　　　ለ) 85　　　　ሐ) 40

የማጠቃለያ መልመጃ

1.

ሀ) የ 10 ቀዳማይ 9 ሲሆን ተከታይ 11 ነዉ፡፡

ለ) የ 30 ቀዳማይ 29 ሲሆን ተከታይ 31 ነዉ፡፡

ሐ) የ 51 ቀዳማይ 50 ሲሆን ተከታይ 52 ነዉ፡፡

መ) የ 75 ቀዳማይ 74 ሲሆን ተከታይ 76 ነዉ፡፡

ሠ) የ 99 ቀዳማይ 98 ሲሆን ተከታይ 100 ነዉ፡፡

1. ባዶ ቦታውን ሙሉ፡፡

ሀ) 20፣ 25፣30፣ 35፣ 40 ፣45፣ 50 ፣55 ::

ለ) 10፣ 20፣ 30፣ 40፣ 50፣ 60፣ 70፣ 80፣ 90፣ 100 ::

ሐ) 15፣ 25፣ 35፣ 45፣ 55፣ 65፣ 75 ፣ 85፣ 95፡፡

2. ሀ) የ26 ቀዳማይ **25**　　ለ) የ35 ቀዳማይ **34**　　ሐ) የ50 ቀዳማይ **49**

መ) የ66 ቀዳማይ **65**　　ሠ) የ 84 ቀዳማይ **83**

3. ሀ) የ 21 ተከታይ **22**　　ለ) የ 32 ተከታይ **33**　　ሐ) የ37 ተከታይ **38**

መ) 55 ተከታይ **56**　　ሠ) የ 99 ተከታይ **100**

4. ሀ) 26፣ 27፣ 28፣ 29፣ 30 እና 31

5. ለ)82፣ 83፣ 84፣ 85፣ 86፣ 87፣ 88፣ 89፣ 90፣ 91፣ 92፣ 93 እና 94

ሐ) 66፣ 67፣ 68፣ 69፣ 70፣ 71፣ 72፣ 73 እና 74

መ) 9፣ 10፣ 11፣ 12፣ 13፣ 14፣ 15 እና 16

6. ሀ) 11፣ 12፣ 13፣ 14፣ 15　　ለ) 21፣ 22፣ 23፣ 24፣ 25

ሐ) 41፣ 42፣ 43፣ 44፣ 45　　መ) 51፣ 52፣ 53፣ 54፣ 55

7. መልሶቹ እንደሚከተሉት ደምቀው የተፃፉት ናቸው፡፡

ሀ) 18፣16፣**14**፣**12**፣10፣**8**፣**6**፣4።

ለ) 78፣79፣**80**፣**81**፣82፣**83**፣**84**፣**85**።

ሐ) 99፣96፣93፣**90**፣87፣**84**፣**81**።

8. በምሳሌው መሠረት መልሶቹ እንደሚከተሉት ናቸው።

ምሳሌ

61		63	64	61	62	63	64
	44	45	46	43	44	45	46
90			93	90	91	92	93
	56	57		55	56	57	58

9. ቀጥሎ ያሉትን ቁጥሮች በአሃዝ ፃፏቸው።

ሀ) 59 ለ) 85 ሐ) 40 መ) 66

10. መልሶቹ እንደሚከተሉት ናቸው።

ሀ) የአንድ ቤት ለ) የአንድ ቤት ሐ) የአሥር ቤት መ) የአሥር ቤት

ሠ) የአሥር ቤት

ምዕራፍ-6

እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መደመርና መቀነስ (27 ክፍለ ጊዜ)

መግቢያ፡ እስከ 100 ካሉ ሙሉ ቁጥሮች መካከል ባለ አንድ ሆሄ ቁጥር ከባለ ሁለት ሆሄ ቁጥር እንድሁም ባለ ሁለት ሆሄ ቁጥር ከባለ ሁለት ሆሄ ቁጥር ጋር የተለያዩ ዘዴዎች በመጠቀም መደመር እና መቀነስ ይቻላል፡፡ በዚህ ምዕራፍ እነዚህን ዜዴዎች እንመለከታለን፡፡

የትምህርቱ ዓላማዎች

- ድምራቸዉ ከ 100 የማይበልጡ ሁለት ባለ ሁለት ሆሄ ቁጥሮችን ይደምራሉ፡፡
- ባለ አንድ ሆሄ ቁጥርን ወይም ባለ ሁለት ሆሄ ቁጥን ከሚበልጠዉ ከባለ ሁለት ሆሄ ቁጥር ላይ ይቀንሳሉ፡፡
- ቁጥሮችን የመነጣጠልና የመገጣጠም ፅንሰ ሀሳብን በመጠቀም ባለ ሁለት ሆሄ ቁጥሮችን ይደምራሉ ይቀንሳሉ፡፡

6.1 ባለ ሁለት ሆሄ ቁጥር እና ባለ አንድ ሆሄ ቁጥርን ሳይነጣጥሉ መደመርና መቀነስ (4 ክፍለ ጊዜ)

መግቢያ፡- በዚህ ንዑስ ርዕስ ተማሪዎች እስከ 100 ያሉ ቁጥሮችን ተጠቅመው ባለ ሁለት ሆሄ ቁጥር እና ባለ አንድ ሆሄ ቁጥርን ሳይነጣጥሉ መደመርና መቀነስን ይማራሉ፡፡

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኃላ ተማሪዎች፡-

- ባለ አንድ ሆሄ ቁጥርን ከባለ ሁለት ሆሄ ቁጥር ጋር ይደምራሉ፡፡
- ባለ አንድ ሆሄ ቁጥርን ከባለ ሁለት ሆሄ ቁጥር ላይ ይቀንሳሉ፡፡

ዝርዝር ዓላማዎች፡ ከዚህ ንዑስ ርዕስ ትምህርት በኂላ ተማሪዎች፡-

- ባለ ሁለትና ባለ አንድ ሆሄ ቁጥርን ሳይነጣጥሉ ይደምራሉ፡፡
- ባለ ሁለትና ባለ አንድ ሆሄ ቁጥርን ሳይነጣጥሉ ይቀንሳሉ፡፡

ለርዕሱ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች

- የመደመር የቁጥር መሥመር ማዘጋጀት፡፡

- የመቀነስ የቁጥር መሥመር ማዘጋጀት፡፡

የማስተማሪያ ስልቶች

- ተማሪዎች መቁጠርን በቁጥር መስመር ስልት ተጠቅመው ባለ አንድ ሆሄ ቁጥርን ከባለ ሁለት ሆሄ ቁጥር ጋር እንዲደምሩ ማድረግ፡፡

6.1.1 ባለ ሁለት ሆሄ ቁጥርን ከባለ አንድ ሆሄ ቁጥር ጋር አግድም መደመር

ባለሁለት ሆሄ ቁጥርን ከባለ አንድ ሆሄ ቁጥር ጋር አግድም በመፃፍ መደመር ይቻላል፡፡ ይኸውም በመጀመሪያ የአንድ ቤትን ከአንድ ቤት ጋር ይደምራሉ፡፡ በመቀጠልም የአሥር ቤትን ቀጥታ በመፃፍ ዉጤቱን ማስቀመጥ ይችላሉ፡፡

የመልመጃ፡ 1 መልሶች

ተማሪዎች በተሰጠው ምሳሌ መሰረት አግድም በመደመር ውጤቱን ያስቀምጣሉ፡፡

ሀ) 99 ለ) 44 ሐ) 49 መ) 38 ሠ) 29 ረ) 68 ሰ) 19 ሸ) 89

6.1.2 ባለ ሁለት ሆሄ ቁጥርን ከባለ አንድ ሆሄ ቁጥር ጋር ቁልቁል መደመር

ተማሪዎች ባለ ሁለት ሆሄ ቁጥርን ከባለ አንድ ሆሄ ቁጥር ጋር ቁልቁል በመፃፍ መደመር ይቻላሉ፡፡ መጀመሪያ የአንድ ቤትን ከአንድ ቤት ጋር ይደምራሉ፡፡ በመቀጠል የአሥር ቤትን ቀጥታ በማዉረድ ዉጤቱን ማስቀመጥ ይችላሉ፡፡

የመልመጃ፡ 2 መልሶች

ሀ) 89	ለ) 69	ሐ) 39	መ) 99	ሠ) 29
ረ) 99	ሰ) 49	ሸ) 87	ቀ) 75	

6.1.3 ከባለ ሁለት ሆሄ ቁጥር ላይ ባለ አንድ ሆሄ ቁጥርን አግድም መቀነስ

ተማሪዎች ከባለ ሁለት ሆሄ ቁጥር ላይ ባለ አንድ ሆሄ ቁጥርን አግድም በመፃፍ መቀነስ ይችላሉ፡፡ ይኸዉም በመጀመሪያ ከአንድ ቤት ላይ የአንድ ቤትን መቀነስና ከዚያም የአሥር ቤትን ቀጥታ በመፃፍ ዉጤቱን ያስቀምጣሉ፡፡

የመልመጃ፡- 3 መልሶች

ሀ) 85 ለ) 50 ሐ) 44 መ) 60 ሠ) 11 ረ) 51 ሰ) 60 ሸ)73

6.1.4 ከባለ ሁለት ሆሄ ቁጥር ላይ ባለ አንድ ሆሄ ቁጥርን ቁልቁል መቀነስ

ከባለ ሁለት ሆሄ ቁጥር ላይ ባለ አንድ ሆሄ ቁጥርን ቁልቁል በመፃፍ መቀነስ ይችላሉ፡፡ ይኸውም መጀመሪያ ከአንድ ቤት ላይ የአንድ ቤትን ይቀንሳሉ፡፡ ከዚያም የአሥር ቤትን ቀጥታ በማዉረድ ዉጤቱን ማስቀመጥ ይችላሉ፡፡

ምዘና

- የቡድን ሥራ በመስጠት ተማሪዎች ቁጥርን ሳይነጣጥሉ እንዲደምሩና እንዲቀንሱ ማድረግ፡፡
- የተለያዩ ጥያቄዎችን የቤት ሥራ በመስጠት ቁጥርን ሳይነጣጥሉ እንዲደምሩና እንዲቀንሱ ማድረግ፡፡

የመልመጃ፡ 4 መልሶች

ሀ) 17 **ለ)** 82 **ሐ)** 73 **መ)** 91 **ሠ)** 20 **ረ)** 52 **ሰ)** 44 **ሸ)** 81

6.2 ባለ ሁለት ሆሄ ቁጥርና ባለ አንድ ሆሄ ቁጥርን በመነጣጠልና በመገጣጠም መደመርና መቀነስ (5 ክፍለ ጊዜ)

መግቢያ፡- በዚህ ንዑስ ርዕስ ተማሪዎች ባለ ሁለት ሆሄ ቁጥርና ባለ አንድ ሆሄ ቁጥርን በመነጣጠልና በመገጣጠም መደመርና መቀነስን ይለማመዳሉ፡፡

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- ባለ አንድ ሆሄ ቁጥርን ከባለ ሁለት ሆሄ ቁጥር ጋር ይደምራሉ፡፡
- ባለ አንድ ሆሄ ቁጥርን ከባለ ሁለት ሆሄ ቁጥር ላይ ይቀንሳሉ፡፡

ዝርዝር ዓላማዎች፡ ከዚህ ንዑስ ርዕስ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- ባለ ሁለትና ባለ አንድ ሆሄ ቁጥርን በመነጣጠል በመገጣጠም ይደምራሉ፡፡
- ባለ ሁለትና ባለ አንድ ሆሄ ቁጥርን በመነጣጠል በመገጣጠም ይቀንሳሉ፡፡
- የመነጣጠልና የመገጣጠም ፅንሰ ሀሳብን ይገነዘባሉ፡፡

ለርዕሱ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች

- የቁጥር ቤት ሥርዓትን የያዘ ቻርት ማዘጋጀት

የማስተማሪያ ስልቶች

- ተማሪዎች የመደመር የቁጥር ቤት ሥርአት ተጠቅመው እንዲደምሩ ማድረግ፡፡
- የመነጣጠል ዘዴን በመጠቀም ተደጋጋሚ ምሳሌዎችን ተጠቅሞ ማሰራት፡፡

6.2.1 ባለ ሁለት ሆሄ ቁጥርን ከባለ አንድ ሆሄ ቁጥር ጋር በመነጣጠል መደመር

- ተማሪዎች ባለ አንድ ሆሄ እና ባለ ሁለት ሆሄያት ቁጥሮችን የመነጣጠል ዘዴን በመጠቀም መደመር ይችላሉ፡፡ እነዚህን ዘዴዎች በተማሪው መፅሐፍ በተሰጠው ምሳሌ መሠረት ይደምራሉ፡፡

የመልመጃ፡ 5 መልሶች

1. ሀ) 17 ለ) 38 ሐ) 30 መ) 68 ሠ) 89 ረ) 46 ሰ) 97 ሸ) 79 ቀ) 59

6.2.2 ባለ ሁለት ሆሄ ቁጥርን ከባለ አንድ ሆሄ ቁጥር ጋር የቁጥር ቤት ዋጋ ሥርዓትን በመጠቀም መደመር

ተማሪዎች የቁጥር ቤት ሥርዓትን ተጠቅመው ሲደምሩ መጀመሪያ የአንድ ቤትን ከአንድ ቤት ጋር ከደመሩ በኃላ የአሥር ቤትን ቀጥታ በማውረድ ውጤቱን ያገኛሉ፡፡

የመልመጃ፡ 6 መልሶች

ሀ) 19 **ለ)** 27 **ሐ)** 36 **መ)** 78 **ሠ)** 69 **ረ)** 78

6.2.3 ከባለ ሁለት ሆሄያት ቁጥር ላይ ባለ አንድ ሆሄ ቁጥርን ያለ ብድር መቀነስ

ተማሪዎች ከባለ ሁለት ሆሄ ቁጥር ላይ ባለ አንድ ሆሄ ቁጥርን ለመቀነስ የመነጣጠል ዘዴን ይጠቀማሉ፡

የመልመጃ፡ 7 መልሶች

1. 13 2. 47 3. 24 4. 13 5. 82 6. 34 7. 72 8. 92

6.2.4 ከባለ ሁለት ሆሄያት ቁጥር ላይ ባለ አንድ ሆሄ ቁጥርን በብድር መቀነስ

ከባለ ሁለት ሆሄ ቁጥር ባለ እንድ ሆሄ ቁጥርን ለመቀነስ የቁጥር ቤት ሥርዓትን መጠቀም ይችላሉ፡፡

ምዘና

- በቁጥር ቤት ሥርዓት እንዲደምሩና እንዲቀንሱ ጥያቄዎችን በመስጠት መከታተል
- በመነጣጠል እንዲደምሩና እንዲቀንሱ የክፍል ሥራ በመስጠት መከታተል
- የፅሁፍ ፈተና በማዘጋጀት የተማሪዎችን ክህሎት መገምገም

የመልመጃ፡ 8 መልሶች

1. በምሳሌዉ መሥረት መልሶቹ እንደሚከተሉት ይሆናሉ፡፡

ሀ)13	ለ)23	ሐ)32	መ)43	ሠ)43	ረ)13	ሰ)74
ሸ)84	ቀ)9					

2. የቃላት ፕሮብሌም መልሶች

ሀ) 33 የወይራ ችግኞችን + 5 የወይራ ችግኞችን = 38 የወይራ

ችግኞችን ተክለዋል ፡፡

ለ) 46 - 5 = ብር ይቀራታል፡፡ ሐ) 85 + 4 = 89 ብር አውጥተዋል፡፡

መ) 18 ብርቱካናች - 3 ብርቱካኖች - 2 ብርቱካኖች = 13 ብርቱካኖች ይቀሯታል፡፡

6.3 ባለ ሁለት ሆሄ ቁጥሮችን ያለ አለኝታ መደመርና ያለብድር መቀነስ (6 ክፍለ ጊዜ)

መግቢያ፡ በዚህ ንዑስ ርዕስ ተማሪዎች ባለ ሁለት ሆሄ ቁጥሮችን ያለ አለኝታ መደመርና ያለብድር መቀነስን ይለማመዳሉ፡፡

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- ባለ ሁለት ሆሄ ቁጥሮችን ይደምራሉ ይቀንሳሉ፡፡

ዝርዝር ዓላማዎች፡ ከዚህ ንዑስ ርዕስ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- ባለ ሁለት ሆሄ ቁጥሮችን ያለ አለኝታ ይደምራሉ፡፡
- ባለ ሁለት ሆሄ ቁጥሮችን ያለ ብድር ይቀንሳሉ፡፡
- የባለ ሁለት ሆሄ ቁጥሮችን የመደመርና የመቀነስ ዝምድና ይረዳሉ፡፡

ለርዕሱ የሚያስፈልጉ ግባቶች

- የቁጥር ቤት ሥርዓትን የያዘ የመደመርና የመቀነስ ቻርት ማዘጋጀት

የማስተማሪያ ስልቶች

ቁጥርን የመተንተን ፅንሰ ሀሳብን በመጠቀም መደመርና መቀነስን እንዲለማመዱ ማድረግ

ምሳሌ፡- 82 – 6 ማለት 8 ባለ አስር ምድብ እና 2 ባለ አንድ ሲቀንስ 6 ማለት ነው፡፡ በመቀጠል ከ8 ባለ እስር ምድብ ውስጥ አንድ ባለ እስር ምድብ በመዉሰድ ከሁለት ባለ አንድ ምድብ ጋር መደመር ይቻላል፡፡

6.3.1 ባለ ሁለት ሆሄያት ቁጥሮችን ያለ አለኝታ በመነጣጠል መደመር

መልመጃ፡- 9 መልሶች

ሀ) 59 ለ) 65 ሐ) 96 መ) 96 ሠ) 99 ረ) 99 ሰ) 99 ሸ) 79 ቀ) 35 በ) 99

6.3.2 ባለ ሁለት ሆሄያት ቁጥሮችን ያለ አለኝታ የቁጥር ቤት ሥርዓትን በመጠቀም መደመር

የቁጥር ቤት ዋጋ ፅንሰ ሀሳብን በመጠቀም ባለ ሁለት ሆሄያት ቁጥሮችን መደመርን ይለማመዳሉ፡፡

የመልመጃ፡ 10 መልሶች

1.	ሀ)78	ለ)79	ሐ)79	መ)99
	ሠ)99	ረ)78	ሰ)97	ሸ)79
	ቀ)90	በ)39	ተ)96	ቸ)79

6.3.2 ባለ ሁለት ሆሄያት ቁጥርን በቁጥር ቤት ዋጋ ሥርዓት ያለብድር መቀነስ

ባለ ሁለት ሆሄያት ቁጥሮችን ለመቀነስ የቁጥር ቤትን ሥርዓት እንጠቀማለን። ይህን ዘዴ ለማለማመድ የሚከተለዉን ምሳሌ ይጠቀማሉ።

ምዘና፡

- በቁጥር ቤት ሥርዓት እንዲደምሩና እንዲቀንሱ የቡድን ሥራ በመስጠት መከታተል
- በመነጣጠል እንዲደምሩና እንዲቀንሱ የክፍል ሥራ በመስጠት መከታተል
- የፅሁፍ ፈተና በማዘጋጀት ተማሪዎች ያለ አለኝታ የመደመርና ያለብድር የመቀነስ ክህሎታቸውን መገምገም

የመልመጃ፡ 11 **መልሶች**

1.

ሀ) 11	ለ) 12	ሐ) 11	መ) 35	
ሠ) 36	ረ) 21	ሰ) 13	ሸ) 20	ቀ) 61
በ) 11	ተ) 23	ቸ) 31		

2.

ሀ) 46 ፍየሎች - 12 ፍየሎች = 34 ፍየሎች ይቀሩታል።

ለ) 36 ብርቱካኖች - 22 ብርቱካኖች = 14 ብርቱካኖች ይቀሩታል።

6.4 ባለ ሁለት ሆሄያት ቁጥሮችን በአለኝታ መደመርና በብድር መቀነስ (6 ክፍለ ጊዜ)

መግቢያ፡ በዚህ ንዑስ ርዕስ ተማሪዎች ባለ ሁለት ሆሄ ቁጥሮችን በአለኝታ መደመርና በብድር መቀነስን ይለማመዳሉ።

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- ባለ ሁለት ሆሄ ቁጥሮችን የመነጣጠልና የመገጣጠም ፅንሰ ሀሳብ በመጠቀም ይደምራሉ ይቀንሳሉ

ዝርዝር ዓላማዎች፡ ከዚህ ንዑስ ርዕስ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- ባለ ሁለት ሆሄ ቁጥሮችን ከአስር ቤት በመበደር ይደምራሉ፡፡
- ባለ ሁለት ሆሄ ቁጥሮችን ከአስር ቤት በመበደር ይቀንሳሉ፡፡
- በአለኝታ የመደመርና በብድር የመቀነስ ፅንሰ ሀሳብ ይገነዘባሉ፡፡

ለርዕሱ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች

- የመነጣጠልና የመገነጣጠል ፅንሰ ሀሳብን የያዘ የመደመርና የመቀነስ ቻርት ማዘጋጀት

የማስተማሪያ ስልቶች

ቁጥርን የመተንተን ፅንሰ ሀሳብን በመጠቀም መደመርና መቀነስን እንዲለማመዱ ማድረግ

ምሳሌ፡- $82-6$ ማለት 8 ባለ አስር ምድብ እና 2 ባለ አንድ ሲቀንስ 6 ማለት ነው፡፡ በመቀጠል ከ8 ባለ እስር ምድብ ውስጥ አንድ ባለ እስር ምድብ በመዉሰድ ከሁለት ባለ አንድ ምድብ ጋር መደመር፡፡ በዚህ የተነሳ $82 = 70 + 12$ በመጨረሻም $82-6$ ማለት $70+12-6$ ማለት ነው ፡፡ ስለዚህ $82-6 = 70+12-6 = 70+6 = 76$

6.4.1 ሁለት ሆሄያት ቁጥሮችን በመነጣጠል በአለኝታ መደመር

እስከ አሁን ሁለት ሆሄያት ቁጥሮችን ያለ አለኝታ መደመር ተለማምደዋል፡፡ አሁን ደግሞ በአለኝታ መደመርን ይማራሉ፡፡

በሁለት ሆሄያት በአሌኝታ ለመደመር የመነጣጠል የመደመር ዘዴን መጠቀም እንችላለን፡

የመልመጃ፡ 12 መልሶች

*ሀ)*43 **ለ)** 54 *ሐ)* 94 *መ)* 91 *ሠ)* 82 **ረ)** 83 ሰ) 79 ሸ) 94 ቀ) 48

6.4.2 ሁለት ሆሄያት ቁጥሮችን የቁጥር ቤት ዋጋ ሥርዓትን በመጠቀም መደመር

ሀ) $\mathbf{46 + 38 =}$ ____



ለ) $53 + 29 =$ ____



የመልመጃ፡ 13 መልሶች

1) 63	2) 93	3) 97	4) 92	5) 50
6) 80	7) 83	8) 85	9) 66	

6.4.3 ባለ ሁለት ሆሄያት ቁጥሮችን በብድር መቀነስ

1. ከባለ ሁለት ሆሄ ቁጥር ላይ ባለ አንድ ሆሄ ቁጥርን በብድር መቀነስ

ምሳሌ፡-

ሀ) $24 - 6 =$ _______

እዚህ ላይ በቁጥር ቤት ስንቀንስ 4 – 6 ማለት ነዉ፡፡ ይህ ደግሞ አይቻልም፡፡

ተማሪዎች 4 ጠጠሮች ቢኖራቸው እና ከነዚህ ላይ 6 ጠጠሮች ቢያነሱ፡፡ ስንት ጠጠሮች ይቀራቸዋል? በቡድን ሆነው ይወያዩበት፡፡

አይቻልም ካሉ ትክክል ናቸው፡፡ ስለዚህ ከዚህ በታች ያለዉን ምሳሌ ይጠቀማሉ፡፡ ሀ)
$24 - 6 = 20 + 4 - 6$

$= 10 + 10 + 4 - 6$

$= 10 + 14 - 6$ (1 አሥር እና 4 አንዶች 14 አንዶች ይሆናሉ)

$= 10 + 8$

$= 18$

ለ) $96 - 8 = 90 + 6 - 8$

$= 80 + 10 + 6 - 8$

$= 80 + 16 - 8$

$= 80 + 8$

$= 88$

የመልመጃ: 14 መልሶች

1. $28 - 9 = 20 + 8 - 9$

   =10+10+8-9

   =10+18-9

   =10+9=19

2. $25 - 8 = 20 + 5 - 8$

   = 10+10+5-8

   =10+15-8

   =10+7=17

3. $32 - 9 = 30 + 2 - 9$

   =20+10+2-9

   =20+12-9

   =20+3=23

4. $43 - 5 = 40 + 3 - 5$

   = 30+10+3-5

   =30+13-5

   =30+8=38

5. $73 - 5 = 70 + 3 - 5$

   = 60+10+3-5

   =60+13-5

   =60+8=68

6. $80 - 8 = 70 + 10 - 8$

   =70+2=72

2. ከባለ ሁለት ሆሄ ቁጥር ላይ ባለ ሁለት ሆሄ ቁጥርን በብድር መቀነስ

ተማሪዎች ሁለት ሆሄያት ያላቸዉን ቁጥሮች በብድር ለመቀነስ የሚከተሉትን ዘዴ ወይም ስልት መጠቀም ይችላሉ።

ምሳሌ፡- *ሀ)* **43 – 29** = ___

43 $\underline{-29}$	*መጀመሪያ የአንድን ቤት ተመልከቱ።* $3 < 9$ ስለዚህ ከ3 ላይ 9ን

14	መቀነስ አይቻልም። ከ 43 ቁጥር ላይ ከአሥር ቤት አንድ እንበደርና ወደ 10 አንዶች እናሳልፋለን። $43 = 40 + 3 = 30 + 10 + 3 = 30 + 13$ $13 - 9 = 4$ ስለዚህ 4 አንዶችን እናገኛለን። 1 አሥር ስለተበደርን 3 አሥሮች ይቀሩናል። $3 - 2 = 1$ በአሥር ቤት እንፅፋለን።

የመልመጃ፡ 15 መልሶች

በምሳሌው መሰረት መልሶቹ እንደሚከተሉት ናቸው።

ሀ) 4	ለ) 56	ሐ) 47	መ) 9	ሠ) 4
ረ) 8	ሰ) 16	ሸ) 58	ቀ) 8	

ማስታወሻ፡ ተማሪዎች ሁለት ቁጥሮችን ሲያቀናንሱ ትክክል መሆናቸውን ለማረጋገጥ ተቀናሽ እና ልዩነትን ይደምራሉ። ለዚህም ቀጥሎ ያሉትን ምሳሌ በትኩረት ይመለከታሉ።

ምሳሌ፡ ሀ) $94 - 37 = 57$ ምክንያቱም $57 + 37 = 94$

ለ) $27 - 18 = 9$ ምክንያቱም $9 + 18 = 27$

ሐ) $75 - 37 = 38$ ምክንያቱም $38 + 37 = 65$

ምዘና

- የክፍል ሥራ በመስጠት ተማሪዎች በአለኝታ መደመርና በብድር መቀነስ መቻላቸውን መከታተል ያስፈልጋል
- የፅሁፍ ፈተና በማዘጋጀት የተማሪዎችን ክህሎት መገምገም ያስፈልጋል

የመልመጃ፡ 16 መልሶች

1) $53 - 17 = 36$ ምክንያቱም $17 + 36 = 53$
2) $42 - 16 = 26$ ምክንያቱም $16 + 26 = 42$
3) $75 - 26 = 49$ ምክንያቱም $26 + 49 = 75$
4) $34 - 17 = 17$ ምክንያቱም $17 + 17 = 34$
5) $91 - 73 = 18$ ምክንያቱም $73 + 18 = 91$

6) $41 - 18 = 23$ ምክንያቱም $18 + 23 = 41$

6.5 የቃላት ፕሮብሌሞችን መደመርና መቀነስን በመጠቀም ማስላት (6 ክፍለ ጊዜ)

መግቢያ፡ በዚህ ንዑስ ርዕስ ተማሪዎች የባለ አንድ ሆሄ ቁጥሮችንና ባለ ሁለት ሆሄ ቁጥሮችን የቃላት ፕሮብሌሞች መደመርና መቀነስን በመጠቀም ያሰላሉ፡፡

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- ድምራቸዉ ወይም የመቀነስ ዉጤታቸዉ ከ 100 የማይበልጡ የቃላት ፕሮብሌሞችን ይሰራሉ

የትምህርቱ ዓላማዎች፡ ከዚህ ክፍል ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡

- የቃላት ፕሮብሌሞችን መደመርን በመጠቀም ያሰላሉ፡፡
- የቃላት ፕሮብሌሞችን መቀነስን በመጠቀም ያሰላሉ፡፡
- የቃላት ፕሮብሌሞችን ወደ ቁጥር በመቀየር ያሰላሉ፡፡

ለርዕሱ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች

- የመነጣጠልና የመገነጣጠል ፅንሰ ሀሳብን የያዘ የመደመርና የመቀነስ ቻርት ማዘጋጀት

የማስተማሪያ ስልቶች

- ተማሪዎች የቁጥር መስመር ስልት ተጠቅመው የቃላት ፕሮብሌሞችን እንዲያሰሉ ማድረግ፡፡
- ተማሪዎች የመደመር የቁጥር ቤት ሥርዓት ተጠቅመው የቃላት ፕሮብሌሞችን እንዲሰሩ ማድረግ፡፡

ማብራሪያ

ከዚህ በታች እስከ 100 ላሉ ቁጥሮች በውስጡ መደመርንና እና መቀነስን የያዘ የተለያዩ የቃላት ፕሮብሌሞችን በመረዳት ይሰራሉ፡፡

የመልመጃ፡ 17 መልሶች

1) 76 ብርቱካኖችን ላይ 28 ብርቱካኖችን መቀነስ።

$76 - 28 = 48$ ብርቱካኖችን ይቀራሉ።

2) የስኳሩንና የጨውን ብር መደመር።

$65 + 20 = 85$ ብር ሸጠዋል።

3) አብደላ ባለው ብር ላይ የአባቱንና የወንድሙን መደመር።

$63 + 17 + 16 = 96$ ብር ይኖረዋል።

4) ከ 1ኛ እስከ 4ኛ ያሉትን የተማሪዎች ብዛት መደመር።

ስለሆነም $25 + 37 + 23 + 14 = 99$ ተማሪዎች አሉ።

5) ሀ) ሀብታሙና ሙሉቀን የተከሉትን የችግኝ ብዛት መደመር።

ስለሆነም $38 + 47 = 85$ ችግኞችን ተክለዋል።

ለ) ሙሉቀንና ውብሸት የተከሉትን የችግኝ ብዛት መደመር።

ስለሆነም $47 + 29 = 76$ ችግኞችን ተክለዋል።

ሐ) ሀብታሙና ውብሸት የተከሉትን የችግኝ ብዛት መደመር።

ስለሆነም $38 + 29 = 67$ ችግኞችን ተክለዋል።

መ) ሙሉቀን ከተከለው የችግኝ ብዛት ላይ የሀብታሙን መቀነስ።

$47 - 29 = 18$ ስለዚህ ሙሉቀን የተከለው ችግኝ ሀብታሙ ከተከለው ችግኝ በ18 ያክል ይበልጣል።

ሠ) መፍትሄ፡ ሀብታሙ ከተከለው የችግኝ ብዛት ላይ የውብሸትን

መቀነስ። $38 - 29 = 8$ ስለዚህ ሀብታሙ የተከለው ችግኝ ውብሸት

ከተከለው ችግኝ በ8 ያክል ይበልጣል።

ምዕራፍ-7

ቅርፆች (16 ክፍለ ጊዜ)

መግቢያ: ባለ ሁለት አውታር ምስሎችን መለየት እንድሁም በማንኛውም ጠለል ላይ ምስላቸውን መሳል፡፡ የታወቁ ባለ ሁለት አውታር ምስሎች የባህሪይ መለያን በራስ ቋንቋ መግለጽን እና በአካባቢ ስም መጥራት በዚህ ምዕራፍ ይመለከታሉ፡፡

የትምህርቱ ዓላማዎች: ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- ባለ ሁለት አዉታር ምስሎችን ግማሽ ክብ፣ዲያመንድ፣ሞላላ፣አምስት ጎን እና ስድስት ጎንን በስም ይለያሉ፡፡
- የባለ ሁለት አዉታር ምስሎች የባህሪ መለያን በራሳቸዉ ቋንቋ ይገልፃሉ፡፡

ተፈላጊ ብቃት: ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- ባለ ሁለት አዉታር ምስሎችን በስም ይለያሉ፡፡
  ምሳሌ፡- ግማሽ ክብ፣ ዲያመንድ፣ ሞላላ፣ አምስት ጎን እና ስድስት ጎን
- የባለ ሁለት አዉታር ምስሎችን የባህሪ መለያን በራሳቸዉ ቋንቋ ይገልፃሉ
- ጎን እና አንግልን በመጠቀም ቅርፆችን ይገልፃሉ፡፡

የቡድን ሥራ-1 መልስ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድን ከተወያዩ በኃላ የተስማሙበትን ሐሳብ ለመምህራቸው ያሳያሉ፡፡

1. ከቡድን ውይይት በኋላ ቀጥሎ የሚከተሉት መልሶች ይጠበቃሉ፡፡

ሀ. 

ለ.

ሐ. 

ሀ. የሒሳብ መጽሐፋችሁ ቅርፅ በ "ለ" ላይ የተጠቀሰውን ምስል ይመስላል፡፡

ለ. የክፍላችሁ ወለል ጠርዝስ ቅርፅ በ"ለ" ላይ የተጠቀሰውን ምስል ይመስላል፡፡

7.1 ባለሁለት አዉታር ምስሎችን መለየት (4 ክፍለ ጊዜ)

መግቢያ፡ ባለ ሁለት አውታር ምስሎች ጠለል ላይ መስመሮችን በመጠቀም የሚሳሉ ቅርፆች ሲሆኑ ከዚህ እንደሚከተለው ተገልጸዋል፡፡

ዝርዝር ዓላማዎች፡ ከዚህ ንዑስ ርዕስ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- ባለ ሁለት አውታር ምስሎችን ለይተው ይናገራሉ፡፡
- ባለ ሁለት አውታር ምስሎችን ይዘረዝራሉ፡፡

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኃላ ተማሪዎች፡-

- ባለ ሁለት አዉታር ምስሎችን በስም ይለያሉ፡፡

ለርዕሱ የሚያስፈልጉ ግበዓቶች

- የካሬ፣ የሬክታንግል፣ የክብ፣ የጎነ ሦስት ሞዴሎች

የማስተማሪያ ስልቶች፡ ለተማሪዎች የተለያዩ ባለሁለት አዉታር ምስሎችን ግማሽ ክብ ፣ሞላላ ክብ፣ዲያመንድ ፣ባለ አምስት ጎን እና ስድስት ጎን በመርጃ መሣሪያ በማስደገፍ ማቅረብ፡፡ ተማሪዎች በራሳቸዉ ቋንቋ የምስሎችን ስያሜ እና አይነት እንዲለዩ ማድረግ፡፡

የተግባር-1 መልሶች

1. ከሚከተሉት ምስሎች የትኞቹ ጎነ ሦስት ፣ የትኞቹ ጎነ አራት እና የትኞቹ ደግሞ ክብ እንደሆኑ ለይታችሁ ተናገሩ

ሀ) ጎነ አራት **ለ)** ክብ **ሐ)** ጎነ ሦስት **መ)** ጎነ አራት

ሠ) ጎነ ሦስት **ረ)** ጎነ አራት **ሰ)**ጎነ አራት

ተማሪዎች ከላይ ከተጠቀሱትን ምሥሎች ጋር የሚመሳሰል እንዲጠቅሱ መመህሩ ያበረታታል፡፡

ከዚህ በታች ባለ ሁለት አውታር ምስሎች ከነስያሜያቸው ቀርበዋል ተማሪዎች በትኩረት እንዲመለከቱና እንዲያጠኑ መምህሩ የራሱን ድጋፍ ያደርጋል፡፡

ሀ.  ጎነ ሶስት

ለ. ጎነ አራት

ሐ.  ጎነ አምስት

መ.  ጎነ ስድስት

ሠ.  ክብ

ረ. ሞላላ

ሰ  ድያመንድ

የመልመጃ -1 መልስ

1. በስተግራ ለተገለጹት ስሞች ተመሳሳይ የሆነውን ቅርፅ ማቅለም፡፡

ክብ				
ሬክታንግል				
ካሬ				

ድያመንድ	
ኮከብ	
ጎነ ሦስት	
ሞላላ	

2. ተመሳሳይ ምስሎች ማዛመድ



7.2 ባለሁለት አዉታር ምስሎችን መሳል (6 ክፍለ ጊዜ)

መግቢያ፡ የሚከተሉትን ምስሎች በምሳሌዉ መሠረት በተሰጠዉ ባዶ ቦታ ደጋግመው እንዲስሉ መምህሩ ድጋፍ ያደርጋል፡፡

ዝርዝር ዓላማዎች፡ ከዚህ ንዑስ ርዕስ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- ባለ ሁለት አውታር ምስሎችን ቅርፅ ይለያሉ፡፡
- ባለ ሁለት አውታር ምስሎችን ይስላሉ፡፡

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኃላ ተማሪዎች፡-

- ባለ ሁለት አዉታር ምስሎችን በስም ይለያሉ፡፡

ለርዕሱ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች

- ማሥመሪያ፣ የማንቲም ዲናር፣ ወረቀት የመሳሰሉት

የማስተማሪያ ስልቶች

- ከዚህ በታች የተገለፁትን ምስሎች ለተማሪዎች በጥቁር ሠሌዳ በመሣል ማሳየት ፡፡ተማሪዎች ከተሳሉት ምስሎች ዉስጥ በመስመር ብቻ የሚሳሉትን ለይቶ እንዲስሉ መጠየቅ፡፡



- ከዚህ በታች የተገለፁትን መሰል ጥያቄዎች ለተማሪዎች በማቅርብ ተማሪዎች ጎነ አራት እና ክብ እንዲሰሩ መደገፍ፡፡ **ለምሳሌ፡-** “አስቴር ዛሬ ጠዋት ምስል ተመለከተች ምስሉም ልክ የሳይክል ጎማ ወይም ሃምሳ ሳንቲም ይመስላል ተማሪዎች አስቴር የተመለከተችዉ ምስል ቅርፅ ምን ይባላል?“

ማብራሪያ



ከዚህ በታች የጠሰጡትን ምስሎች ተማሪዎች በቀለም የቀባሉ፡፡



የመልመጃ -2 መልስ

1. በደብተራችሁ ላይ ሁለት የጎነ ሦስት ምስሎችን ፣ ሁለት የጎነ አራት ምስሎችን እና ሁለት የክብ ምስሎችን በመሳል ለመምህራቸው ያሳያሉ፡፡
2. ምሰሉ እንደሚከተለው ተቀብቷል፡፡



3. ነጠብጣቦችን በማያያዝ ያደምቃሉ



7.3 ምስሎችን በስም መዘርዘር(6 ክፍለ ጊዜ)

መግቢያ፡ የባለ ሁለት አዉታር ምስሎችና ስሞቻቸዉ እንድሁም የባህሪይ መለያቸው እንደሚከተለው ተገልፃል፡፡

ዝርዝር ዓላማዎች፡ ከዚህ ንዑስ ርዕስ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- ባለ ሁለት አዉታር ምስሎች በስም ይለያሉ፡፡
- ባለ ሁለት አዉታር ምስሎች በስም ይዘረዝራሉ፡፡

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኃላ ተማሪዎች፡-

- የባለ ሁለት አዉታር ምስሎችን የባህሪ መለያን በራሳቸዉ ቋንቋ ይገልፃሉ

የባለ ሁለት አዉታር ምስሎችና ስሞቻቸዉ

ምስሎች	ስም
	ካሬ
	ሬክታንግል
	ጎነ አምስት
	ጎነ ስድስት
	ዳይመንድ
	ሞላላ

የመልመጃ -3 መልሶች

1. በስተቀኝ በኩል ያሉትን ቁሶች ከተመሳሳይ በስተግራ ካሉ ቅርጻቸው ጋር አዛምዱ፡፡

ሀ. ክብ ከ ሰዓት ለ. ካሬ ከ ፎቶ ማስቀመጫ

ሐ. ጎነ ሦስት ከ ልብስ ማንጠልጠያ መ. ሬክታንግል ከ ማስመሪያ

2. የሚከተሉትን ምስሎች ስም ይጠራሉ።ካሬ፣ ሬክታንግ፣ ጎነ ሦስት እና ክብ።





3. ነጠብጣቦችን በማያያዝ የሚያገኙትን ምስል በስም ይገልፃሉ

ሀ.



ጎነ ሦስት

ለ.



ክብ

ሐ.



ካሬ

መ.



ድያመንድ

ሠ. 

ጎነ አምስት

ረ. 

ጎነ ስድስት

1.3.1 ሬክታንግል

ሬክታንግል አራት ጎኖች አሉት፡፡ ሁለት ጥንድ ተቃራኒ ጎኖቹ እኩል ናቸው፡፡ ለምሳሌ ቀጥሎ ያለውን ምስል ሬክታንግል ይባላል፡፡



ከላይ ያለው ሬክታንግል ሀለሐመ በመባል ይጠራል፡፡

ጎነ ሶስት ሶስት ጎኖች አሉት፡፡ ከዚህ በታች ያለው ምስል ጎነ ሶስት ይባላል፡፡ ጎነ ሶስት ሀለሐ ተብሎ ይጠራል፡፡ ይህን በምልክት ስንጽፍ ∆ሀለሐ ይሆናል፡፡



1.3.2 ካሬ

ካሬ አራት ጎኖች አሉት የሁሉም ጎኖች ርዝመት እኩል ነው፡፡



ካሬውም ሲጠራ ካሬ ሀለሐመ ይባላል፡፡

1.3.3 ክብ

ቀጥሎ የተገለጸው ምስል ክብ ይባላል፡፡



መ የክብ እምብርት ይባላል፡፡ ይህ ክብ ሲጠራ ክብ መ ይባላል፡፡

የመልመጃ -4 መልሶች

1. ለ 2. ሀ

የማጠቃለያ መልመጃ

1. የሒሳብ መፅሐፋቸው የሬክታንግል ቅርፅ አለው፡፡
2. የክፍላቸው ወለል ጎነ አራት ቅርፅ አለው፡፡
3. ከ ሀ እስከ ለ የጠሰጡትን ምስሎች ወረቀት በመጠቀም አሰመስለው ቆርጠው እንዲያመጡ መምህሩ እገዛ ያደርጋል፡፡
4. ከሚከተሉት ምስሎች መካከል የትኞቹ ጎነ ሦስት የትኞቹ ጎነ አራት እና የትኞቹ ክብ እንደሆኑ ለዩ፡፡

   ሀ) ክብ **ለ)** ጎነ አራት **ሐ)** ጎነ ሦስት **መ)** ጎነ ሦስት **ሠ)** ጎነ አራት **ረ)** ጎነ አራት **ሰ)** ጎነ ሦስት **ሸ)** ጎነ ሦስት **ቀ)** ክብ

5. ነጠብጣቦችን በማያያዝ የምስሉን ስም ይገልፃሉ፡፡

   ሀ. ካሬ ለ. ጎነ ሦስት ሐ. ክብ መ. ሬክታንግል
   ሠ. ጎነ ሦስት ረ. ጎነ ሦስት

6. በግራ በኩል ያሉትን ቅርፆች በቀኝ በኩል ካሉት የቅርፆች ስም ጋር አዛምዱ፡፡

   ሀ. ክብ ለ. ጎነ ሦስት ሐ. ሬክታንግል
   መ. ጎነ አምስት ሠ. ጎነ ስድስት ረ. ሞላላ

ምዕራፍ-8

ሥርዓተ ጥለት (16 ክፍለ ጊዜ)

መግቢያ፡ የቁጥሮችንና የቅርፃ ቅርፆችን ቀላል ድርድር ወይም ደጋግሞ መጣል፣ ደጋግሞ መጣልን ማስቀጠል እንድሁም አምሳያ ደጋግሞ መጣል በዚህ ምዕራፍ እንመለከታለን፡፡

የትምህርቱ ዓላማዎች፡ ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኂላ ተማሪዎች፡-

- ተደጋጋሚ ሥርዓተ ጥለቶችን ለይተዉ ይረዳሉ፡፡
- ቀላል ተደጋጋሚ ጥለቶችን ይመሰርታሉ፡፡

ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኃላ ተማሪዎች፡-

- ተደጋጋሚ ጥለቶችን ለይተዉ ከተረዱ በኃላ አምሳያቸዉን ከሁለት በላይ መድገም
- ተደጋጋሚ ጥለቶችን ለይተዉ ተረድተዉ ተከታይ ዋጋቸዉን ያስቀጥላሉ
- ቀላል ተደጋጋሚ ጥለቶችን ይመሰርታሉ

8.1 ደጋግሞ መጣል (4 ክፍለ ጊዜ)

መግቢያ፡ የቁጥሮችንና የቅርፃ ቅርፆችን ቀላል ድርድር እንደ አጀማመራቸው በመመልከት መደርደር ይችላሉ፡፡

ዝርዝር ዓላማዎች፡ ከዚህ ንዑስ ርዕስ ትምህርት በኂላ ተማሪዎች

- ምስሎችን ደጋግመው ይጥላሉ፡፡
- ጥለቶቹን በማየት ቀጥሎ የሚመጡትን ጥለቶች ይጥላሉ፡፡

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኃላ ተማሪዎች፡-

- ተደጋጋሚ ጥለቶችን ለይተዉ ከተረዱ በኃላ አምሳያቸዉን ከሁለት በላይ ይደግማሉ

የተግባር-1 መልሶች

ሀ) 

ለ)

የመልመጃ-1፡ መልሶች

ሀ) 

ለ) 

ሐ 

የመልመጃ -2፡ መልሶች

ሀ 

ለ



8.2 ተደጋጋሚ ሥርዓተ ጥለትን ማስቀጠል (5 ክፍለ ጊዜ)

መግቢያ፡ የቁጥሮችንና የቅርፃ ቅርጾችን ቀላል ድርድርን በመመልከት ተከታታይ የድርድር ዋጋዎችን ማግኘት ወይም የጎደሉ የድርድር ዋጋዎችን መስራት ይቻላል። የሚከተሉትን ተግባራት እና አስረጅዎች ተመልከቱ።

ዝርዝር ዓላማዎች፡ ከዚህ ንዑስ ርዕስ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- ሥርዓተ ጥለትን ይረዳሉ።

- ሥርዓተ ጥለትን ያስቀጥላሉ፡፡

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኃላ ተማሪዎች፡-

- ተደጋጋሚ ጥለቶችን ለይተዉ ተረድተዉ ተከታይ ዋጋቸዉን ያስቀጥላሉ

የተግባር -2፡ መልሶች

መልሶቹ እንደሚከተሉት ይሆናሉ፡፡

ሀ)

ለ)

የመልመጃ -3፡ መልሶች

በምሳሌው መሰረት መልሶቹ እነደሚከተሉት ናቸው፡፡

ሀ	
ለ	
ሐ	

8.3 ሥርዓተ ጥለትን መመሥረት (7 ክፍለ ጊዜ)

ዝርዝር ዓላማዎች፡ ከዚህ ንዑስ ርዕስ ትምህርት በኂላ ተማሪዎች፡-

- ተደጋጋሚ ሥርዓተ ጥለቶችን ይመሰርታሉ፡፡
- አምሳያን ደጋግመው መጣል ይረዳሉ፡፡

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኃላ ተማሪዎች

- ቀላል ተደጋጋሚ ጥለቶችን ይመሰርታሉ

የተግባር -3፡ መልሶች

ተከትሎ የሚመጣው ቅርፅ ይህ ነው።

የመልመጃ -4፡ መልሶች

1.ሀ)



ለ)

ሐ)



መ)



2.

2	4	6	8	10	12	14
4	8	12	16	20	24	28
5	10	15	20	25	30	35
3	6	9	12	15	18	21

የማጠቃለያ መልመጃ መልሶች

1. ሀ)



2. የቅርፆችን ምስል በማየት በተዘጋጀው ባዶ ቦታ ላይ ደግማቹ ሳሉ

ሀ.

ለ.

3. የሚከተሉትን ሥርዓተ ጥለት ደጋማችሁሞ በመጣል በማስቀጠል ባዶ ቦታውን ሙሉ

ሀ)



ለ)



4. የሚከተሉትን ደጋግሞ የተጣሉትን ምስሎች በመመልከት የጎደለውን ምስል አሟሉ

ሀ



ለ



ምዕራፍ-9

የርዝመት፤የክብደትና የይዘት መለኪያ (25 ክፍለ ጊዜ)

መግቢያ፡ በተለያዩ አካባቢዎች ሰዎች ርዝመትን፣ ክብደትንና መጠንን ለመለካት ልማዳዊ መሥፈሪያዎችን ይጠቀማሉ፡፡ በልማዳዊና ሣይንሳዊ መሣሪያዎችን በመጠቀም የቁሶችን ርዝመት፣ ክብደትና ይዘት መለካት ይችላሉ፡፡

የትምህርቱ ዓላማዎች

- ርዝመትን፤ ክብደትንና ይዘትን በኢትዮጲያ ልማዳዊ መለኪያዎች ይለካሉ፡፡
- በርዝመት፤ በክብደትና በይዘት መለኪያዎች ልኬቶችን ያነፃፅራሉ፡፡

9.1 የኢትዮጲያ ልማዳዊ የርዝመት መለኪያ (3 ክፍለ ጊዜ)

መግቢያ፡ በዚህ ንዑስ ርዕስ ተማሪዎች ሰዎች በአካባቢያቸው የሚጠቀሟቸውን የተለያዩ የርዝመት መለኪያዎችን ለይተው ማወቅና እነዚያን ልማዳዊ የርዝመት መለኪያዎች በመጠቀም ርዝመትን መለካት ይማራሉ፡፡

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት

ከዚህ ትምህርት በኃላ ተማሪዎች፡-

- ርዝመትን በኢትዮጲያ ልማዳዊ የርዝመት መለኪያ በመጠቀም ይለካሉ፡፡

  ዝርዝር ዓላማዎች

  ከዚህ ንዑስ ርዕስ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- የኢትዮጲያ ልማዳዊ የርዝመት መለኪያን ይገልፃሉ፡፡
- የኢትዮጲያ ልማዳዊ የርዝመት መለኪያን ይዘረዝራሉ፡፡
- በኢትዮጲያ ልማዳዊ የርዝመት መለኪያ ርዝመትን ይሰፍራሉ፡፡

ለርዕሱ የሚያስፈልጉ ግብአቶች

- በእርምጃቸው እንዲለኩ ማድረግ፡፡
- በስንዝራቸው ርዝመትን እንዲለኩ ማድረግ፡፡

- በክንዳቸው ርዝመትን እንዲለኩ ማድረግ፡፡
- በጫማቸው ርዝመትን እንዲለኩ ማድረግ፡፡

የማስተማሪያ ስልቶች

- ተማሪዎች የኢትዮጵያን ልማዳዊ የርዝመት መለኪያዎችን ስንዝር፣ ጫማ፣ ክንድ እና እርምጃን በመጠቀም በአከበቢያቸው ያሉት ነገሮች ማለትም መማሪያ መፅሐፍ፣ ጠረጴዛ፣ የመማሪያ ክፍል የጎን ስፋት እና የጥቁር ሰሌዳን እንዲለኩ በማድረግ ስለ ልማዳዊ የርዝመት መለኪያ ግንዛቤ እንዲኖራችው ማድረግ፡፡

ማብራሪያ፡ በአንድ አንድ አካባቢዎች ሰዎች ርዝመትን ለመለካት ልማዳዊ የርዝመት መለኪያዎችን ይጠቀማሉ፡፡ ልማዳዊ የርዝመት መለኪያዎች እንደየአካባቢው የተለያዩ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

የተግባር፡ 1 መልሶች

1. በቡድን ሆነው ልማዳዊ የርዝመት መለኪያን ጠይቀው እንዲመጡ ማድረግ፡፡ በተጨማሪም መምህሩ ልማዳዊ የርዝመት መለኪያዎችን ስንዝር፣ እርምጃ፣ ክንድ የመሳሰሉትን ያብራራል፡፡
2. ርዝመትን የምንለካው የቁሶችን ወይም ርቀትን አጭር ወይም ረዥም ለማለት እንዲያስችለን ነው፡፡

- በተለያዩ አካባቢዎች ሰዎች ርዝመትን ለመለካት ከሚጠቀሟቸው ልማዳዊ የርዝመት መለኪያዎች ጥቂቶቹ ስንዝር፣ እርምጃ፣ ክንድ፣ ጫማ፣ ገመድ ወዘተ የመሳሰሉት ናቸው፡፡ እነዚህን ልማዳዊ የርዝመት መለኪያዎች ተጠቅመው ከሣይንሳዊ የርዝመት መለኪያ ጋር ተቀራራቢ የሆነ ግምት ያስቀምጣሉ፡፡

ምዘና

- ተማሪዎች የተሰጣቸዉን ቁስ እንዴት በትክክል መለካት እንደሚችሉ መመልከትና መገምገም
- መምህሩ የተለያዩ ጥያቄዎችን በመስጠት ተማሪዎች ስንዝር፣ እርምጃ፣ ክንድ እና ጫማን ተጠቅመው ርዝመትን የመለካት ክህሎታቸውን እንዲያዳብሩ መከታተል፡፡

የመልመጃ፡ 1 መልሶች

1. ተማሪዎች የተቀመጡበትን ዴስክ በክንዳቸው እንዲለኩ እገዛ ማድረግና ማብራሪያ መስጠት፡፡
2. ተማሪዎች የክፍላችሁን ወለል ከጫፍ እስከ ጫፍ በእርምጃቸው

    እንዲለኩ እገዛ ማድረግና ማብራሪያ መስጠት፡፡

3. የሒሳብ መፅሐፋቸውንና የሒሳብ ደብተራቸውን እንዲለኩ እገዛ ማድረግና

አጭሩንና ረዥሙን ለይቶ ለተማሪዎች ማስረዳት፡፡

9.2 ርዝመትን ማነፃፀር (4 ክፍለ ጊዜ)

መግቢያ፡ የቁሶችን ርዝመት በልማዳዊ የርዝመት መለኪያ ወይም በሣይንሳዊ የርዝመት መለኪያ ሣንቲ ሜትር እና ሜትርን በመጠቀም አጭርና ረዥም በማለት ርዝመትን ያነፃፅራሉ፡፡

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኃላ ተማሪዎች

- ሣይንሳዊ የርዝመት፤ የክብደትና የመጠን መለኪያን በመጠቀም ርዝመትን፤ ክብደትንና መጠንን መለካት ይችላሉ፤
- የተለያ ቁሳቁሶችን ርዝመት ያነፃፅራሉ፡፡

ዝርዝር ዓላማዎች፡ ከዚህ ንዑስ ርዕስ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- በኢትዮጲያ ልማዳዊ የርዝመት መለኪያ ርዝመትን ያነፃፅራሉ፡፡
- በኢትዮጲያ ሣይንሳዊ የርዝመት መለኪያ ርዝመትን ያነፃፅራሉ፡፡
- ቁሶችን ወይም ርቀትን አጭር ወይም ረዥም በማለት ይለያሉ፡፡

ለርዕሱ የሚያስፈልጉ ግብአቶች

- ሳይንሳዊ የርዝመት መለኪያ በማቅረብ እንዲለኩ ማድረግ፡፡
- በስንዝራቸው ደብተራቸውን፣እስክሪብቷቸውን በመለካት እንዲያነፃፅሩ ማድረግ፡፡
- በእርምጃቸው የክፍላቸውን ርዝመት እንዲለኩ ማድረግ፡፡

የማስተማሪያ ስልቶች

- ለተማሪዎች በአቅራቢያቸው የሚገኙትን ቁሳቁስ በማቅረብ ተማሪዎች ርዝመታቸውን በመለካት እንዲያነፃፅሩ ማበረታታት በዚህ የተነሳ አንፃራዊ የዝርመት መግለጫዎች አጭር፣ረጅም የሚሉትን ማስረዳት ፡፡
- ለተማሪዎች በሳንቲ ሜትር የተከፋፈለ ማስመሪያ እና ሜትር በማቅረብ ተማሪዎች ሳንቲ ሜትር እና ሜትርን በንፅፅር እንዲገልፁ ማድረግ፡፡ ከተማሪው ሀሳብ በመነሳት በሳንቲ ሜትር እና በሜትር መካከል ያለውን ቁርኝት ለተማሪዎች በመግለፅ በምሳሌ ማስረዳት፡፡

ማብራሪያ

የተግባር፡ 2 መልሶች

1. የደብተራቸውንና የእስኪሪብቷቸውን ርዝመት በስንዝራችሁ ለክተው እንዲያነፃፅሩ ማድረግ፡፡
2. ከአምስቱ የእጃቸው ጣቶች መካከል ረዥሙንና አጭሩን ለይተው እንዲናገሩ ማድረግ፡፡
3. የ“ሀ” መሥመር ረዥም ሲሆን የ“**ለ**” **ደግሞ** አጭር ነው፡፡

9.2.1 ርዝመትን በሣንቲ ሜትርና በሜትር መለካት

ሣይንሳዊ የርዝመት መለኪያዎችን በመጠቀም ርዝመትን መለካት እንችላለን፡፡ ሣይንሳዊ የርዝመት መለኪያ አሃድ የምንላቸዉ ሜትር፣ ሣንቲ ሜትር የመሳሰሉት ናቸዉ፡፡
ከዚህ በታች የምትመለከቱት ባለ አንድ ሜትር ማስመሪያ ወይም 100 ሣንቲ ሜትር ማስመሪያ ነው፡፡



ምሳሌ፡- ማስመሪያውን በመጠቀም የጠረጴዛውን ርዝመት መለካት ትችላለችሁ፡፡

ስለዚህ ከላይ ከሥዕሉ እንደምትረዱት የጠረጴዛዉ ርዝመት 80 ሣንቲ ሜትር ነው፡፡

ማስታወሻ

1. ሜትርና ሣንቲ ሜትር መካከለኛ እና አጫጭር ርቀትን ወይም ርዝመትን ለመለካት የምንገለገልባቸው ምድቦች ናቸው፡፡
2. ሜትር በአጭሩ ሲፃፍ **ሜ** ሲሆን ሣንቲ ሜትር ደግሞ **ሣ.ሜ** ብለን በመፃፍ መግለፅ እንችላለን ፡፡
3. 1 ሜትር ከ100 ሣንቲ ሜትር ጋር እኩል ነዉ፡፡

ስለዚህ ተማሪዎች ተመሳሳይ አሃድ ያላቸውን ምድቦች መደመርና መቀነስ ይማራሉ፡፡

ምዘና

- መምህሩ የተለየዩ ቁሶችን ርዝመት በመስጠት የርዝመት መለኪያ ሜትር፣ ሣንቲ ሜትርና እንዲሁም ልማዳዊ የርዝመት መለኪያን ተጠቅመው ርዝመትን ማነፃፀር መቻላቸዉን ማረጋገጥ፡፡

የመልመጃ፡ 2 መልሶች

1. **100ሣ.ሜ** 2. **30ሣ.ሜ** 3. **10ሜ** 4. **3ሜ**

9.3 የኢትዮጲያ ልማዳዊ የክብደት መለኪያ(4 ክፍለ ጊዜ)

መግቢያ፡ ልማዳዊ የክብደት መለኪያ መሣሪያዎችን በመጠቀም የተለያዩ

ቁሶችን ክብደት መለካት ይማራሉ፡፡

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኃላ ተማሪዎች፡-

- ክብደትን በኢትዮጲያ ልማዳዊ የክብደት መለኪያ በመጠቀም ይለካሉ፡፡

ዝርዝር ዓላማዎች፡ ከዚህ ንዑስ ርዕስ ትምህርት በኂላ ተማሪዎች፡-

- የኢትዮጲያ ልማዳዊ የክብደት መለኪያን ይናገራሉ፡፡
- የኢትዮጲያ ልማዳዊ የክብደት መለኪያን ይዘረዝራሉ፡፡
- በኢትዮጲያ ልማዳዊ የክብደት መለኪያ ክብደትን ይሰፍራሉ፡፡

ለርዕሱ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች

- ባህላዊ የክብደት መለኪያ ሚዛን በማዘጋጀት ማሳየት፡፡
- እጆቻቸውን ተጠቅመው እንዲያመዛዝኑ ማበረታታት፡፡

የማስተማሪያ ስልቶች

- ተማሪዎችን በመኖሪያ ቤት፣ በአካባቢያቸው እንዲሁም በገበያ እና በሱቅ ውስጥ ክብደትን እንዴት እንደሚለኩ እንዲናገሩ ማበረታታት፡፡ ከተማሪዎች ምላሽ በመነሳት ስለ ኢትዮጵያ ልማዳዊ የክብደት መለኪያዎች እና ሳይንሳዊ የክብደት መለኪያዎች ማስረዳት ወይም ማብራራት፡፡

ማብራሪያ፡ ልማዳዊ የክብደት መለኪያ መሣሪያዎችን በመጠቀም የተለያዩ

ቁሶችን ክብደት መለካት ይቻላል፡፡

የቡድን ሥራ፡ 1 መልስ

1. ልማዳዊ ሚዛን፡፡
2. ክብደትን የምንለካው ቁሶችን ከባድ ወይም ቀላል ለማለት ነው፡፡
3. ክብደትን በልማዳዊ መለኪያ ወይም በሣይንሳዊ መስፈሪያ መለካት እንችላለን፡፡

ምሳሌ፡ በልማዳዊ የክብደት መለኪያ ክብደትን ማነፃፀር ይችላሉ፡፡ የኸውም መምህሩ ባህላዊ የክብደት መለኪያን ለማስረዳት ያክል ከታች በምሳሌው የምንመለከተውን መሰል ሚዛን

በማዘጋጀት ተማሪዎች ቀላል እና ከባድ የሆኑ ቁሶችን አስቀምጠው በማየት እንዲለዩ ማድረግ ይቻላል፡፡



ከልማዳዊ የክብደት ሚዛኑ እንደምንረዳው የኤሊዋ ክብደት ቀላል ሲሆን የጥንቸሏ ክብደት ደግሞ ከባድ መሆኑን ያሳየናል፡፡

ማስታወሻ፡ በቀኝ እና በግራ እጆቻችን የሁለት ቁሶችን ክብደት ማመዛዘን እንችላለን፡፡

ምዘና

- ተማሪዎች የተሰጣቸዉን ሁለት የተለያየ ክብደት ያላቸውን ቁሶች ክብደት ልማዳዊ የክብደት መለኪያ ሚዛንን ተጠቅመው እንዴት በትክክል መለካት እንደሚችሉ መመልከትና መገምገም፡፡

9.4 ክብደትን ማነፃፀር(5 ክፍለ ጊዜ)

መግቢያ፡ የተለያዩ ቁሶችን ክብደት በልማዳዊ የክብደት መለኪያ ወይም በሣይንሳዊ መለኪያ በመጠቀም ከባድ ወይም ቀላል በማለት ማነፃፀር እንዲችሉ ይማራሉ፡፡

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ንዑስ ርዕስ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- ሣይንሳዊ የርዝመት፤ የክብደትና የመጠን መለኪያን በመጠቀም ርዝመትን፤ክብደትንና መጠንን መለካት ይችላሉ
- የተለያዩ ቁሳቁሶችን ክብደት ያነፃፅራሉ፡፡

ዝርዝር ዓላማዎች፡ ከዚህ ክፍል ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡

- በኢትዮጵያ ልማዳዊ የክብደት ሚዛን ክብደትን ያነፃፅራሉ፡፡
- ሣይንሳዊ የክብደት መለኪያ ክብደት ያነፃፅራሉ፡፡
- ቁሶችን በመስፈር ከባድ ወይም ቀላል በማለት ይናገራሉ፡፡

ለርዕሱ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች

- ባህላዊ የክብደት መለኪያ ሚዛን፤
- ሳይንሳዊ የክብደት መለኪያ በማዘጋጀት ክብደትን መለካት፤
- በእጆች ማመዛዘን፡፡

የማስተማሪያ ስልቶች

- ተማሪዎችን በመኖሪያ ቤት፣ በአከባያቸው እንዲሁም በገበያ እና በሱቅ ውስጥ ክብደትን እንዴት እንደሚለኩ እንዲናገሩ ማበረታታት፡፡ ከተማሪዎች ምላሽ በመነሳት ስለ ኢትዮጵያ ልማዳዊ የክብደት መለኪያዎች እና ሳይንሳዊ የክብደት መለኪያዎች ማስረዳት ወይም ማብራራት፡፡

ማብራሪያ፡ የተለያዩ ቁሶችን ክብደት በልማዳዊ የክብደት መለኪያ ወይም በሣይንሳዊ መሥፈሪያ በመጠቀም ማነፃፀር ይቻላል፡፡ በተማሪው መማሪያ ላይ እንደተቀመጠው የተለያየ ክብደት ያላቸውን ጥንድ ቁሶችን በመውሰድ ተማሪዎች በግምት የትኛው ቁስ እነደሚከብድ መጠየቅ፡፡ ማንሳት የሚችሉት ቁስ ከሆነ ደግሞ አንስተው ክብደቱን እንዲናገሩ ማድረግና ባህላዊ ሚዛንም በመጠቀም ማነፃፀር ይችላሉ፡፡

የመልመጃ፡ 3 መልሶች



የ“ሀ” ምስል ቀላል ሲሆን የ“ለ” ምስል ከባድ ነው፡፡

2. **ሀ.** **ለ.**

ሰይክል

እርሳስ

የ“ሀ” ምስል ከባድ ሲሆን የ“ለ” ምስል ቀላል ነው፡፡

3. **ሀ.** **ለ.**

ኮፍያ

አናናስ

የ“ሀ” ምስል ቀላል ሲሆን የ“ለ” ምስል ከባድ ነው፡፡

9.4.1 ኪሎ ግራምንና ግራምን በመጠቀም ክብደትን መለካት

የተለያዩ ሣይንሳዊ የክበደት መለኪያዎች አሉ፡፡ ጥቂቶቹን ለመግለፅ ያክል የወርቅ ሚዛን፣ የዲጂታል ሚዛን፣ የተለያዩ ጥራጥሬዎችን ለመስፈር የምነጠቀምበት ሚዛን ወዘተ ናቸው፡፡ እነዚህም በተማሪው መማሪያ ላይ ተቀምጠዋል፡፡የቁሶችንም ክብደት ከለካን በኃላ የምናገኘዉን ዉጤት በኪሎ ግራም ወይም በግራም እንገልፃለን፡፡ ስለዚህ ሣይነሳዊ የክብደት መለኪያ አሃዶች የምንላቸው ኪሎግራም፣ ግራም የመሳሰሉት ናቸዉ፡፡

ማስታወሻ

1. ኪሎ ግራም በአጭሩ ሲፃፍ ኪ.ግ ሲሆን ግራም ደግሞ ግ ብለን በመፃፍ መግለፅ እንችላለን፡፡

2. ተመሳሳይ አሃድ ያላቸውን ምድቦች መደመርና መቀነስ ይችላሉ፡፡ ተመሳሳይ አሃድ የሚባሉት ኪ.ግ እና ኪ.ግ ወይም ግ እና ግ ናቸው፡፡

ምዘና

- ተማሪዎች የተሰጣቸዉን ቁስ ክብደት እንዴት በትክክል መለካት እንደሚችሉ መመልከትና መገምገም
- ልማዳዊ የክብደት መለኪያ ሚዛንን እና ሣይንሳዊ መለኪያን ተጠቅመው ሁለት የተለያዩ ቁሦችን ክብደት ከባድና ቀላል በማለት ማነፃፀር መቻላቸውን ማረጋገጥ

የመልመጃ፡ 4 መልስ

1. 10 ኪ.ግ 2. 22 ኪ.ግ 3. 28 ግ 4. 30 ግ 5. 75 ግ

9.5 የኢትዮጲያ ልማዳዊ የይዘት መለኪያ (4 ክፍለ ጊዜ)

መግቢያ፡ በዚህ ንዑስ ርዕስ ሰዎች በተለያዩ ቦታዎች የሚጠቀሟቸውን የመጠን መለኪያዎችን ወይም መስፈሪያዎችን ትማራላችሁ፡

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኃላ ተማሪዎች፡-

- ይዘትን በኢትዮጲያ ልማዳዊ የይዘት መለኪያ በመጠቀም ይለካሉ፤

ዝርዝር ዓላማዎች፡ ከዚህ ንዑስ ርዕስ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- የኢትዮጲያ ልማዳዊ የይዘት መለኪያን ይገልፃሉ፡፡
- የኢትዮጲያ ልማዳዊ የይዘት መለኪያን ይዘረዝራሉ፡፡
- በኢትዮጲያ ልማዳዊ የይዘት መለኪያ ይሰፍራሉ፡፡

ለርዕሱ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች

- ባህላዊ የመጠን መለኪያ ቁሳቁሶች ኩባያ፣ ማስታጠቢያ ፣ ጀሪካን፣ እንስራ፣ ቅል፣ ጀበና የመሳሰሉትን መጠቀም፡፡

የማስተማሪያ ስልቶች

- በተመሳሳይ መንገድ ተማሪዎች መጠንን ለመግለፅ የሚጠቀሙትን የተለያዩ መለኪያዎችን እንዲገልፁ ማበረታታት ከዚህም በመነሳት ቁና ፣ኩባያ፣ ማስታጠቢያ፣ ጆሪካን ወዘተ የተባሉትን ልማዳዊ የኢትዮጵያ የስፍረት መለኪያን መግለፅ። ስለ ሳይንሳዊ የስፍረት መለኪያዎች ማብራራትና በምሳሌ ማጠናከር።

ማብራሪያ፡ በዚህ ንዑስ ርዕስ ሰዎች በተለያዩ ቦታዎች የሚጠቀሟቸውን ልማዳዊ የይዘት መለኪያዎችን ወይም መስፈሪያዎችን እንመለከታለን። ልማዳዊ የይዘት መለኪያ የምንላቸው ቁና፣ ኩባያ፣ ማስታጠቢያ ፣ ጆሪካን የመሳሰሉት ናቸው።

ምዘና

- ተማሪዎች ልማዳዊ የመጠን መለኪያ ቁሶችን በመጠቀም የተለያዩ መጠን ያላቸውን እቃዎች የመያዝ አቅም በትክክል መለካት መቻላቸውን መመልከትና መገምገም

የተግባር፡ 3 መልሾች

ተማሪዎች ልማዳዊ የመጠን መለኪያዎችን ጠይቀው እንዲመጡ ማድረግ። በተጨማሪም ቁና ፣ኩባያ፣ ማስታጠቢያ ፣ጆሪካን የመሳሰሉትን በመጥቀስና እነዚህን ባህላዊ መስፈሪያዎች ከሣይንሳዊ መስፈሪያ ጋር ያላቸውን ቁርኝት በተግባር ሰፍሮ ማሳየትና ማብራራት።

9.6 ይዘትን ማነፃፀር (5 ክፍለ ጊዜ)

መግቢያ፡ ልማዳዊ የይዘት መሥፈሪያን ወይም ሊትርን በመጠቀም የቁሶችን የመያዝ አቅም ብዙ ወይም ትንሽ በማለት ይማራሉ።

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኃላ ተማሪዎች

- ሣይንሳዊ የርዝመት፤ የክብደትና የመጠን መለኪያን በመጠቀም ርዝመትን፤ክብደትንና መጠንን መለካት ይችላሉ፤
- የተለያዩ የይዘት መጠን ልኬቶችን ያነፃፅራሉ።

ዝርዝር ዓላማዎች፡ ከዚህ ንዑስ ርዕስ ትምህርት በኊላ ተማሪዎች

- በኢትዮጲያ ልማዳዊ የይዘት መለኪያ የይዘት ያነፃፅራሉ።
- ልማዳዊ የይዘት መለኪያዎችንና ሊትርን ያነፃፅራሉ።

- የቁሶችን የመያዝ አቅም ብዙ ወይም ትንሽ በማለት ይናገራሉ፡፡

ለርዕሱ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች

- ባህላዊ የመጠን መለኪያ ኩባያ፣ ማስታጠቢያ ፣ ጀሪካን ሊትርን ሚሊ ሊትርን መጠቀም፡፡

የማስተማሪያ ስልቶች

- ለተማሪዎች የተለያዩ ምሳሌዎችን በመጠቀም አንፃራዊ የንፅፅር ገላጭ ቃላትን ብዙ ወይም ትንሽ እንዲሉ ማድረግ ፡፡
- ከስፍር ወይም ከልኬት ጋር ተያያዥ የሆኑ የቃላት ፕሮብሌሞችን መስራትና ተማሪዎችን ማሰራት፡፡

ማብራሪያ፡ ልማዳዊ የይዘት መሥፈሪያን ወይም ሊትርን በመጠቀም

የቁሶችን የመያዝ አቅም ማወቅ እንችላለን፡፡

የተግባር፡ 4 መልሶች

1. የሻይ መጠጫ ብርጭቆና የዉሃ መጠጫ ብርጭቆ በማምጣት

   ለተማሪዎች ሰፍሮ ማሳየት፡፡ ተማሪዎችም በማየት የዉሃ መጠጫ ብርጭቆው ብዙ ውሃ መያዝ እንደሚችል ይረዳሉ፡፡

2. እቤታቸው ሰፍረው እንዲያዩት ማድረግ፡፡ ከዚያም የጀበናው የመያዝ አቅም እንደሚበልጥ በክፍል ውስጥ ሰፍሮ ማሳየት፡፡

የመልመጃ፡ 5 መልሶች

በተማሪው መማሪያ ማለትም በሰንጠረዡ ከተጠቀሱት አራቱ ምስሎች መካከል ትልቁና ብዙ ፈሳሽ መያዝ የሚችለው በ "**መ**" የተቀመጠው ወይም የሮቶው ምስል ሲሆን ከአራቱ ምስሎች ትንሽ ፈሳሽ የሚይዘው ደግሞ በ "**ለ**" የተቀመጠው የቡና መጠጫ ሲኒ ነው፡፡ የተቀሩት በ ሀ የተቀመጡት የጀሪካን ምስል እና በ ሐ የተቀመጡት የውሃ ማቅረቢያ ማንቆርቆሪያ ከሮተው ያነሰ የመያዝ አቅም እና ከቡና መጠጫ ሲነው የበለጠ የመያዝ አቅም አላቸው፡፡

የፈሳሽን ይዘት ወይም መጠን በሊትር ወይም በሚሊ ሊትር ይለካሉ።



ግማሽ ሊትር የሚይዝ ጆግ   1ሊትር የሚይዝ ጆግ   1ሊትር የወተት ጠርሙስ

የፈሳሽ ይዘት መስፈሪያ መሳሪያዎች ወይም ዕቃዎች ናቸው

ማስታወሻ፡ ሊትር በአጭሩ ሲፃፍ **"ሊ"** ተብሎ ይፃፋል።

20ሊትር = 20ሊ፣15ሊትር = 15ሊ፣ 10 ሊትር = 10ሊ፣ ግማሽ ሊትር = ግማሽ ሊ።

ምዘና

- የተለየዩ ቁሶችን በልማዳዊ የይዘት መለኪያና እንዲሁም ሊትርንና ሚሊ ሊትር ተጠቅመው መጠንን ማነፃፀር መቻላቸዉን ማረጋገጥ፤
- ልማዳዊ የይዘት መለኪያንና ሣይንሳዊ የይዘት መለኪያ በሊትርና በሚሊ ሊትር ማነፃፀር መቻላቸዉን ማረጋገጥ

የመልመጃ፡ 6 መልሶች

1. አንድ ሊትር ዕቃ፣ የሻይ ብርጭቆና ውሃ በማምጣት በክፍል ውስጥ ሰፍሮ ማሳየት። ስለዚህ 10 የሻይ ብርጭቆ ይይዛል።
2. የሁለቱ ድምር ማለትም 10 ሊትር ውሃ የሆናል።
3. ከ 25 ሊትር ውሃ ላይ 5 ን ስንቀንስ 20 ሊትር ውሃ ይቀራል።
4. 20 ሊትር መያዝ በሚችል ባልዲ 5 ጊዜ ብንጨምር በርሜሉ ይሞላል።

ይህ ማለት $20 + 20 + 20 + 20 + 20 = 100$ ሊትር ይሆናል።

የማጠቃለያ መልመጃ

1. የለስላሳ ጠርሙስ፣ ሲኒና ውሃ በማምጣት በክፍል ውስጥ ተማሪዎች ሰፍረው እንዲያሳዩ ማድረግ።

2. ከሒሳብ መፅሐፋቸው ይልቅ አንድ የክፍላቸው ወንበር ይከብዳል።

3. በአካባቢያቸው የሚያዉቋቸዉን የይዘት መለኪያዎችን ጠይቀው እንዲመጡ ማድረግ። ተጨማሪ መምህሩ ኩባያ፣ ማስታጠቢያ፣ ጀሪካን በመሳሰሉት ላይ ማብራሪያ ይሰጣል።

4. ተማሪዎች የርዝመት መለኪያ ሜትርን በመጠቀም የክፍላቸውን መጠነ ዙሪያ በመምህራቸው በመታገዝ ይለካሉ።

5. ተማሪዎች ማሥመሪያውን በመጠቀም የጠረጴዛቸውን ርዝመት በመምህራቸው በመታገዝ ይለካሉ።

6. ከ 16 ሜትር እንጨት ላይ 7 ሜትር እንጨት መቀነስ። $16 - 7 = 9$

7. ከ 90 ሊትር ላይ 55 ሊትር ስንቀንስ በርሜሉ ለመሙላት የሚቀረውን የውሃ መጠን እናገኛለን። 90ሊ.-55ሊ.=35ሊ. ይቀራል።

8. $65ኪ.ግ + 25ኪግ = 90ኪግ$

9. $50ግ + 50ግ = 100ግ$

10. $95ግ - 15ግ = 80ግ$

11. $81ሊ - 13ሊ = 68$ ሊ.

12. ታደሰ የሚቀረውን የስኳር መጠን ለማወቅ ከ26 ኪ.ግ ላይ 10 ኪ.ግን እንቀንሳለን። 26 ኪ. ግ-10 ኪ. ግ$= 16$ኪ. ግ ይቀረዋል።

13. 20ሜ ርዝመት ካለው መንገድ 30ሜ ርዝመት ያለው መንገድ ይርቃል።

14. በአጠቃላይ በርሜል ውስጥ ያለውን የውሃ መጠን ለማወቅ 50ሊ. እና 25ሊ. እንደምራለን። 50ሊ. + 25ሊ. = 75ሊ. ውሃ ይኖራል።

ምዕራፍ-10

የኢትዮጵያ ገንዘቦች (8 ክፍለ ጊዜ)

መግቢያ፡ ገንዘብ ማለት ሕዝቦች ለግብይት የሚገለገሉባቸው የብር ኖቶች ወይም የሳንቲም ዲናሮች ናቸው። ገንዘቦቹ የሚታተሙት በመንግሥት ሲሆን የተለያየ የዋጋ መጠን አላቸው።

የትምህርቱ ዓላማዎች፡ ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በሃላ ተማሪዎች፡

- የኢትዮጵያ የብር ኖቶችንና ሳንቲሞችን ይለያሉ።
- በየኢትዮጵያ የብር ኖቶችና ሳንቲሞች መካከል ያለዉን ዝምድና ይረዳሉ።
- ከፍዕራፉ ጋር ተያያዥ የሆኑ የቃላት ፕሮብሌሞችን ይሰራሉ።

ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኃላ ተማሪዎች፡

- የኢትዮጲያን የብር ኖቶችንና ሳንቲሞችን ለይተዉ ያዉቃሉ።
- በኢትዮጲያ ብር ኖቶችና ሳንቲሞች መካከል ያለዉን ዝምድና ይረዳሉ።
- ከምዕራፉ ጋር ተያያዥ የሆኑ የቃላት ፕሮብሌሞችን ይሰራሉ።

10.1 የኢትዮጵያ ሳንቲሞችና የብር ኖቶች (2 ክፍለ ጊዜ)

መግቢያ፡ የኢትዮጲያ ሳንቲሞችና የብር ኖቶች ለሕዝብ ለግብይት መገልገያ የሚውሉ ሲሆን ሁለቱም የፊትና የኃላ ገፅ አላቸው።

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኃላ ተማሪዎች።

- የኢትዮጵያን የብር ኖቶችንና ሳንቲሞችን ይለያሉ።

ዝርዝር ዓላማዎች፡ ከዚህ ንዑስ ርዕስ ትምህርት በኂላ ተማሪዎች

- የኢትዮጵያ የብር ኖቶችን ይለያሉ።
- የኢትዮጵያ የሳንቲም ዲናሮችን ይለያሉ።
- በኢትዮጵያ ገንዘቦች መገበያየት ይለማመዳሉ።

ለርዕሱ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች

- የ1 ብር ሣንቲም፣ የ50 ሣንቲም ፣ የ25 ሣንቲም፣ የ10 ሣንቲም የ5 ሣንቲም እና የአንድ ሣንቲም ዲናሮች፡፡

የማስተማሪያ ስልቶች

- የኢትዮጵያን የገንዘብ ኖቶችንና ሳንቲሞችን ወይም ምስሎቻቸዉን ለተማሪዎች በማሳየት ስዕሎችን በመጠቀም በገንዘብ ኖቶች ወይም ሳንቲሞች መካከል ያለዉን ልዩነት ለተማሪዎች ማብራራት፡፡
- ተማሪዎች 10 እና 25 ሳንቲሞችን በመጠቀም ከ 100 ብር ያነሱ ዋጋዎችን እንዲቆጥሩ ማድረግ፡፡ እንዲሁም የተለያዩ ሳንቲሞችን በመጠቀም ዋጋዉ 100 ሳንቲም የሆነ አገላለፅ እንዲጠቀሙ ማበረታታት፡፡ ከዚህ በመነሳት በሳንቲሞች መካከል ያለዉን ቁርኝት ለተማሪዎች ማስረዳት፡፡

ማብራሪያ፡ ከዚህ በታች የምትመለከቷቸው የሳንቲም ዲናሮች ሁለት ገፅ ያላቸው ሲሆኑ የኢትዮጵያ ገንዘቦች ናቸው፡፡

አንድ ሣንቲም	**አምስት ሣንቲም**	**አሥር ሣንቲም**	**ሃያ አምስት ሣንቲም**	**ሃምሣ ሣንቲም**	**የአንድ ብር ሣንቲም**

አስተውሉ፡ ሁሉም ሣንቲሞች የፊትና የጀርባ ምስሎች አሏቸው፡፡

የ 1 ባለ 5 ሣንቲም ዲናር በ 5 የባለ አንድ ሣንቲም ዲናሮች ይለወጣል ወይም ይመነዘራል፡፡

የ አንድ ባለ 10 ሣንቲም ዲናር በ 2 የባለ አምሥት ሣንቲም ዲናሮች ይለወጣል ወይም ይመነዘራል፡፡

የ አንድ ባለ 50 ሣንቲም ዲናር በ 2 የባለ 25 ሣንቲም ዲናሮች ይለወጣል ወይም ይመነዘራል፡፡

የ አንድ ባለ 50 ሣንቲም ዲናር በ 5 የባለ 10 ሣንቲም ዲናሮች ይለወጣል ወይም ይመነዘራል፡፡

የቡድን ሥራ 1 መልሶች

1. **የ1 ብር ሣንቲም ዲናር**፡ በ2 ባለ 50 ሣንቲም ዲናር፣ በ4 ባለ 25 ሣንቲም ዲናር፣ በ10 ባለ አሥር ሣንቲም ዲናር በ20 ባለ አምስት ሣንቲም እና በ100 የአንድ ሣንቲም ዲናሮች ይመነዘራል፡፡

2. **የባለ 50 ሣንቲም ዲናር**፡ በ2 ባለ 25 ሣንቲም ዲናር፣ በ5 ባለ አሥር ሣንቲም ዲናር በ10 ባለ አምስት ሣንቲም እና በ50 የአንድ ሣንቲም ዲናሮች ይመነዘራል፡፡
3. **የባለ 25 ሣንቲም ዲናር**፡ በ2 ባለ አሥር ሣንቲም በ1 ባለ አምስት ሣንቲም እና በ25 የአንድ ሣንቲም ዲናሮች ይመነዘራል፡፡

የመልመጃ፡ 1 መልሶች

1. ሀ) አንድ ባለ አሥር ሣንቲም ዲናር በ10 ባለ አንድ ሣንቲም ዲናሮች ይመነዘራል፡፡

ለ) አንድ ባለ 25 ሣንቲም ዲናር በአምስት ባለ 5 ሣንቲም ዲናሮች ይመነዝራል፡፡

ሐ) አንድ ባለ 50 ሣንቲም ዲናር በአሥር ባለ 5 ሣንቲም ዲናሮች ይመነዝራል፡፡

2. የሠንጠረዡ መልስ እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

የተሰጡት የሣንቲም ዲናሮች	በባለ 1 ሣንቲም ምንዛሬው ስንት እንደሚሆን ግለፁ	በባለ 5 ሣንቲም ምንዛሬው ስንት እንደሚሆን ግለፁ	በባለ 10 ሣንቲም ምንዛሬው ስንት እንደሚሆን ግለፁ	በባለ 25 ሣንቲም ምንዛሬው ስንት እንደሚሆን ግለፁ
50 ሳንቲም	50	10	5	2
25 ሳንቲም	25	5		
10 ሳንቲም	10	2		
5 ሳንቲም	1			

የብር ኖቶች

የኢትዮጵያ የብር ኖት ምስሎች ሁሉም የፊትና የኃላ ገፅ አላቸው፡፡ እነሱም የአምስት ብር ኖት፣ የአሥር ብር ኖት፣ የሃምሣ ብር ኖት፣ የመቶ ብር ኖት እና የሁለት መቶ ብር ኖት ናቸው፡፡

ምዘና

- ተማሪዎች በብርና በሣንቲም መካከል ያለዉን ቁርኝት እንዴት እንደሚያብራሩ ማጤንና መከታተል፡፡
- የቤት ሥራ በመስጠት በብርና በሣንቲም መካከል ያለዉን የምንዛሬ መጠን አጥንተው እንዲመጡ ማድረግና መገምገም

የመልመጃ፡ 2 መልሶች

የተሰጠው የብር ኖት	ምንዛሪ			
	በባለ 5 ብር ኖት	በባለ 10 ብር ኖት	በባለ 50 ብር ኖት	በባለ 100 ብር ኖት
ባለ 200 ብር	40	20	4	2
ባለ 100 ብር	20	10	2	
ባለ 50 ብር	10	5		
ባለ 10 ብር	2			

10.2 የሣንቲሞችና የብር ኖቶች ዝምድና (3 ክፍለ ጊዜ)

መግቢያ፡ በዚህ ንዑስ ርዕስ ተማሪዎች እንዴት የብር ኖቶች በሣንቲሞች ሊመነዘሩ ወይም ሊለወጡ እንደሚችሉ ይመለከታሉ፡፡

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት: ከዚህ ትምህርት በኃላ ተማሪዎች፡-

- በኢትዮጲያ ብር ኖቶችና ሳንቲሞች መካከል ያለዉን ዝምድና ይለያሉ፡፡

ዝርዝር ዓላማዎች፡ ከዚህ ንዑስ ርዕስ ትምህርት በኂላ ተማሪዎች፡-

- የሣንቲሞችን ዝምድና ይለያሉ፡፡
- የብር ኖቶችን ዝምድና ይለያሉ፡፡
- በሣንቲሞችና በብር ኖቶች መካከል ያለውን ዝምድና ይለያሉ፡፡

ለርዕሱ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች

- የ1 ብር ሣንቲም፣ የ50 ሣንቲም ፣ የ25 ሣንቲም፣ የ10 ሣንቲም እና የ5 ሣንቲም ዲናሮች
- የ 5 ብር ኖት፣ የ10 ብር ኖት፣ የ50 ብር ኖት፣ የ100 ብር ኖት እና የ200 ብር ኖት

የማስተማሪያ ስልቶች

- ተማሪዎች በቡድን ሆነዉ በአስር ሣንቲም እና በአንድ ብር መካከል ያለዉን ቁርኝት እንዲወያዩ ማድረግ፡፡ ከዉይይት ምላሻቸዉ በመነሳት በአንድ ብር የገንዘብ ኖትና በአስር ሣንቲም መካከል ያለዉን ቁርኝት መግለፅ፡፡

- ተማሪዎች በኢትዮጵያ የገንዘብ ኖቶች መካከል ያለዉን የምንዛሬ ግንኙነት ተራ በተራ እንዲገልፁ በማድረግ በገንዘብ ኖቶች መካከል ያለዉን ቁርኝት በምሳሌ ማስረዳት፡፡

ማብራሪያ፡ የብር ኖቶች በሣንቲሞች ሊመነዘሩ ይችላሉ፡፡

ምሳሌ፡

1) አንድ የ5 ብር ኖት በ 10 የ 50 ሣንቲም ዲናሮች ይመነዘራል፡፡ እንዲሁም ይኸዉ የ 5 ብር ኖት በ 20 የሃያ አምስት ሣንቲም ዲናሮች ሊመነዘር ይችላል፡፡
2) በተመሳሳይ መልክ አንድ የ 10 ብር ኖት በ 20 የ 50 ሣንቲም ዲናሮች ሊመነዘር ይችላል፡፡

የቡድን ሥራ 2 መልሶች

1. ተማሪዎች ከዚህ በታች በሰንጠረዡ የተሰጡትን ያጠናሉ፡፡

የብር ኖት	ባለ 1 ሣንቲም ዲናሮች	ባለ 5 ሣንቲም ዲናሮች	ባለ 10 ሣንቲም ዲናሮች	ባለ 25 ሣንቲም ዲናሮች	ባለ 50 ሣንቲም ዲናሮች	ባለ 1 ብር ሣንቲም ዲናር
5		100	50	20	10	5
10			100	40	20	10

2. የሣንቲምና የብር ኖት ሞዴሎችን ከወረቀት ወይም ከሌላ በአካባቢዉ ከሚገኝ ነገር ሰርተው እንዲያቀርቡ መምህሩ እገዛ ያደርጋል፡፡
3. ሞዴሎችን በመጠቀም በተራ ቁጥር 1 ከተሰጡት ጋር በማዛመድ ይወያያሉ፡፡
4. ሞዴሎችን በመጠቀም በቡድን ሆነው ሻጭ እና ገዢ በመሆን ከዚህ በታች የጠሰጠውን የዋጋ ተመን ተጠቅመው ቁሳቁሶችን ይለዋወጣሉ፡፡ መምህሩም እገዛ ያደርጋል፡፡

    1 ደብተር………………………………13 ብር

    1 የሒሳብ መጽሐፍ………………… 38 ብር

    1 እርሳስ………………………………..2 ብር

    1 እስክሪብቶ…………………………...10 ብር

ምዘና

- ተማሪዎች ቁጥሮችን ከብርና ከሳንቲም ጋር እንዴት ማዛመድ እንደሚችሉ መመልከትና መገምገም

10.3 ፕሮብሌሞችን መስራት (3 ክፍለ ጊዜ)

መግቢያ፡ እስከ አሁን ድረስ ስለ ብር ኖቶች፣ ስለ ሣንቲሞችና ዝምድናቸው ተምረዋል፡፡ በዚህ ንዑስ ርዕስ ደግሞ የተለያዩ የብር ኖቶችንና ሣንቲሞችን በተመለከተ የተሠጡትን ፕሮብሌሞች ይሰራሉ፡፡

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት: ከዚህ ትምህርት በኃላ ተማሪዎች

- በኢትዮጵያ ብር ኖቶችና ሣንቲሞች መካከል ያለዉን ዝምድና ይለያሉ፡፡

ዝርዝር ዓላማዎች፡ ከዚህ ንዑስ ርዕስ ትምህርት በኂላ ተማሪዎች፡-

- በሣንቲሞችና በብር ኖቶች የተሰጡትን ፕሮብሌሞች ያሰላሉ፡፡
- የቃላት ፕሮብሌሞችን ወደ ቁጥር በመቀየር ያሰላሉ፡፡

ለርዕሱ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች

- የ1 ብር ሣንቲም፣ የ50 ሣንቲም ፣ የ25 ሣንቲም፣ የ10ሣንቲም እና የ5 ሣንቲም ዲናሮች፤
- የ 5 ብር ኖት፣ የ10 ብር ኖት፣ የ50 ብር ኖት፣ የ100 ብር ኖት እና የ200 ብር ኖት፡፡

የማስተማሪያ ስልቶች

- በገንዘብ የተከናወኑ ሽያጭ እና ግዢ ያለባቸዉ ቀላል የቃላት ፕሮብሌሞችን ለተማሪዎች መስራትና እንዲሰሩ ማበረታታት፡፡

ማብራሪያ

የአንድ ሳሙና ዋጋ 22 ብር ቢሆን የሁለት ሳሙናዎች ዋጋ ስንት ብር ይሆናል?

$22 \text{ ብር} + 22 \text{ ብር} = 44 \text{ ብር}$

ምዘና

- ተማሪዎች ቁጥሮችን ከብርና ከሣንቲም ጋር እንዴት ማዛመድ አንደሚችሉ መመልከትና መገምገም

የመልመጃ፡ 3 መልሶች

1. የዳቦውን እና የሻዩን ዋጋ መደመር፡፡

   2 ብር + 1 ብር ከ 50 ሣንቲም = 2 ብር ከ 50 ሣንቲም

2. ከ 30 ብር ላይ የሳሙናውን ዋጋ መቀነስ፡፡ 30 ብር − 22 ብር = 8 ብር ይመለሳል፡፡
3. 18 ብር + 18 ብር = 36 ብር ይሆናል፡፡

የማጠቃለያ መልመጃ

1. አንድ የመቶ ብር ኖት
   - ሀ) በ20 የ5 ብር ኖቶች ይመነዘራል፡፡
   - ለ) በ2 የ 50 ብር ኖቶች ይመነዘራል፡፡
2. አንድ የ10 ብር ኖት
   - ሀ) በ20 የባለ 50 ሣንቲም ዲናሮች ይመነዘራል፡፡
   - ለ) በ40 የባለ 25 ሣንቲም ዲናሮች ይመነዘራል፡፡
   - ሐ) በ100 የባለ 10 ሣንቲም ዲናሮች ይመነዘራል፡፡
3. አንድ ባለ 5 ብር ኖት
   - ሀ) በ50 የባለ 10 ሣንቲም ዲናሮች ይመነዘራል፡፡
   - ለ) በ20 የባለ 25 ሣንቲም ዲናሮች ይመነዘራል?
   - ሐ) በ10 የባለ 50 ሣንቲም ዲናሮች ይመነዘራል፡፡

ምዕራፍ-11

የኢትዮጵያ ጊዜ (8 ክፍለ ጊዜ)

መግቢያ፡ በዚህ ምዕራፍ ተማሪዎች በአንድ ቀን ውስጥ የሚጠቀሱ ጊዜያትን፣ የሣምንቱን ቀናት እና የቃላት ፕሮብሌምን መሥራት ይማራሉ፡፡

የትምህርቱ ዓላማዎች፡ ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኃላ ተማሪዎች

- የሳምንቱን ቀናት ይገልፃሉ፡፡
- የዕለት ተግባራቸዉን በቅደም ተከተል ይገልፃሉ፡፡
- መአንድ መሥመር የሚፈቱ ፕሮብሌሞችን ይሰራሉ፡፡

11.1 በቀን ዉስጥ የሚጠቀሱ የኢትዮጵያ ጊዜያት (2 ክፍለ ጊዜ)

መግቢያ፡ አንድን ቀን በብዙ ቦታ ከፋፍለን መግለፅ እንችላለን፡፡ እነዚህም ጠዋት፣ እኩለ ቀን፣ ማታ፣ ሌሊትና እኩለ ሌሊት ዋና ዋናዎቹ ናቸዉ፡፡

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት: ከዚህ ትምህርት በኃላ ተማሪዎች

- የእጅ ሰዓት በመጠቀም ጊዜን ይገልፃሉ፡፡

ዝርዝር ዓላማዎች፡ ከዚህ ንዑስ ርዕስ ትምህርት በኂላ ተማሪዎች

- በኢትዮጲያ በቀን ውስጥ የሚጠቀሱ ጊዜያትን ይዘረዝራሉ፡፡
- በቀን ውስጥ የሚጠቀሱ የኢትዮጲያ ጊዜያትን ይዘረዝራሉ፡፡

ለርዕሱ የሚያስፈልጉ ግበዓቶች

- የሰዓት ሞዴል፣ የእጅ ሰዓት፣ የግድግዳ ሰዓት ወዘተ

የማስተማሪያ ስልቶች

- በአንድ ቀን ዉስጥ የሚጠቀሱ ጊዜያትን ለተማሪዎች መግለፅ። **እነሱም**፡- ጠዋት፤ እኩለ ቀን፤ ማታና እኩለ ሌሊት ናቸዉ።

ማብራሪያ፡ አንድን ቀን በብዙ ቦታ ከፋፍለን መግለፅ እንችላለን። እነዚህም ጠዋት፣ እኩለ

ቀን፣ ማታ፣ ሌሊትና እኩለ ሌሊት ዋና ዋናዎቹ ናቸዉ።

ፀሐይ አንዴ ወጥታ፣ ጠልቃ፣ ተመልሳ እስክትወጣ ያለዉ ጊዜ አንድ ቀን ተብሎ ይታወቃል ። እያንዳንዱ ቀን 24 ሰዓታት አሉት። የተለያዩ ዓይነት የሰዓት መቁጠሪያዎች አሉ። ቀጥሉ የሚታዩት የሰዓት መቁጠሪያ ምስሎች ናቸዉ።





ከላይ ያሉት ምስሎች ሁለቱም የሰዓት መስፈሪያ ሞዴሎችን ያመለክታሉ።

የሰዓት መስፈሪያ ሞዴሎች

1) በቀኝ በኩል ያለዉ የሰዓት መቁጠሪያ ስዕል ነዉ። ይህም ዕቃ ሰዓት ይባላል። በዚህ ዕቃ ላይ ወፈር ብሎ አጠር ያለ ጨረር እና ቀጥን ብሎ ረዘም ያለው ጨረር ይታያል። ረዥሙ ጨረር፡ ደቂቃን ያመለክታል። አጭሩ ጨረር፡ ሰዓትን ያመለክታል።



2) በቀኝ በኩል ያለዉ ምስል የሰዓት መቁጠሪያ ዕቃ ነዉ፡፡
ከዚህ ላይ ሰዓትን አንብቦ መናገር ብቻነዉ፡፡
ለምሳሌ በተሰጠዉ ምስል ላይ 6፡00 ን
ያመለክታል፡፡ ሲነበብም ስድስት ሰዓት ተብሎ ነዉ፡፡

የመልመጃ፡ 1 መልሶች

ሀ) በምሳሌው መሰረት መልሶች እንደሚከተሉት ይሆናል፡፡

1. 4፡00
2. 11፡00
3. 8፡00
4. 7፡00
5. 3፡00
6. 5፡00
7. 6፡00
8. 10፡00
9. 1፡00

ለ) በምሳሌው መሰረት መልሶቹ እንደሚከተለው ይሆናሉ፡፡

3.



ከ 4 ሰዓታት ቀጥሎ

4.



ከ 5 ሰዓታት ቀጥሎ

ምዘና

- ተማሪዎች ጊዜን በተመለከተ የወጡ ጥያቄዎችን ማለትም በቀን ውስጥ የሚከናወኑትን ተግባራት አንድ በአንድ መግለፅ መቻላቸውን ማረጋገጥ

11.2 የሣምንቱ ቀናት (3 ክፍለ ጊዜ)

መግቢያ፡ በኢትዮጵያ የሣምንቱ ቀናት ሰባት ናቸው፡፡ ተማሪዎች እነዚህን ቀናት ለይተው ማወቅና በእነዚህ ቀናት ውስጥ የሚከናወኑትን ተግባራት በዝርዝር ይማራሉ፡፡

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት፡ ከዚህ ትምህርት በኃላ ተማሪዎች

- የሳምንቱን ቀናት ይገልፃሉ፡፡

ዝርዝር ዓላማዎች፡ ከዚህ ንዑስ ርዕስ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- የሣምንቱን ቀናት ይዘረዝራሉ፡፡
- የሣምንቱን ቀናት ይፅፋሉ፡፡
- በሣምንት ውስጥ የሚከናወኑ ተግባራትን ይናገራሉ፡፡

ለርዕሱ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች

- የሣምንቱ ቀናት የያዘ ቻርት ወይም በራሪ ወረቀት ማዘጋጀት

የማስተማሪያ ስልቶች

- ተማሪዎች በተደጋጋሚ የሚፈፅሙትን የዕለት ተግባራቸዉን እንዲገልፁ ማድረግ፡፡
- በሳምንት ዉስጥ ያሉትን ቀናት መግለፅ፡፡ አንድ ቀን በምሳሌ በመስጠት ከቀኑ በፊት እና በኃላ ያለዉን ቀን እንዲገልፁ ማድረግ፡፡

ማብራሪያ፡ ከላይ አንድ ቀን በ24 ሰዓታት እንደሚከፋፈል አይተዋል፡፡

ይህም ማለት 24 ሰዓታት አንድ ቀን እንደሚሆን ያሳያል፡፡

በተመሳሳይ 7 ቀናት አንድ ሳምንት ይሆናሉ፡፡ የሳምንቱም ቀናት

የየራሳቸው ስም አሏቸዉ፡፡

የሚከተሉት የሳምንቱ ቀናት ናቸው፡፡ እነሱም ሰኞ ፣ ማክሰኞ፣ ረቡዕ ፣ ሐሙስ ፣ ዓርብ፣ቅዳሜ እና እሁድ ናቸው፡፡

የቡድን ሥራ 1 መልስ

- በመምህሩ በመታገዝ የሳምንቱን ቀናት የሚገለፅ መዝሙር ይዘምራሉ፡፡

ምዘና

- ተማሪዎች የሣምንቱን ቀናት አንድ በአንድ ለማስታወስ ይረዳቸው ዘንድ በየዕለት የሚያከናውኗቸውን ተግባራት መዘርዘር መቻላቸውን ማረጋገጥ
- ከሰኞ እስከ እሁድ ያሉ ቀናትን በትክክል መጥራታቸውን ማረጋገጥ

የመልመጃ፡ 2 መልስ

1. አንድ ቀን 24 ሰዓታት ሲሆን ሁለት ቀናት $24 + 24 = 48$ ሰዓታት ይኖሩታል፡፡
2. አንድ ሣምንት 7 ቀናት ሲኖረው ሁለት ሳምንታት $7 + 7 = 14$ ቀናት ይኖሩታል፡፡
3. ረቡዕ 4. ቅዳሜ 5. ማክሰኞ 6. ቅዳሜ

11.3 የቃላት ፕሮብሌሞች (3 ክፍለ ጊዜ)

መግቢያ፡ በዚህ ንዑስ ርዕስ ተማሪዎች የሣምንቱን ቀናትና በቀን ውስጥ የሚጠቀሱ

ጊዜያትን በተመለከት የተሰጡ የቃላት ፕሮብሌሞች በጥልቀት በመረዳት ይሰራሉ፡፡

የትምህርቱ ተፈላጊ ብቃት: ከዚህ ትምህርት በኃላ ተማሪዎች

- ጊዜን በተመለከተ የቃለት ፕሮብሌሞች ይሰራሉ

ዝርዝር ዓላማዎች፡ ከዚህ ንዑስ ርዕስ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- የሣምንቱን ቀናት የሚመለከት የቃላት ፕሮብሌም ይሰራሉ፡፡
- በቀን ውስጥ የሚጠቀሱ ጊዜያትን በተመለከተ የተሰጡ የቃላት ፕሮብሌም መረዳት ይናገራሉ፡፡

ለርዕሱ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች

- የሣምንቱ ቀናት የያዘ ቻርት ወይም በራሪ ወረቀት ማዘጋጀት፤
- የሰዓት ሞዴል የእጅ ሰዓት፣ የግድግዳ ሰዓት የመሳሰሉትን መጠቀም፡፡

የማስተማሪያ ስልቶች

- የጊዜን ልኬት የተለያዩ የጊዜ መለኪያ በመጠቀም ማስረዳት፡፡

ማብራሪያ

ሶስት ሳምንቶች ስንት ቀናት አላቸው?

ሶስት ሳምንት = 1 ሳምንት + 1 ሳምንት + 1 ሳምንት

= 7 ቀናት + 7 ቀናት + 7 ቀናት

= 21 ቀናት

ምዘና

- ተማሪዎች ጊዜንና የሣምንቱ ቀናትን በተመለከተ የወጡ ጥያቄዎችን ተረድተው በምን መልኩ እንደሚመልሱ ማየትና ጥያቄዎችን በመስጠት መገምገም

የመልመጃ: 3 መልሶች

1. አንድ ቀን 24 ሰዓት ሲሆን ሶስት ቀናት $24 + 24 + 24 = 72$ ሰዓታት ይሆናል፡፡
2. 3 ቀናት + 2 ቀናት = 5 ቀናት፡፡
3. 4 ሣምንት ወይም 30 ቀናት፡፡
4. 2 ቀናት ወይም 48 ሰዓታት፡፡

የማጠቃለያ መልመጃ

አዛምድ

1. ሐ 2. ሠ 3. ሰ 4. ሀ 5. መ